# 90 ደቂቃ
# በመንግሥተ ሰማይ ደጅ

ሞቶ የተመለሰ ሰው እውነተኛ
የሕይወት ታሪክ

ዶን ፒፐር
ከሲስል ሙርፊ ጋር በመተባበር

ተርጓሚ ደረጀ በቀለ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 2001 ዓ.ም.

# 90 ደቂቃ
# በመንግሥተ ሰማይ ደጅ

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
90 Minutes in Heaven
ከሚለው መጽሐፍ ነው።
Don Piper with Cecil Murphey

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም
እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RPTR-29 3M

"እኩለ ሌሊት አካባቢ ጓደኛዬ ይህንን መጽሃፍ ሰጠኝ፤ እናም ከማለዳው ወደ ሁለትና ሦስት ሰዓት አካባቢ ተመልሶ መጣ፤ በዚያ ጊዜም እያነበብኩት ነበር:: በአመለካከትዎ ላይ ብርሃን የሚፈነጥቅ፣ ደህንነትዎን የሚያረጋግጥልዎት ግልጽነትና ሞቅ ያለ ስሜት እንዲሰማዎ የሚያደርግ አስደናቂና በመገለጥ የተሞላ መጽሐፍ ነው::"

ዶናአልድ ሚለር

የብሉ ሌክ ጃዝ

ደራሲ

"የዶን ፒፐር ዘጠና ደቂቃ በመንግሥተ ሰማይ የሚለው ይህ መጽሐፍ ሕይወቱንና አመለካከቱን ለውጦታል:: ይህንን መጽሐፍ ማንበብዎ እግዚአብሔር እጅግ ዘግናኝ ከሆነ ሁኔታዎ ውስጥ እንኳን አሳልፎ ሊያወጣዎ ታማኝ እንደሆነ እንዲተማመኑ ያስችልዎታል:: የዚህ ሰው የአይን ምስክርነት ዘገባ በፊትዎ ስላለው ተስፋና ስለዚህም ሕይወት ያለዎትን አመለካከት ይቀይረው!"

ሚካኤል ካርተር

የሲ.ቢ.ኤን የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

"ማራኪነት ያለውና በወጉ የተጻፈው ይህ መጽሐፍ ቀልብዎን ብዙውን ጊዜም ልብዎን ገዝቶ ይይዛል:: ዶን ታሪኩንና ክርስቲያኖች ሁሉ ሊሰሙት የሚናፍቁትን የሕይወት ልምዱን ያጫውተናል:: የሕይወት ልምምዱ መንፈስዎን ያነቃቃል የውስጥዎንም ስቃይ ያስረሳል:: "

ሮን ሂል

የሳን አንቶኒዬ ፈሎሽፕ ፓስተር

**ለፀሎት ጦረኞች ...**

**እናንተ በመጸለያችሁ እኔ በዚህ አለሁ!**



# ማውጫ

**ገጽ**

ምስጋና 7

መቅድም 12

1. አደጋው ..........13
2. የመንግሥተ ሰማይ ቆይታዬ..........22
3. ሰማያዊ ዝማሬ..........34
4. ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ምድር ..........45
5. በምድር ሆስፒታል ውስጥ ..........56
6. እየተሻለኝ መጣ..........71
7. ውሣኔና ተግዳሮቶች ..........86
8. የሕመም ስቃይና ማስተካከያዎቹ ..........101
9. ማለቂያ የሌለው ማስተካከያ ..........125
10. ተጨማሪ ተዓምራት..........139
11. ወደ ቤተክርስቲያን መመለስ..........152
12. መንገዱ ተከፈተ..........174
13. አጥብቆ የያዘኝ እጅ..........188
14. አዲሱ ሕይወት..........193

**15. ነፍሳትን መድረስ ......................................................................224**

**16. ዓላማን ማወቅ ......................................................................258**

**17. ወደ ቤቴ እናፍቃለሁ ......................................................................277**

**18. ለምን? ......................................................................284**



# ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ የጻፍኩት ራሴን የሚገባውን ያህል ለመግለጽ ነው:: ከ1989 ጀምሮ የሕይወት ልምምዴን እንደገና በመናገር ፈጣን ወይም የተብራራ መልስ በመስጠት ብዙዎችን ማርካት እንዳልቻልኩ ተገንዝቤአለሁ:: በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጦች፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው መድረኮችና ንግግር እንዳደርግ በተጋበዝኩባቸው ሥፍራዎች ሁሉ፤ አመርቂ የሆነ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በጥቅሉ ሲታይ በርካታ ጥያቄዎችን ሳልመልስ ቀርቻለሁ:: ሰዎች ያለማቋረጥ ተጨማሪ ነገሮችን ማወቅ ይፈልጋሉ . . . ሁልጊዜም ተጨማሪ:: በጥያቄ የተሞሉ የሰዎችን አዕምሮዎች ለማርካት ይህን ተሞክሮየን አስመልክቼ ሦስት ያህል ጽሑፎችን ጽፌአለሁ:: ሁሉም እርካታን አልሰጡኝም:: በዚያ ጊዜ ነበር እጅግ አጠያያቂ ለሆነው የሞቴና የሕይወቴ ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት፤ በአሜሪካ ታዋቂ ከሆኑት የመጽሐፍ ደራሲ ጋር በመተባበር አንድ መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሣሁት:: ስሲል ሙርፊ፤ የፍራንክሊን ግራሃማን፣ ትሩት ካቲን፣ የቢ.ጄ ቶማስን፣ የዲኖ ካርስ እንካስንና የዶ/ር ቢን ካርስንን የሕይወት ታሪክ በመጻፍ ኮከብ የሆኑ ሰው ናቸው:: እኚህ ሰው ናቸው አሁን በእጅዎ የያዙትን መጽሐፍ ልጽፍ በፈለግኩበት መንገድ እጽፍ ዘንድ አቅጣጫን ያመላከቱኝ::

ስሲል ታማኝ፣ ልብ የሚጣልባቸውና መልካም ምክር የሚለግሱ ጓደኛዬ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ:: በርግጥም ይህንን መጽሐፍ በማዘጋጀት ካገኘኋቸው በረከቶች አንዱ ከስሲል ሙርፊ ጋር መተዋወቅ መቻሌ ነው:: በመጽሐፍ ዝግጅቱ ሂደት ውስጥ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ብርቱ ጥረታቸው ታክሎበታል:: አመሰግናለሁ ሲስ! በጥልቀት ሲመሰገኑ የሚገባዎ ነዎት:: እንደዚሁ ደግሞ ከናይት ኤጀንሲ የሆኑት ዴድር

ናይት በመጽሐፍ ዝግጅት ላይ የነበራቸው ታላቅ እምነት በእጅጉ የሚመሰገን ነው። በተጨማሪም ከባከር አታሚዎች ሕብረት ለሆኑት ዶ/ር ቪ.ክ. ክሩሞፐቶን አድናቆቴ እየጨመረ የሚሄድ ነው። ታሪኩ ታትሞ ለማየት በነበራት ፍላጎት ያደረገችው ጥረት ታላቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው።

የኸርማነን መታሰቢያ የህክምና ማዕከል የጉዳተኞች ክፍልንና በሆስተን የሚገኘው የቅዱስ ሉቃስ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ የነበሩ የህክምና ባለሞያዎች ለሰውነቴ መዳን ስላደረጉት ትልቅ ጥረት ላመስግናቸው እወዳለሁ። ይልቁንም ደግሞ ከዚያች ከጥር 18፤ 1989 አስጨናቂ ሌሊት ጀምሮ የኦርቶፔዲክ ቀዶ ጥገና ህክምና ሲያደርጉልኝ ለቆዮት ለዶ/ር ቶማስ ገራደር የተለየ ምሥጋና አቀርባለሁ።

እጅግ በርካታ በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ የተወደዱ የእግዚአብሔር ህዝቦች እንዳገለግላቸው ፈቅደውልኛል። በሕይወት ለመኖሬ የሚያደርጉልኝ ጸሎት ወሳኝ ነበር፤ ይልቁን ደግሞ በአካል ተገኝተው ማጽናናታቸው ለአገልግሎቴ ታላቅ በረከት ሆኗል። በአልቪን፣ በቴክሳስ ለሚገኙ የደቡብ ፓርክ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ታላላቅ የፀሎት ጦረኞት የጠለቀ ምስጋናዬን እነሆ እላለሁ። የተለየ አስተዋጽኦዋቸውን ላደረጉልኝ ለመጀመሪያው የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን፣ የኤርላይን መጥምቃውያን ቤተክርስቲያንና የባርክስዳል መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን፣ በሉሲያን ለምትገኘው ለመላዋ የቦስሲር ከተማም ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የእኚህ የሁለቱ አብያተ ክርስቲናት የቀድሞ እረኛ የነበሩት አባቴ ዶ/ር ዳሞን ቪ. ቫሁገን የጣሉብኝ ውለታ እጅግ ታላቅ ነው።



አደጋው ከደረሰብኝ ጊዜ አንስቶ በታማኝነት አጠገቤ ለቆሙት በሮሻሮን፣ በቴክሳስ ለሚገኙት የመጀመሪያዋ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን፣ በቴክሳስ ፕሌኖ ውስጥ ለሚገኙ የሃንተርስ ግሊንና በሙርፊ ጎዳና የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የአገልግሎት መስማሪያዎቼ ነበሩና ህያው የሆነ ፍቅሬን ለመግለጽ እፈልጋለሁ። ይህ የመጽሐፍ ዝግጅት እንዲጠናቀቅ ያደረጋችሁልኝ ድጋፍ መልካምና ያልተቋረጠ ነበር።

ለአኒታ ዋንሪከርና ለሚቹ ባለቤትዋ ጂክ እግዚአብሔር በዚህ ሥራ ላይ አስደናቂ በሆነ መንገድ እንዲጠቀምባችሁ ፈቅዳችኋልና አመሰግናለሁ። በክርስቶስ ላላችሁ ወንድሞቼና እህቶቼ ጓደኞቼም ሁሉ፤ ከልባችሁ በሆነ ፍቅር ለጸለያችሁልኝ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። የከፈላችሁትን መስዋእትነትና የፍቅራችሁን ልክ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡ እውነተኛ ስጦታዎች የሆኑልኝን የረዥም ዓመታት ጓደኞቼን ክሊፍ ማክአርድልንና ዴቪድ ጀንቷልስን አመስግናቸዋለሁ። በቀንም ይሁን በሌሊት፣ በተመቸም ባልተመቸም ጊዜ፣ ቀናም ይሁን ዋጋ መክፈል በሚያስፈልግበት ሁኔታ ውስጥ ሁልጊዜም ታማኝ ሆናችሁልኛል። ይህ መጽሐፍ እንዲጠናቀቅ ላደረጋችሁልኝ ማበረታታት ሁሉ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም፤ የባለቤቴ ወላጆች የሆኑት ኢልደንና ኢቴል ፔኒኮስት እንዲሁም የራሴ ወላጆች የሆኑት ራልፍና ቢሊ ፒፐር ለከፈሉት በዋጋ ለማይተመን መስዋእትነትና የታመነ ድጋፋቸው ወሰን የሌለው አክብሮቴን እገልጻለሁ። ለሦስቱ ልጆቼ ለኒኮል፣ ለክሪስና ለጆይ ... ማግኘት ከሚገባኝ በላይ እግዚአብሔር የሰጠኝ መልካም ልጆች ለማለት


እደፍራለሁ:: በእናንተ እጅጉን ተባርኬአለሁ:: ለእኔ እጅግ ዋጋ ላላችሁ ለእናንተ ይልቁን ደግሞ ከዚያች የቆየች ረቡዕ ሌሊት ወዲህ ስላሉት ጊዜያት አመሰግናለሁ ማለት ብቻ በቂ ይሆን? እንደገናም ደግሞ ለሠላሣ አመታት ያህል የትዳር ጓደኛዬ የሆንሽው ኢቫ፣ አንቺ ለእኔ ያደረግሽውን ያህል የትኛውም ሰው እንዳላደረገልኝ ልገልጽልሽ እወዳለሁ:: አንቺ ነገሮችን ሁሉ ያደረግሽልኝ በታማኝነት፣ በርህራሄና ያለምንም ማመንታት ነበር:: ከጓደኞቼና ከቤተሰቦቼ ሁሉ ይልቅ በእያንዳንዱ እለት ባለው ጉዞዬ ስቃዮ ምን ያህል ታላቅ እንደነበር በእውነት የምታውቀው ኢቫ ብቻ ነች፤ ምክንያቱም በቅርቤ ሆና ሁኔታዎችን በጽናት ተጋፍጣቸዋለችና ነው:: ኢቫ! አንቺ እኮ ከእግዚአብሔር የተሰጠሽኝ ስጦታ ነሽ::

ጌታ ሆይ፤ እኔ ሁልጊዜም የሆኑት ነገሮች በምን መንገድ እንደሆኑ እንደማላውቅ አንተ ታውቃለህ፤ ቢሆንም በአንተ መታመኔን አላቋርጥም:: አብ አባት ሆይ! በፍጹም የልብ ትህትና የምተርከው ታሪክ አንተን ደስ እንዲያሰኝህ ለብዙዎችም ባርኮት ይሆን ዘንድ እጸልያለሁ:: አሜን::

ዶን ፒፐር

የካቲት 2004





በ1982፣ ዶን ከመንትያ ልጆቹ ከክሪስ እና ከጆይ ጋር

## መቅድም

ጥር 18 1989 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየሁ:: የህክምና ባለሙያዎች የአደጋው ውጤት ምን እንደሆነ ለመናገር የፈጀባቸው የደቂቃዎች ጊዜ ብቻ ነው:: የልብ ምቴ ፈጽሞ ቆሞ ስለነበር እንደሞትኩ ተናገሩ:: በአንሶላ ሸፍነውኝ ስለነበር ሌሎች ቁስለኞችን ለመጎብኘት የሚመጡ ሁሉ አፍጥጠው ሊመለከቱኝ እድል አልነበራቸውም:: በአጠገቤ ሃኪምም ይሁን ማንም ሰው እንዳለ ፈጽሞ አላውቅም ነበር::

ከሞትኩ በኋላ ወዲያውኑ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማይ አመራሁ::

በመንግስተ ሰማይ በነበርኩበት ጊዜ፤ አንድ የመጥምቃውያን ሰባኪ አደጋው የፈጠረበት ሃዘን ውስጥ ሆኖ ወደ እኔ መጣ:: እንደሞትኩ ያወቀ ቢሆንም እንኳን ወደ ሙት አካሌ በፍጥነት መጥቶ ይጸልይልኝ ጀመር:: የድንገተኛ አደጋ የህክምና ባለሙያዎች በዙሪያው ሆነው ቢያላግጡበትም እርሱ ግን መጸለዩን ለማቆም አልፈለገም::

የህክምና ባለሙያዎቹ መሞቴን ከተናገሩ ቢያንስ ቢያንስ ከዘጠና ደቂቃ በኋላ እግዚአብሔር የዚያን ሰው ጸሎት መለሰ::

እንደገና ወደ ምድር ተመለስኩ::

እናም ታሪኬ እንዲህ ነው::



# 1 አደጋው

ስለዚህ በድፍረት "እግዚአብሔር ረዳቴ ነው አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?" ዕብ 13፥6

ብለን መናገር የምንችልበት ምክንያት ይ ነው::

በቴክሳስ የሚገኘው የመጥምቃውያን አጠቃላይ ጉባኤ፤ ዓመታዊ የሆነ አገር አቀፋዊ ስብሰባውን ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ነበር:: ጥር ወር 1989 በታላቁ ሀውስቶን አካባቢ የሚገኙ ከሁሉም የመጥምቃውያን አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ የመጥምቀውያን ጉባኤ ህብረት አባላት፤ ጉባኤው ከሊቪንግስተን ሃይቅ ዳርቻ በስተሰሜን በሚገኘው ትሪኒቲ ፒንስ በተባለው ታላቅ የጉባኤ አዳራሽ እንዲሆን መረጡ:: ጉባኤው ያተኮረው የቤተክርስቲያንን እድገት በሚመለከት ጉዳይ ላይ ነበር:: እኔም በዚያ የተገኘሁበት ምክንያት በወቅቱ አዲስ ቤተክርስቲያን ለመመስረት ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ የምገኝ በመሆኔ ነበር::

ጉባኤው የተጀመረው ሰኞ ዕለት ሲሆን እስከ ረቡዕ ድረስ እንዲቀጥል የታቀደለትም ነበር:: ማክሰኞ ምሽት የህብረቱ መሪና ወዳጅም ከሆኑት ጄ.ቪ. ቶማስ ጋር በመሆን ረዘም ያለ የእግር መንገድ አደረግን:: እርሳቸው የልብ ድካም ህመም ከያዛቸው ወዲህ የእግር ጉዞ

የሚያዘውትሩ ሆነው ነበር፡፡ ለዚህም ነበር የጉባኤውን የመጨረሻ ምሽት በእግር ጉዞ ለማሳለፍ የወሰንነው፡፡

ከወራት በፊት፤ አዲስ ቤተክርስቲያን መመሥረት እንደሚገባኝ ማሰብ ጀምሬ ነበር፡፡ ወደዚህ ታላቅ ሥራ ከመግባቴ በፊት ግን ማግኘት የሚገባኝን መረጃ ሁሉ ማግኘት ያስፈልገኝ ነበር፡፡ የጉባኤው ህብረት መሪዎች ሁሉ ጄ.ቪ. ቶማስ ስለ አዲስ ቤተክርስቲያን ምሥረታና እድገት የላቀ ተሞክሮና እውቀት እንዳላቸው እናውቃለን፡፡ በግዛታችን ውስጥ ስኬታማ የሆኑ በርካታ አብያተክርስቲናትን መስርተው ስለነበር ሕብዛኞቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ የተለየ ባለሙያ አድርገን እንቆጥራቸዋለን፡፡ በዚያ ምሽት አብረን በመጓዝ ላይ ሳለን እኔ ስለምመሠርታት አዲስ ቤተክርስቲያን እንጫወት ነበር፡፡ መቼ እንደምጀምራት፣ የት እንደምመሠርታት ሁሉ አወራን፡፡ ያለውን ውጣ ውረድና ሊደርስ የሚችለውን ችግር እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ለማወቅ እፈልግ ነበር፡፡ እርሳቸውም ማለቂያ የሌላቸው የሚመስሉ ጥያቄዎቼን ይመልሱና ፈጽሞ አስቤአቸው የማላውቅ ጉዳዮችን እያነሱ በዝርዝር ያጫውቱኝ ነበር፡፡

ለአንድ ሰዓት ያህል እየተጓዝን ብዙ ነገሮች አወራን፡፡ ምንም እንኳን ዝናባማና ብርዳማ ምሽት ቢሆንም የነበረን የአንድነት ጊዜ ድንቅ ነበር፡፡ ጄ.ቪም ያንን ጊዜ ደህና አድርገው ያስታውሱታል፡፡

እኔም ያችን ምሽት በፍጹም አልረሣትም፤ ይሁን እንጂ በተለየ ምክንያት ነው፡፡ ምናልባትም ያች ምሽት በትክክል መራመድ የቻልኩባት የመጨረሻዋ ምሽት ነበረች፡፡



በቀጣዩ ቀን ማለት ረቡዕ የአየሩ ሁኔታ እየባሰበት ሄደ፡፡ የማያቋርጥ ዝናብ መዝነብ ቀጠለ፡፡ የነበረው ቅዝቃዜ ከዚያ በላይ ጥቂት እንኳን ቢጨምር ፈጽሞ መጓዝ አንችልም ነበር፤ ምክንያቱም ሁሉም ነገር ወደ በረዶነት ይለወጥ ነበር፡፡

የማለዳው ስብሰባ በሰዓቱ ተጀመረ፡፡ የመጨረሻውን ንግግር አቅራቢ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ሰባኪ፣ አድርጎት የማያውቀውን እንግዳ ነገር አደረገ ንግግሩን በአጭር ቋጨው፡፡ በትሪኒቲ ፒንስ የሚገኙ ሠራተኞች ከምሣ ሰዓት በፊት በአራት ሰዓት ተኩል አካባቢ የምንቀማምሰውን ነገር አቀረቡልን፡፡ እናም ምሽቱ ከመቃረቡ በፊት ጓዜን ሁሉ የ1986 ሞዴል በሆነችው ቀይ ፎርድ መኪናዬ መጫኛ ላይ ቀረቀብኩ፡፡

ምግብ መመገባችንን እንዳበቃን ወዲያውኑ ወዳጆቼን ሁሉ ተሰናብቼ ወደ መኪናዬ ገባሁ፡፡ ጉዞዬም ወደመጣሁበት በአልቪን ወደሚገኘው ወደወከልኩት የሳውዝፓርክ መጥምቃውያን ቤተክርስቲያን በመጓዝ ከሁሰተን ማህበረሰብ ጋር ለመቀላቀል ነበር፡፡

በመኪናው ውስጥ ገብቼ ገና ሞተሩን እንደቀሰቀስኩ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ከሦስት ሣምንት በፊት መኪናዬን በማሽከርከር ላይ ሳለሁ የአደጋ መከላከያ ቀበቶዬን ባለማጥለቄ የትራፊክ ቅጣት ደረሰኝ ተቆርጦ ተሰጥቶኛል፡፡ በዚያ ጊዜ የጉሮሮ ቀዶ ህክምና ሊደረግለት በዝግጅት ላይ ለነበረ አንድ መጋቢ ጓደኛዬ ቃል ላካፍለው እየሄድኩ ነበር፡፡ የቴክሳስ ትራፊክ ያዘኝ፡፡ ደረሰኙ አጠገቤ ካለው ወንበር ላይ ተቀምጦ ስለነበር ወደአልቪን እንደተመለስኩ ቅጣቱን ወዲያውኑ መክፈል እንዳለብኝ አሳሰበኝ፡፡ የቅጣት ደረሰኙን ከመቀበሌ በፊት የአደጋ መጠበቂያ

ቀበቶውን የማጥለቅ ልምድ አልነበረኝም፤ ከዚያ በኋላ ግን መንገዴን በመቀየር ህጉን ማክበር ጀምሬአለሁ::

ያንን ደረሰኝ ባየሁት ጊዜ፤ "ዳግመኛ ትራፊክ እንዲያስቆመኝ አልፈልግም፤" ስል አሰብኩ:: በመሆኑም ቀበቶውን አጠላኩና ደህና አድርጌ አሰርኩት:: ይች ትንሽ ተግባር ታላቅ ውሳኔ ልትሆን ችላለች::

ወደ ሀውስተንና ወደ አልቪን ለመሄድ ሁለት አማራጭ መንገዶች አሉ:: የትሪኒቲ ፒንስን የጉባኤ አዳራሽ ዋንኛ በር አልፌ እንደወጣሁ፤ በሊቪንግስተን አቆራርጬ ቁልቁል ወደ ሃይዌይ 59 ወይም ደግሞ ብዙ ጊዜ ገልፍ ፍሪዌይ ተብሎ ወደሚጠራው ሁንትስቪል እና አይ - 45 በምሥራቅ አቅጣጫ መንዝ እንደነበረብኝ መምረጥ ነበረብኝ:: ሁለቱም ምርጫዎች ምናልባትም ርቀታቸው እኩል ይሆናል:: ወደ ትሪኒቲ ፒንስ በመጣሁባቸውና በተመለስኩባቸው ጊዜዎች ሁሉ ምርጫዬ በሃይዌይ 59 አቅጣጫ ማሽከርከር ነበር:: በዚያ ጠዋት ግን በገልፍ ፍሪዌይ አቅጣጫ ለመንዝ ወሰንኩ::

በጠዋት መንዝ እንድንችል አስቀድመው ስላለቀቁን እፎይታ ተሰምቶኝ ነበር:: አምስት ሰዓት ሲሆን የቀሩት ጥቂት ደቂቃዎች ነበሩ፤ በመሆኑም በስምንት ሰዓት አካባቢ ወደ ቤተክርስቲያኔ ተመልሼ መድረስ እችላለሁ ማለት ነው:: የቤተክርስቲያናችን ዋንኛው አገልጋይ አንድ ህብረት ለመምራት ወደ ቅድስቲቱ ከተማ ተጉዞ ነበር:: በመሆኑም በሳምንቱ አጋማሽ ላይ በሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን የነበረውን የአገልግሎት ሃላፊነት የጣለው በእኔ ላይ ነበር:: በቀጣዮቹ ሁለት ሣምንታትም በቤተክርስቲያን የስብከቱን አገልግሎት እንዳገለግል ጠይቆኛል:: በዚያ ማክሰኞ ምሽት ጥቂት ዝግጅት የሚጠይቅ የፀሎት



አገልግሎት ነበረን፤ እኔ ግን ለቀጣዩ ሰንበት የሚሆነውን ስብከት ማዘጋጀት ያስፈልገኝ ነበር::

አልቪንን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት ለመጀመሪያው ሳምንት የሚሆነኝን ስብከት ረቂቅ አዘጋጅቼ ነበር፤ የሰጠሁትም ርዕስ በታላቁ እግዚአብሔር እምናለሁ! የሚል ነው:: መኪናዬን በማሽከርክር ላይ እያለሁ ይህንኑ የስብከት ረቂቅ ጽሑፌን በጨረፍታ እየተመለከትኩ እስከ አሁን የሠራሁትን ለመገምገም አቀድኩ::

ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ በገልፍ ፍሪዌይ አቅጣጫ ለመንዝ የወሰንኩትን ውሳኔ ደጋግሜ ማሰላሰል ጀመርኩ:: አንዳንድ ጥቃቅን ውሣኔዎችን ስንወስን ምንም ያህል ትኩረት ሳንሰጥ የመሆኑ እውነት ያስደንቃል:: ያም ቢሆን እጅግ ትንሽ የሆነች ውሳኔአችን በቀጣዩ ሕይወታችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ውጤቶችን ያቀፈች እንደሆነች ራሴን ማሳሰቤን አልተውኩም::

ከትሪኒቲ ፒንስ ቅጥር ግቢ እንደወጣሁ በስተቀኝ በመታጠፍ በቴክሳስ ሃይዌ 19 አቅጣጫ ቁልቁል ተፈተለኩ:: በዚህ መንገድ ወደ ሁንትስቪል እንዳለሁ፤ ቀጥሎም አይ - 45ን አቋርጣለሁ፤ ከዚያም ወደ ሃውስተን ገባሁ ማለት ነው:: ሰው ሰራሽ ወደሆነው የትሪኒቲ ወንዝ ግድብ ለመድረስ ብዙ ማሽከርከር አልነበረብኝም:: አንድ ጊዜ የወንዝ ውሃ ይተኛበት የነበረው ያ ስፍራ እጅግ የሚያምር ሰፊ ሃይቅ ሆኗል:: ከውሃው ከፍታ በላይ የሊቪንግስተንን ሃይቅ አቋርጦ የሚያልፍ ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ ተዘርግቷል:: መንገዱ በግራና በቀኝ የመጠበቂያ ደርዝ ያልነበረው ከመሆኑም በላይ እጅግ ጠባብ ነው:: ወደሚቀጥለው የመንገድ ጫፍ እስከደርስ ድረስ በውሃው ላይ በተሠራው ጠባብ ጎዳና ላይ የግድ መንዝ ነበረብኝ:: በዚያ መንገድ ላይ ለማሽከርከር ፈቃድ

አልነበረኝም፤ ያም ቢሆን መንገዱ የግራና ቀኝ ደርዝ እንደሌለው አውቄአለሁ።

በሃይቁ ላይ የተዘረጋው መንገድ ሲያበቃ፤ በትሪኒቲ ወንዝ ላይ የተሠራው የቀድሞው ድልድይ ይገኛል። ከድልድዩ ቀጥሎ ደግሞ መንገድ እየጠበበ ይሄድና ሽቅብ የትሪኒቲን ወንዝ አሳብሮ ያልፋል። ጠባብ የሆኑት የመታጠፊያ ስላቾች ከሁለቱም አቅጣጫዎች የሚመጡ አሽከርካሪዎች አደጋ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ግልጽ አድርገው ያሣያሉ።

ያንን ድልድይ ስመለከት የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር፤ በሚያስገርም ሁኔታ ያለስፍራው የተቀመጠ ነበር። ስለተሠራበት ዘመን የማውቀው ነገር የለም ይሁን እንጂ ድልድዩ እጅግ ረዥም ነው። አሮጌ ከመሆኑም በላይ በግዙፍ የዛጉ ብረቶች የተገጣጠመ ነበር። ከፊት ለፊቱ ካለው አውራ ጎዳናና ከጥቂት ተሽከርካሪዎች በስተቀር ሌሎች መኪናዎችን ማየት አልቻልኩም። በጣም አደገኛ ድልድይ ነበር፤ በኋላ እንደሰማሁት በዚያ ድልድይ ላይ በርካታ አደጋዎች ተከስተዋል (በአሁኑ ጊዜ በጥቅም ላይ ባይውልም ድልድዩ በነበረበት ስፍራ አለ። መንግስት ከአጠገቡ ሌላ ተለዋጭ ድልድይ ሠርቷል)።

እጓዝ የነበረበት ፍጥነት በሰዓት ሃምሣ ማይል ነበር፤ ምክንያቱም ያ ስፍራ ለእኔ አዲስ ነው። በመኪናው ውስጥ ከነበረው ቅዝቃዜ የተነሣ ትካሻዎቼ ተቆራምደዋል። በዚያ ላይ ንፋሱ ደግሞ የጠዋቱን ቅዝቃዜ ይበልጥ እንዲጨምር ያደረገው ይመስላል። ሣያቋርጥ ይዘንብ የነበረው ዝናብ ወደ ውሽንፍርነት ተቀይሯል። ተመልሼ ወደ አልቪን የምደርስበትን ጊዜ እጅግ ናፈቅሁ። ድልድዮን አቋርጬ ከመውጣቴ በፊት አምስት ሰዓት ከአርባ አምስት አካባቢ፤



የቴክሣስ ጠባይ ማረሚያ እስረኛ በሆነ ከእስር ቤቱ ውጭ መኪና ለመንዳት በጎ ፈቃደኛ ሆኖ በተገኘ እስረኛ ሰው ይሽከረከር የነበረ፤ ባለ 18 ጎማ ከባድ መኪና በአውራ ጎዳናው መካከል እየተጠማዘዘ መጥቶ መኪናዬን ፊት ለፊት ገጫት። መኪናዬም በድልድዩና በከባድ መኪናው መካከል እንደ ሳንድዊች ሆነች። እነኛ ሁሉ ጐማዎች በመኪናዬ ላይ ተከመሩና ጨፈላለቋት። የማስታውሰው የአደጋውን ከፊል ሁኔታ ብቻ ነው፤ አብዛኛውን መረጃ ያገኘሁት ግን በኋላ ከአደጋው ዘገባና በስፍራው ከነበሩ ሰዎች ነው።

የአይን ምስክር ከሆኑ ሰዎች እንደደረሰኝ ገለጻ፤ ያ ከባድ መኪና ወደ ሌላው የጎዳናው አቅጣጫ ተጠማዞ ወደ ጠባቡ የድልድዩ ወገን በማምራት ሁለት መኪናዎችን ጠርጎ ከድልድዮ ላይ አፈናጥሮ ጥሏቸዋል። እነዚህ መኪናዎች ከከባድ መኪናው ፊት ፊት ይጓዙ የነበሩና በተቃራኒ አቅጣጫ እኔን አልፈውኝ የሄዱ መኪናዎች ነበሩ። የፖሊስ ዘገባ እንደገለጸው ከሆነ ከባድ መኪናው መኪናዬን በገጨበት ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ ስድሣ ማይል በሰዓት በመጓዝ በፍጥነት የሚሽከረከር ነበር። ልምድ ያልነበረው አሽከርካሪ በመጨረሻው በድልድዩ ማብቂያ አካባቢ መኪናውን ሊያቆመው ችሏል።

ግጭት ከደረሰባቸው ሁለት መኪናዎች በአንደኛው ውስጥ አንድ ወጣት ቬትናማዊ የነበረ ሲሆን በሁለተኛው መኪና ውስጥ ደግሞ አንድ እድሜ የጠገቡ የካሁሳ ተወላጅ ነበሩበት። ምንም እንኳን በግጭቱ ታላቅ ድንጋጤ የደረሰባቸው ቢሆንም ያገኛቸው መጠነኛ የሆነ የመቁሰልና የሰውነት መላጥ ጉዳት ብቻ ነበር። እርዳታ ማግኘት ባለመፈለጋቸው የህክምና ሰዎች ሁለቱንም ወደ ሆስፒታል አልወሰዷቸውም።

በከባድ መኪናው ፍጥነት ምክንያት የአደጋው ውጤት አንድ መቶ አስር ማይል በሰዓት እንደነበር የአደጋው ሪፖርት ይዘግባል። ይህም ከባድ መኪናው መኪናዋን ሲገጭ ይሽከረከርበት የነበረው የስድሣ ማይል በሰዓት ፍጥነት፣ እኔ በዝግታ አሽከረክርበት ከነበረው የሃምሳ ማይልስ ፍጥነት በሰዓት ተደምሮ ነው። እስረኛው መኪናውንና የመኪናውን ፍጥነት መቆጣጠር ባለመቻል ክስ ተመሠረተበት። በኋላ ላይ የተገኙ መረጃዎች እንደጠቆሙት እሥረኛው ያንን ከባድ መኪና ለማሽከርከር የመንጃ ፈቃድ አልነበረውም። በእስር ቤቱ ውስጥ ተቆጣጣሪው በዚያ ከባድ መኪና ምግብ ወደ እሥር ቤቱ ለማምጣት ፈቃደኞች እንዳሉ ጠይቆ ነበር። የተገኘው ብቸኛ ፈቃደኛ እርሱ በመሆኑ ያንን መኪና እንዲነዳው ይፈቅዱለታል። ሌሎች ሁለት ዘቦች ደግሞ የመንግስት በሆነች አንድ ፒክ አፕ መኪና በቅርብ ርቀት ይከተሉት ነበር።

ከአደጋው በኋላ፣ የከባድ መኪናው አሽከርካሪ አንድም ጭረት እንኳን በሰውነቱ ላይ አልተገኘም። የወህኒ ቤቱ ከባድ መኪና ብቻ ጥቂት ጉዳት አጋጥሞታል። ይሁን እንጂ ያ ግዙፍ መኪና የኔን ፎርድ ጨፈላልቆ ከጠባቡ መንገድ ገፍቶ አውጥቷታል። ወደ ሃይቁ ከመወርወር ያዳናት የድልድዮ ድጋፍ ብቻ ነበር።

በስፍራው የነበሩ የዐይን እማኞች እንደተናገሩት ከሆነ፣ በፒካፕ መኪናዋ ውስጥ የነበሩ ዘቦች ወደ እስር ቤቱ በመደወል የህክምና እርዳታ በመጠየቃቸው ባለሙያዎቹ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደረሱ። አንድ ሰው ምርመራውን አደረገልኝ፣ የልብ ምቴ ፈጽሞ ቆሟል፣ በመሆኑም አደጋው በተፈጸመበት ቅጽበት እንደተገደልኩ አስታወቀ።



ከዚያ በኋላ ስለተፈጸመው ነገርም ይሁን ስለአደጋው ውጤት የማስታውሰው ነገር አልነበረም።

እጅግ ሃያል በሆነች በአንዲት ሰከንድ ሞትኩ።

# 2

# የመንግስተ ሰማይ ቆይታዬ

ፈራ እንዲህም አለ፤ "ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራል፤ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህም የእግዚአብሔር ደጅ ነው።" ዘፍ 28 ፥ 17

በሞትኩ ጊዜ፤ እረጅምና ጥቁር በሆነ ዋሻ ውስጥ እየተንሳፈፍኩ አልሄድኩም። የመነጠቅም ይሁን ወደ ምድር የመመለስ ስሜት አልተሰማኝም። አካሌ ወደ ብርሃንነት እየተለወጠ እንዳለም አልተሰማኝም። እኔን የሚጠራ ወይም ሌላ ድምጽ በጭራሽ አልሰማሁም። የመጨረሻው ትውስታዬ ከሆነው ከድልድዩና ከዝናቡ እይታዬ በኋላ ወዲያውኑ፤ ከቶውን ምድራዊ ቃል ሊገልጸው በማይችል አንጸባራቂ ብርሃን ውስጥ ተጠቀለልኩ። የማውቀው ያንን ብቻ ነው።

ቀጥሎ ያወቅኩት ነገር ቢኖር፤ በመንግስተ ሰማይ ውስጥ መቆሜን ነበር።

ዙሪያዬን ስመለከት ደስታ በውስጤ መፍሰስ ጀመረ፤ በዚያው ቅጽበት ደግሞ በአካባቢዬ እጅግ በርካታ ሰዎች እንደነበሩ ተረዳሁ። አንጸባራቂና ድንቀኛ ውበት ባለው መግቢያ በር ላይ ቆመዋል። ከእኔ ምን ያህል ርቀት እንደነበራቸው አላውቅም፤ በዚያ ርቀትን የመሳሰሉ



ነገሮች ዋጋ ያላቸው አይደሉም። ሰዎቹ ወደአለሁበት ሥፍራ እየተመሙ በመጡ ጊዜ፤ ኢየሱስን አላየሁትም ነበር። ነገር ግን የማውቃቸውን ሰዎች አይቻለሁ። በዚያው ቅጽበት አንድ ነገር ተገነዘብኩ፤ እነዚያ ሁሉ ሰዎች የሞቱት እኔ በኖርኩባቸው የሕይወት ዓመታት ውስጥ ነው። ሁኔታቸው ሁሉ ልክ ፍጹም ፍጥረታዊ ሰዎችን ይመስላል።

ወደ እኔ እየፈጠኑ መጡ፤ እያንዳንዳቸው ፈገግ ይሉ፤ ይጮኹና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። ማንም ሰው እንዲህ ነው ብሎ ባይነግረኝም እንኳን እኔን በክብር ለመቀበል የመጡ የእንግዳ ተቀባይ ቡድኖች መሆናቸውን ተረዳሁ። ነገሩ ሁሉ ሁሉም ከመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ ሆነው እኔን እየተጠባበቁኝ እንደነበር ይመስላል።

በደንብ ያስታወስኩት የመጀመሪያው ሰው አያቴ ጆ ኩልቢዝን ነበር። ልክ ያን ጊዜ የማውቀውን ነው የሚመስለው፤ ሽበቶ ፀጉሩና "ትልቅ ሙዝ ይመስላል እለው የነበረ" አፍንጫው ሁሉ እንዳለ ነው። ለቅጽበት ያህል ቆም አለና በአፍታ ደግሞ በፊት ለፊቴ ቆመ። ፊቱ በፈገግታ ተሞልቷል። ስሙን የጠራሁት ይመስለኛል፤ እርግጠኛ ግን አይደለሁም።

"ዶኒ!" አለና ጮኸ (አያቴ ሁልጊዜም የሚጠራኝ እንዲህ ነበር)። አይኖቹ መብራት ጀመሩ፤ አጠገቤ በደረሰባት የመጨረሻ እርምጃውም እጆቹን ወደ እኔ ዘረጋ። በእቅፉ ውስጥ አስገብቶ ጀርባዬን በእጆቹ እየጠበጠበ ያጽናናኝ ጀመር። ልክ በልጅነቴ ዓመታት እንደማውቀው ግዙፍና ጠንካራ አያቴ አሁን ደግሞ እንደቀድሞው ሆኖ አየዋለሁ።

በቤታችን ውስጥ በልብ ድካም ህመም በመሰቃየት ላይ ባለበት ሰዓት ከእርሱ ጋር ነበርኩ፤ በአምቡላንስ ውስጥ ሆኜ አብሬው ሄጃለሁ:: ዶክተሩ ወደ እኔ እየተራመደ መጥቶ ከፊት ለፊቴ ሲቆም በድንገተኛ አደጋ የህክምና ክፍል በር ላይ ቆሜ ነበር:: ራሱን በሃዘኔታ እያወዛወዘ፤ ማድረግ የምንችለውን ነገር ሁሉ አድርገን ነበር አለ ልስልስ ባለ ድምጽ::

አያቴ ለቀቀኝ፤ አሻቅቤ ፊቱን ስመለከት ወሰን በሌለው ደስታ ተሞላሁ:: ስለ ልብ ድካም በሽታውም ይሁን ስለ ሞቱ አላሰብኩም፤ ምክንያቱም እንደገና የመገናኘታችንን ደስታ ገና አልጠገብኩትም ነበር:: ሁለታችንም በገነት የመገኘታችንም ጉዳይ ትኩረት የሰጠነው ነገር አልነበረም::

በመጀመሪያ ያየሁት ሰው ለምን አያቴ ሲሆን እንደ ቻለ ምክንያቱን አላውቅም:: ምናልባትም እርሱ በሞተበት ጊዜ አጠገቡ የነበርኩት ሰው እኔ ስለነበርኩ ይሆናል:: እርሱ ምንም እንኳን ሕይወቴ በቀና መንገድ እንዲመራ አስተዋጽኦ የነበረው ሰው ቢሆንም፤ ሕይወቴን በመንፈሳዊ አቅጣጫ ከመሩት ትልቅ ሚና ከነበራቸው መካከል አንዱ አይደለም::

በአያቴ እቅፍ ውስጥ ከተጽናናሁ በኋላ ቀጣዩ ሁለተኛው ወይም ሦስተኛ ሰው ማን እንደነበረ አላስታውስም:: ህዝቡ በዙሪያዬ ከበቡኝ:: አንዳንዶቹ ያቅፉኛል፣ ሌሎች ደግሞ ጉንጬን ይስሙኛል፤ እጆቼን ይጨብጣሉ:: ከዚያ ጊዜ በፊት እንደዚያ የመወደድ ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም::

እኔን ለመቀበል ከመጡት ሰዎች መካከል አንዱ፤ የልጅነት ጓደኛዬ የነበረው ሚክውድ ነበር:: ሚክ ለእኔ የተለየ ሰው ነበር፤



ምክንያቱም ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የጋበዘኝና ክርስቲያን እንድሆን ትልቁን አስተዋፅኦ ያደረገው እርሱ ነው:: ከማውቃቸው ክርስቲያኖች ሁሉ ሚክ ለእምነቱ ፈጽሞ የተሰጠ ወጣት ክርስቲያን ነበር:: ዝነኛና በእግር ኳስ፣ በቅርጫት ኳስ፣ በሩጫና በሜዳ ላይ በሚደረጉ ውድድሮችም ለአራት ዓመታት ኮከብ የነበረ ልጅ ነው:: በተጨማሪም ለእኔ እንደ ሞዴል የሆነልኝም ልጅ ነበር፤ ምክንያቱም የሚናገረውን ቀክርስትና ሕይወት ሲኖረው ተመልክቻለሁ:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ሚክ በሉሲያና ግዛት ዩኒቨርስቲ ውስጥ የሙሉ ነፃ ትምህርት ዕድል አገኘ:: ዕድሜው አስራ ዘጠኝ በደረሰ ጊዜም ሚክ በመኪና አደጋ ተገደለ:: የሞቱን ዜና በሰማሁ ጊዜ ልቤ በሀዘን ተሰብሮ ነበር፤ ያንን ሃዘን ለመርሳትም የወሰደብኝ ብዙ ጊዜ ነበር:: በሕይወቴ ውስጥ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ከደረሰብኝ ሃዘን ሁሉ የእርሱ ሞት እጅግ አስደንጋጩና የመረረው ሃዘኔ ነበር::

በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ በተገኘሁበት ጊዜ ማልቀስ አቁሜ ከሆነ ይገርመኛል:: እግዚአብሔር እንደዚያ ያለውን ደቀመዝሙር ለምን እንደወሰደው አልገባኝም:: ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት መሪር ሃዘኑንና መለያየታችንን ለመርሳት አልቻልኩም ነበር:: ሁልጊዜም አስታውሰዋለሁ ማለት አይደለም፤ ባስታወስኩት ጊዜ ግን ንዴቴ ይመጣል::

አሁን ሚክን በመንግስተሰማይ አየሁት:: በክንዶቹ አቅፎ ጀርባዬን በእጆቹ ሲጠበጥብ ስቃዮና ሃዘኔ ጥሎኝ ሄደ:: እንደዚያ ባለ ብሩህ ፈገግታ ውስጥ ሚኪን አይቼው አላውቅም:: እስካሁንም ምክንያቱ ባይገባኝም እንኳን በአካባቢው የተፈጠረው ደስታ ጥያቄን ሁሉ የሚያስረሳ ነው:: ሁሉም ነገር የተባረከና ፍጹም ነው::

ብዙ ሰዎች ወደ እኔ እየመጡ በስሜ ይጠሩኝ ጀመር:: በመንግስተ ሰማይ ሊቀበሉኝ በመጡ ሰዎች ብዛት ትልቅ ደስታ ተሰማኝ:: ቁጥራቸው ብዙ ነበር፤ በፊታቸው ላይ የማየውን ደስታ ያህል ማንም ሰው ተደስቶ እንደሚያውቅ አልገምትም:: ሁሉም ሕይወት የሞላባቸውና ፍልቅ ደስታ የሚነበብባቸው ነበሩ::

በዚያ ጊዜ ትርጉም አልነበረውም:: ይሁን እንጂ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ይህንን የመንግስተ ሰማይ ልምምዴን ከጊዜ ጋር እንዲገናዘብ አድርጌዋለሁ::

እንደገናም ቅድመ አያቴን አየሁት፤ ድምጹንም ሰማሁ:: እነርሱን ለመቀላቀል በዚያ በመገኘቴም የተሰማውን ደስታ ገለጸልኝ:: በትምህርት ቤት የክፍል ጓደኛዬ የነበረውንና በኋላም በሃይቅ ውስጥ ሰጥሞ የሞተውን ቤሪ ዊልሰንን አየሁት:: ቤሪ አቀፈኝ፤ በፊቱ ላይ በማየው ፈገግታ ውስጥ የሚንጸባረቀው ደስታ መገመት ከምችለው በላይ ነበር:: እርሱና ሌሎቹም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ የሚከተሉኝ ሁሉ እኔን በማየታቸውና በመንግስተ ሰማይ ሊቃበሉኝ በመምጣታቸውና አብረን ሕብረት በማድረጋችንም የተሰማቸውን ደስታ ሁሉ ገለጹልኝ::

ከዚያ በኋላ ደግሞ፤ ይወዱኝ የነበሩና ብዙ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ያጫውቱኝ የነበሩ አስተማሪዎቼን አየኋቸው:: በመካከላቸው በማለፍ ላይ ሳለሁ በእድሜያቸው መካከል የነበረውን ሰፊ ልዩነት አስተዋልኩ:: በእድሜ የሸመገሉና ወጣቶች፤ በእነርሱም መካከል ያሉ በሁሉም ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ነበሩ:: አብዛኞቹ በምድር በኖሩበት ዘመን አይተዋወቁም፤ ይሁን እንጂ ሁሉም ቢሆን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በሕይወቴ ላይ በጎ ተጽእኖ የነበራቸው ሰዎች ናቸው:: ምንም እንኳን



በምድር ላይ እርስ በእርሳቸው የማይተዋወቁ ቢሆኑም፤ አሁን በዚያ የሚተዋወቁ ይመስላሉ::

ይህንን ለመግለጽ ስሞክር፤ ቃላቶቼ የደከሙና ብቃት የሌላቸው ይሆኑብኛል፤ ምክንያቱም ትርጉም ሊሰጠው የማይችል ደስታን፣ ዝሴትን፣ መጽናናትንና ሙሉ ፍስሃን ለመግለጽ ምድራዊ ቋንቋ መጠቀም ግድ ስለሚሆንብን ነው:: ሁሉም ያለማቋረጥ ያጽናኑኝ፣ ይደባብሱኝ፣ ያናግሩኝ ያሳስቁኝና እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር:: ይህ ስረዥም ጊዜ የቀጠለ የሚመስል ነበር፤ ይሁን እንጂ በፍጹም አልደከመኝም ነበር::

አባቴ፤ ወላጆቹ ከወለዷቸው አሥራ አንድ ልጆች መካከል አንዱ ነበር:: አንዳንዶቹ ወንድሞቹና እህቶቹ አሥራ ሦስት የሚደርስ ቁጥር ያላቸው ልጆችን ወልደዋል:: ገና ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ቤተሰቡ ብአንድነት ለመሰብሰብ ብዛት ያለው ከመሆኑ የተነሣ በአርካንሰስ ሞንትሴሎ ከተማ የሚገኘውን ሙሉውን የመዝናኛ ሥፍራ እኛው እንከራየው ነበር:: እኛ የፒፐርስ ቤተሰቦች እርስ በእርስ የምንዋደድ ስለነበርን በተገናኘን ጊዜ ሁሉ እንተቃቀፋለን፤ እንሳሳማለን:: ይሁን እንጂ በምድር ላይ የነበረው ያ የቤተሰብ የአንድነት ጊዜ በዚህ በመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ ካጋጠመኝ የቅዱሳን ጉባኤ ጋር ፈጽሞ ሊመሳሰል የሚችል አልነበረም::

በዚያ በሞንትሴሎ ይሰበሰቡ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ አሁን ደግሞ በዚህ በመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸዋለሁ:: መንግስተሰማይ ብዙ ነገር ናት፤ ይሁን እንጂ ያለጥርጥር ከሁሉም ይልቅ የቤተሰቦች እንደገና የመገናኛ ሥፍራ ናት::

እዚያ እየሆነ ያለው ሁኔታ ሁሉ በአዕምሮ ውስጥ ትልቅ ትውስታን የሚያሠርጽ ነው። እንደዚያ ያለ ታላቅ መጽናናት ተሰምቶኝም ይሁን በእንደዚያ ያለ ውበት አይኖቼ ተስበው የሚያውቁበት ጊዜ የለም። የመንግስተ ሰማያዊ ብርሃንና ውበት ምድራዊ እይታንም ይሁን ገለጻን እልፎ የሚሄድ ነው። ሙቀትና አንጸባራቂ ብርሃን ከቦኛል። አካባቢዬን ስቃኝ አንጸባራቂውንና እጅግ የተዋቡ ቀለማት ያሉትን የደመና ቁልል ማየት ውበቱ መገመት ከምችለው በላይ ነው። የማየው የቀለማት አይነትና የነገሮች ውበት ከዚያ በፊት ያየኋቸውን ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ የሚያስንቅ ነበር።

የስሜት ህዋሳቶቼ ሁሉ ንቁና የተጉ ቢሆኑም ቅሉ፤ ከዚህ በፊት ማንኛውም ነገር እንዲህ ፍጹም ወደ እውነት ቀርቦ አይቼም ሆነ ሰምቼ እንደማላውቅ ተሰማኝ። ምንም ነገር መቅመሴን አላስታውስም፤ ይሁን እንጂ ብቀምስ ኖሮ እርሱም በምድር ላይ ከተመገብኳቸው ወይም ከጠጣኋቸው ነገሮች ሁሉ የበለጠ ሞገስ ያለው ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ። ይህንን ነገር መግለጽ የምችልበት በጣም የተሻለው መንገድ፤ በተለየ ሁኔታና አቅጣጫ ውስጥ እንደሆንኩ ይሰማኛል፤ ብሎ መናገር ይመስለኛል። በምድር ላይ እጅግ ደስተኛ በሆንኩበት ሁኔታ ውስጥ እንኳን እንዲህ ሙሉ የሆነ ሕይወት በጭራሽ ተሰምቶኝ አያውቅም። በእነዚያ በተወደዱ ሰዎች ፊት ለፊት በዝምታ ቆሜአለሁ፤ አሁንም ሁሉንም ነገር ለመረዳት እየሞከርኩ ነበር። አሁንም አሁንም ደጋግሜ የምሰማው ነገር እኔን በማየታቸው ምን ያህል እንደተደሰቱና በመካከላቸውም በመሆኔ የተሰማቸውን ሃሴት የሚገልጹበትን ቃላት ነበር። ቃላቶቹን ይናገሯቸው ወይም አይናገሯቸው እርግጠኛ አይደለሁም፤ ይሁን እንጂ መምጣቴን ተዘጋጅተው ይጠብቁ እንደነበር



አውቄአለሁ። በተጨማሪም ደግሞ በመንግስተ ሰማይ ጊዜ እያለፈ የማይሄድ መሆኑን አውቄአለሁ።

የሰዎቹን ፊት ትክ ብዬ እንደገና ስመለከት፤ በምድር ላይ ክርስቲያን እንድሆን አስተዋጽኦ አድርገው የነበሩ ወይም እንደ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቴ እንዳድግ ያበረታቱኝ ሰዎች መሆናቸውን ተገነዘብኩ። እያንዳንዳቸው አዎንታዊ በሆነ መልኩ በሕይወቴ ላይ ተጽእኖ ነበራቸው። እያንዳንዳቸው በሆነ መንገድ የተሻለ ደቀመዝሙር እንድሆን መንፈሳዊ አስተዋጽኦዋቸውን አበርክተዋል። ያንን መረጃ እንዴት እንዳገኘሁት ባልገነዘበውም እንኳን፤ እንደገና ደግሞ አንድ ነገር አውቄአለሁ፤ ከእርሱ ጋር በመንግስተ ሰማይ እሆን ዘንድ የቻልኩት በእነርሱ ምክንያት ነው።

ለእኔ አድርገውት ስለነበረው ነገር አልተጨዋወትንም። ነገራችን ሁሉ ያጠነጠነው የእኔ በዚያ መገኘት የፈጠረው ደስታና እኔን በማየታቸው ስለተሰማቸው ሃሴት ነው።

በዚያው የተሟሟቀ ሁኔታ ውስጥ እንደነበርን ላቀረቡልኝ የአቀባበል መልካም ቃላት እንዴት መልስ እንደምሰጥ አላወቅኩም ነበር። ከእናንተ ጋር መሆን በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ አልኳቸው። እነኝህም ቃላት ቢሆኑ በምወዳቸው በእነዚያ ሰዎች መካከል መሆኔና በመጽናናቴ በውስጤ የሚፈሰውን ደስታ የሚገልጡ አልነበሩም።

ወደ ኋላዬ ትቼው ስለመጣሁት ነገር ሁሉ ምንም አላስታውስም፤ ቤተሰቦቼንም ይሁን የነበረኝን ንብረት ትቼ በመምጣቴ አንዳች ቅሬታ አልተሰማኝም። እግዚአብሔር አስጨናቂ የሆኑና አሉታዊ ነገሮችን ሁሉ ከአዕምሮዬ ውስጥ የጠረጋቸው ይመስላል፤ ማድረግ የቻልኩት አንድ

ነገር ከእነዚህ አስደሳች ሰዎች ጋር በአንድ ላይ በመሆኑ ወሰን የሌለው ደስታ መፈንጠዝ ነበር።

አንድ ጊዜ እንደማውቃቸው እንደነበሩ ሆነው ነው አሁን ያሉት። ልዩነቱ በምድር ላይ ከነበሩበት ከማናቸውም ጊዜ ይልቅ አሁን የሚያንጸባርቁና በደስታ የተሞሉ መሆናቸው ነው።

ቅድመ አያቴ የሆነችው ሃቲ ማነን ዘሯ ከአሜሪካ ጥንታዊ ነዋሪዎች መካከል ነው። በልጅነቴ እርሷን የያኋት በአጥንት ህመም በሽታ ከተያዘች በኋላ ነበር። ጭንቅላቷና ትከሻዋ ወደ ፊት አዘንብለው ነበር። ይህም ክብ ሊሆን ምንም ያህል ያልቀረው የጎበጠ አይታ ሰጥቷት ነበር። በጣም የማስታውሳት ደግሞ ፊቷ በጣም የተጨማደደ በመሆኗ ነው። ስለ እርሷ በነበረኝ ትውስታዬ ሌላው የማልረሳው ነገር ጥርሶቿ አርቴፊሻል መሆናቸውን ነው። ብዙ ጊዜ ግን አታደርጋቸውም ነበር። በመንግስተ ሰማይ በተገናኘን ጊዜ ግን ፈገግታዋን ስትለግሰኝ ጥርሶቿ ያንጸባርቁ ነበር። እነኝህ ጥርሶች አርቴፊሻል ሳይሆኑ የራሷ ጥርሶች እንደሆኑ አውቄአለሁ፤ ፈገግ ስትል ካየኋቸው ፈገግታዎች ሁሉ ውበት ያለው ፈገግታ ነው።

እንደገና ደግሞ አንድ ነገር አስተዋልኩ አሁን እንደ ጥንቱ ጎባጣ አልነበረችም። ጠንካራና ቀጥ ብላ የቆመች ነች፤ ፊቷን ያጨማደዱት እነዚያ የሕይወት መስመሮች ሁሉ ሙልጭ ብለው ጠፍተዋል። በምን ያህል ዕድሜ ላይ እንደሆነች አላውቅም፤ ስለዚህ ነገር ለማሰብም እንኳን አልፈልግም። የሚያንጸባርቅ ፊቷን ትክ ብዬ ስመለከት በመንግስተ ሰማይ የዕድሜ ጉዳይ ዋጋ ያለው ነገር እንዳልሆነ ተገነዘብኩ።

ዕድሜ የሚገልጸው የጊዜን እያለፈ መሄድ ነው፤ በዚያ ደግሞ ጊዜ የሚባል ነገር የለም። በዚያ ያገኘኋቸው ሰዎች ሁሉ ልክ ለመጨረሻ



ጊዜ ባየኋቸው ዕድሜ ላይ ነው የሚገኙት-ልዩነቱ በምድር ላይ ያሳለፉት ሕይወት ያሳደረባቸው ከፉ የሕይወት ጠባሳ ፈጽሞ ተጠርጎ መወሰዱ ነው። በምድር ላይ ምንም እንኳን አንዳንዶቹ የለውነት ገጽታቸው ውበት ያልነበረው ቢሆንም በመንግስተ ሰማይ ግን ሁሉም ነገር አትኩረው ሲመለከቱት የሚያጓጓ ፍጹም የሆነ፣ ውበትን የተጎናጸፈና አስደናቂ ነው።

እነሆ ብዙ ዓመት ካለፈ በኋላ አሁን እንኳን፤ አንዳንድ ጊዜ አይኖቼን ጨፍኜ፤ ከአየኋቸው የለው የፊት ገጽታዎች ሁሉ ፍጹምነት ባለው አቻ በማይገኝለት ፈገግታ ወንድማዊ የፍቅር ግለት ተሞልተው ያስደነቁኝን እነኛን ፊቶች ለማየት እችላለሁ። ከእነርሱ ጋር አብሮ መሆን በራሱ የተቀደሰ ጊዜና ታላቅ ግምት በሚሰጠው ተስፋ ውስጥ እንደመቆየት ማለት ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ መንግስተ ሰማይን ስረግጥ፣ አስቀድሞም ከፊት ለፊቴ ነበሩ፤ ደግሞም እየፈጠኑ ወደ እኔ ይመጡ ነበር። ሁሉም የማጽናናትን ቃል ይናገሩኛል፤ በየትኛውም አቅጣጫ ልመልከት አንድ ጊዜ ይወደኝና እኔም እወደው የነበረውን ሰው እመለከታለሁ። በዙሪያዬ ከበውኝ ይዞሩ ስለነበሩ እያንዳንዳቸው ወደ መንግስተ ሰማይ እንኳን ደህና መጣህ ሊሉኝ ሰፊ እድል ነበራቸው።

የተወደድሁ እንደሆንኩ ተሰማኝ በኖርኩባቸው ዘመናት ከተወደድኩት በላይ እንደተወደድኩ ተሰማኝ። ይናገሩኝ የነበሩትን ቃላት አሁን አላስታውስም። ወደ እኔ አተኩረው ሲመለከቱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ፤ ፍጹም ፍቅር ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አወቅሁ። እኔን ከከበቡኝ ሰዎች ሁሉ ፊት ላይ የሚንጸባረቀው ይሄው ነበር።

ወደ እነርሱ አተኩሬ ተመለከትኩ፤ እንዲህ ባደረኩ ጊዜ ደግሞ በእነርሱ ውስጥ የነበረ ፍቅር ወደ እኔ የሚሰርጽ ይመስለኝ ነበር። ቀና ብዬ በዙሪያዬ ያለውን ሁሉ ቃኘሁት፤ ባየሁት ነገር ሁሉ ፈጽሞ ተማረኩ። በዚያ ያለው እያንዳንዱ ነገር ብሩህ ገጽታ ነበረው። ከመግቢያው በር ወጥተው ጥቂት እልፍ እንዳሉ፤ አሁን ከቦን ካለው ብርሃን ይልቅ የደመቀ ንጻት ያለው ውብ ብርሃን ሙሉ በሙሉ ይንጸባረቃል። የሰዎቹን ፊት አተኩሬ መመልከቴን ባቆምኩ ጊዜ፤ በአካባቢዬ ያለው ሁሉ አስገራሚ በሆነ ደማቅ ብርሃን የሚንቆጠቆጥ እንደሆነ ተገነዘብኩ። በዚያ የነበረውን ሁኔታ ለመዘገብ፤ ቃላት ፈጽሞ አቅም የላቸውም፤ ምክንያቱም ሰውኛ የሆኑ ቃላት የነበርኩበት ሁኔታ የፈጠረብኝን የአግራሞትና የመደነቅ ስሜት ሊገልጹት አይቻላቸውም።

እመለከተው የነበረ ማንኛውም ነገር አንጸባራቂ የሆነ ብርሃን ያመነጫል። ደህና አድርጌ ልገልጸው የምችለው ነገር ወደዚያ ብርሃን እየቀረብን መሄዳችንን ነው። ማንም ሰው እንደዚያ ለማድረግ ጊዜው እንደሆነ አልተናገረንም፤ ይሁን እንጂ ሁላችንም በአንድ ጊዜ ወደፊት መሄድ ጀመርን የእያንዳንዱ ነገር አንጸባራቂነት እየጨመረ ይሄዳል። ነገሩ ሁሉ ልክ ወደ አንድ ተራራ እየቀረብን በሄድን መጠን ግዝፈቱ እየጨመረ እየጨመረ እንደሚሄደው አይነት ነው። በሩን አልፈን በገባን ጊዜ የሆነ ጨለማ ነገር እያለሁ ብዬ ገምቼ ነበር፤ ነገር ግን ማየት የምችለውን ያህል አርቄ በተመለከትኩ ጊዜ ሌላ ነገር አልተመለከትኩም ነገር ግን ያየሁት ነገር ቢኖር ብሩህና አንጸባራቂ ብርሃን ብቻ ነው።

በንጽጽር ሲታይ፤ ከመግቢያው በር ላይ ወዳጆቼንና ጓደኞቼን ባገኘሁበት ሥፍራ ያየሁት ታላቅ ብርሃን፤ ከፊት ለፊቴ ካለው እየጨመረ ከሚሄደው አንጸባራቂ ብርሃን ጋር ሲነጻጸር እንደ ጨለማ



የሚቆጠር ነው። የምራመደው እያንዳንዱ እርምጃዬ የብርሃኑን ነጸብራቅ እየጨመረ እንዲሄድ የሚያደርገው ይመስላል። ብርሃኑ እንዴት እየጨመረ እንደሚሄድ አላውቅም ነበር፤ የሆነው ግን እንደዚያ ነው። ነገሩ ሁሉ የጨለማውን ክፍል በር ሰብሮ በመውጣት በእኩለ ቀን ብርሃን ውስጥ እንደመራመድ ይቆጠራል። በሩ ተበርግዶ በተከፈተ ጊዜ፤ እንደባረቂ በሆነ የፀሐይ ብርሃን ሙላት እንከበባለን፤ ለቅጽበት ያህልም ማየት አንችልም።

በርግጥ ማየት የማልችል አልሆንኩም፤ የብርሃኑ ድምቀትና ውበት እየጨመረ በመሄዱ ግን አገረም ነበር። ሁሉም ነገር እንግዳ ነገር ይመስላል፤ የሚታየው ነገር ሁሉም ያንጸባርቃል፤ ወደፊት በተራመድኩበት በእያንዳንዱ ቅጽበት አስገራሚው ውበት እየጨመረ ይሄዳል። ርቄ በሄድኩ መጠን ብርሃኑ ይደምቃል። ብርሃኑም አጥለቅልቆኛል፤ ወደ እግዚአብሔር መገኛ እየቀረብኩ እንደመጣሁ ይሰማኝ ጀመር። ምንም እንኳን ምድራዊ አይናችን ከብርሃን ወይም ከጨለማ ጋር የሚላመደው ቀስ በቀስ ቢሆንም፤ ሰማያዊ አይኖቼ ግን ያለምንም ችግር ሙሉ ለሙሉ ይመለከቱ ነበር። በመንግስተ ሰማይ እያንዳንዱ የስሜት ህዋሳቶቻችን ሙሉ ለሙሉ ለመሥራት መጠነ ሰፊ በሆነ ሁኔታ ብቃታቸው ይጨምራል። ኦ! ለስሜት ህዋሶቻችን ይህ እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው!

ወደፊት እየተራመድኩ በሄድኩ ቁጥር በተቀደሰ አግራሞት እየተሞላሁ መጣሁ። ከፊት ለፊቴ ሲሆን ስላለው ነገር ምንም እውቀት የለኝም፤ ይሁን እንጂ በማደርጋት በእያንዳንዷ እርምጃዬ መደነቁ እየጨመረ እንደሚሄድ ገምቻለሁ።

እናም ዝማሬ ሰማሁ።

# 3
# ሰማያዊ ዝማሬ

"ሰዮሁም፤ በዙፋኑም፣ በእንስሶቹም፣ በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምጽ ሰማሁ፤ ቁጥራቸውም እልፍ ጊዜ እልፍና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበረ።" ራዕ 5፥11

ልጅ በነበርኩበት ጊዜ በገጠርና ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ረዘም ያለ ጊዜ አሳልፍ ነበር። በደረቀው ሣር ላይ በምረማመድበት ጊዜ፣ ብዛት ያላቸው ወፎች ከጐጇቸው ውስጥ እየወጡ በመሬቱ ላይ ሲያርፉ እደነቅ ነበር። በሚበሩበት ጊዜ የንፋሱ ድምጽ የሚርገበገቡትን ክንፎቻቸውን ያጅበዋል።

በመንግስተ ሰማይ ቆይታዬ ጥርት ያለ ትውስታ ያለኝ ለሰማሁት ነገር ነው። ጥሩ አድርጌ እገልጽበታለሁ የምለው ቃል የክንፎችን የተቀደሰ እርግብግቦሽ ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ በመንግስተ ሰማይ ያለው ድምጽ የሚፈጥረውን ሁኔታ በአግባቡ ለመግለጽ ይህንን አባባሌን ሽህ ጊዜ አጎላው ዘንድ ያስፈልገኛል።

ከሰማኋቸው ድምጾች ሁሉ ውበት ያለውና አስደሳች ድምጽ ነበር፤ ደግሞ እኮ ፈጽሞ የማቆም ድምጽ አልነበረም። ልክ ከዘላለም እስከ ዘላለም እየቀጠለ እንደሚሄድ ዝማሬ ነበር። በመገረም ከመሞላቴ የተነሳ፤ የምፈልገው ነገር ማድመጥን ብቻ ነበር። ዝማሬን ብቻ አልነበረም የምሰማው። እኔ ራሴ የዝማሬው አካል የሆንኩኝ ይመስል



ነበር እናም ዝማሬው ወደ እኔ ውስጥ ይገባል በውስጤም ይመላለሳል። ቀጥ ብዬ ቆሜአለሁ፤ ይሁን እንጂ በዝማሬው ድምጽ እየተጽናናሁ ነበር።

አየሩን ከሞላው አስደሳች ድምጽና ዜማ ጋር መዋሃዴን ተገነዘብኩ፤ ፈጽሞ የሚጠገብ አልነበረም። ሰማያዊያኑ ዘማሪዎች የማንነቴ ሁለንተና ሁሉ በዝማሬው እንዲሳተፍ የፈቀዱልኝ ይመስላል። በዚያው ጊዜ ውስጥ ደግሞ በዙሪያዬ ስለሚሆነው ነገር ሁሉ ለማወቅ አትኩሮቴን ከአካባቢው ላይ አድርጌአለሁ።

የድምጹ ምንጭ ከወዴት እንደሆነ ያየሁት ነገር የለም። እኔ እንደገመትኩት ዝማሬውን ማንም ያመነጨው ድምጽ የሚመጣው ግን ከእኔ በላይ ካለ ስፍራ ነው። ነገር ግን ቀና ብዬ አላየሁም። ለምን እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም። ምናልባትም ዙሪያዬን በብዙ ሰዎች ስለተከበብኩ ወይም በአንድ ጊዜ በሁሉም ነገር ላይ ትኩረት በማድረጌ ስሜቶቼ በብርቱ ሥራ ስለተጠመዱም ሊሆን ይችላል። አንዳችም ጥያቄ አልጠየኩም፤ ስለምንም ነገር አልተደነቅኩም። ሁሉም ነገር ፍጹም ነበር። ልክ ሁሉንም ነገር እንደማውቀውና የምጠይቀው ነገር እንዳልነበር ይሰማኝ ነበር።

የሚኻርኅደጐዱ ድምጾች አዕምሮዬንና ልቤን ጭምር ሞልተውት ነበር፤ እነኝህን ድምጾች መግለጽ አስቸጋሪ ነው። ይሁን እንጂ እጅግ አስደናቂ የነበረው የመላእክቱ ክንፎች ናቸው። በእርግጥ አላየኋቸውም፤ ይሁን እንጂ የሚያሰሙት ድምጽ ግን ውበት ነበረው፤ በጭራሽ የማያቋርጥ ስልቱን የጠበቀ የተቀደሰ ዜማ። በአየሩ ላይ የሰፈፈው የሚያስተጋባ ድምጽ ማለቂያና ማብቂያ ከሌለው የዘላለም ምስጋና

ምንጭ የሚፈልቅ ይመስላል:: ባደመጥኩት ቁጥር ምን እንደሆነ እረዳው ነበር::

ሁለተኛው ድምጽ ዛሬም ድረስ በውስጤ ቀርቷል፤ ከመንግስተ ሰማይ ቆይታ ልምምዶቼ መካከል ጥርት ያለ ትውስታ ሰዚህ አንድ ድምጽ አለኝ:: እኔ ሙዚቃ ብዬ ነው የምጠራው፤ ይሁን እንጂ በምድር በኖርኩበት ዘመን ከሰማሁት ሙዚቃ ሁሉ የተሰየ ነው፤ ወደፊትም በምድር ላይ እሰማዋለሁ ብዬ አልገምትም:: የምስጋናው ዜማ እየሩን ሁሉ ሞልቶታል:: የማያቋርጠው አንጸባራቂ ብርሃንና ማለቂያ የሌለው ተሰዋዋጭነቱ በአግራሞት ሞላኝ::

ምስጋናው ፈጽሞ የሚያቋርጥ አልነበረም፤ ይሁን እንጂ እኔ በጣም የማስታውሰው ነገር በአንድ ጊዜ በመቶዎች የሚቆጠሩ መዝሙሮች የመዘመራቸው ነገር ነው ሁሉም እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ነበሩ:: ወደ ታላቁ አንጸባራቂ የመግቢያ በር ስቃረብ ዝማሬዎቹን ከተለያዩ አቅጣጫዎች መስማት ቻልኩ፤ እናም እያንዳንዱ ድምጽ እግዚአብሔርን የሚያከብር እንደ ነበር ተገነዘብኩ:: እኔ ዜማ መቀመር እችላለሁ፤ ይሄ ግን ከዚያ የላቀ ነበር:: አንዳንዱ ዝማሬ በሙዚቃ መሣሪያ የታጀበ ይመስላል፤ ነገር ግን እርግጠኛ አይደለሁም ስለ እርሱም ብዙ ትኩረት አልሰጠሁትም:: በየትም ቦታ የምሰማው የምስጋና ድምጽ ነበር፤ ሁሉም ደግሞ በሙዚቃ የተቀነባበረ ነበር፤ ይሁን እንጂ በውስጣቸው ያዘሉት ዜማና ድምጽ ግን ከዚህ በፊት አድምጨው የማውቀው አልነበረም::

“ሃሌ ሉያ!” “ምስጋና!” ክብር ለእግዚአብሔር! “ክብር ለንጉሱ!” የሚሉ ቃላት በሙዚቃው ጣልቃ ጎልተው ይደመጣሉ:: እነኝህን ዝማሬዎች መላእክቱ ይዘምሯቸው ወይም ከሰዎች ይውጡ ያወቅኩት



ነገር አልነበረም:: በመንግስተ ሰማይ ሁኔታ እጅግ ተገርሜ ስለነበር ዙሪያዬን አልቃኘሁም:: ልቤ ከዚህ በፊት ቀምሳው በማታውቅ ታላቅ ደስታ ተሞልታ ነበር:: በአምልኮው አብሬ አልተሳተፍኩም፤ ይሁን እንጂ ልቤ በዚያው አይነት ደስታና መንፈሳዊ ልቀት ውስጥ ትፈስ ነበር::

ሦስት የምስጋና ሲዲዎችን በአንድ ጊዜ ከፍተን ብንለቃቸው ድብልቅልቁና ምስቅልቅሉ የወጣ ድምጽ አዕምሯችንን ይረብሸዋል:: ይህ የምላችሁ ግን ፈጽሞ የተለየ ነው:: እያንዳንዱ ድምጽ ኅብር ባለው ሁኔታ የተዋሃደ ነው፤ እያንዳንዱ ድምጽ ወይም የሙዚቃ መሣሪያ ለሌላው ውበትን የሚጨምር ነው::

ምናልባትም እንግዳ ነገር ሊመስል ይችል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ እያንዳንዱን ዝማሬ ጥርት አድርጌ እሰየው ነበር:: የመግቢያ በሩን አልፌ በሄድኩ መጠን የእያንዳንዱን ዜማ ቅኝ እየተረዳሁት የምሄድ ይመስላል::

በሕይወት ዘመኔ በተለያዩ ዓመታት የዘመርኳቸው የቆዩ ቅኔዎችና ዝማሬዎች፤ ከዚህ በፊት ሰምቻቸው ከማላውቅ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዝማሬዎች ጋር ተደምረው የሙዚቃው አካል ነበሩ:: የምስጋና ቅኔዎች፤ ዘመናዊ ድምጸት ያላቸው ዝማሬዎችና የቆዩ አጫጭር አዝማቾች ጆሮዎቼን ሞሉት:: በውስጤ የፈጠሩትም ጥልቅ ሰላምን ብቻ ሳይሆን አይቼው የማላውቀውን ደስታ ጭምር ነበር::

ከመግቢያው ፊት ለፊት እንደቆምኩ፤ በዚያ ጊዜ ልብ ባልለውም በኋላ ላይ እንደተገነዘብኩት ግን፤ “አሮጌውና ግዙፉ መስቀል” ወይም፤ “በሚስማር ተቸንክረው የተዘረጉ እጆች” የሚሉ ዝማሬዎችን

አልሰማሁም:: አየሩን የሞሉት የትኞቹም ዝማሬዎች ኢየሱስ በምድር ላይ ስለከፈለው መስዋእትነት ወይም ሞት የሚያወሱ አልነበሩም:: አሳዛኝ ዝማሬዎችን አላዳመጥኩም፤ እንዲሁ በደመ ነፍስ አንድ ነገር ተረዳሁ:: በመንግስተ ሰማይ አሳዛኝ ዝማሬዎች የሉም:: ለምን እንዲዚህ ሆነ? ሁሉም ዝማሬዎች ኢየሱስ የነገሥታት ንጉሥ በመሆኑ የሚያመሰግኑ ነበሩ፤ በዚያ የነበረ በደስታ የተሞላ አምልኮ ለእኛ ስላደረገልን ታላቅ ነገርና ኢየሱስ ምንኛ ድንቅ እንደሆነ የሚያበስሩ ዝማሬዎች ነበሩ::

ሰማያዊ ዝማሬዎች ከሰማኋቸው ሁሉ የላቁ ነበሩ:: የዝማሬዎቹን ቁጥር ማስላት አልችልም:: ምናልባትም በሺህ የሚቆጠሩ ይሆናሉ፤ በአንድነት ያለማቋረጥ ይንቆረቆራሉ፤ ይሁን እንጂ አይዘበራረቁም፤ ይህን እንድል ያስቻለኝ እያንዳንዱን ዝማሬ ለማዳመጥና ግጥማቸውንና ዜማቸውንም አጣርቼ ለመለየት ችሎታው የነበረኝ በመሆኑ ነው::

ሞገስ በጠገበው በዚያ ዝማሬ ተገርሜ ነበር:: በሕይወት ሳለሁ ጥሩ የተባለ የዝማሬ ድምጽ ባይኖረኝም፤ አሁን ግን ብዘምር ድምጼ በትክክለኛው ቅኝት ውስጥ እንደሚገባና፤ በጆሮዬ እየተንቆረቆረ ካለው አየሩን ከሞላው በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች ድምጾችና የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር ህብር ባለው ሁኔታ ተዋህዶ መዘመር እንደምችል አውቄአለሁ::

አሁን ወደ ምድር ከተመለስኩ በኋላ እንኳን፤ አንዳንድ ጊዜ እነኛ ዝማሬዎች እንደ ገደለ ማሚቶ ድምጽ እያስተጋቡ በዝግታ ሲመጡ አደምጣቸዋለሁ:: በተለይ ደግሞ ድክምክም ብዬ በአልጋዬ ላይ ጋደም ባልኩና አይኖቼን በጨፈንኩ ጊዜ፤ አልፎ አልፎ በእንቅልፍ የምወሰደው



በነዚያ ልቤንና አዕምሮዬን በሚሞሉ ሰማያዊ ድምጾች እየሰማሁ ነው:: ቀኑ ለእኔ ምንም ያህል አስቸጋሪ ሆኖ ይዋል፤ ወዲያውኑ እያንዳንዱ ህልውናዬ ጥልቅ በሆነ ሰላም ይሞላል:: ዛሬም ቢሆን ትውስታዎቼ አልጠፉም፤ እርግጥ ነው እነኝህ ትውስታዎች እኛ ትውስታ ከምንላቸው ነገሮች የተለዩ ናቸው:: የእኔው ትውስታ ከእይታ ይልቅ እጅጉን በድምጽ ላይ የተመሠረተ ነው::

ስለ ዝማሬዎቹ ያለኝን ትውስታ በጥልቀት ስመለከተው፤ ሁኔታዎቹ ያልተለመዱ ናቸው:: በመንግስተ ሰማይ ላየሁት አንድ ነገር ወይም የተወደዱት ሰዎች ላደረጉልኝ ማጽናናት ጥልቅ የሆነ ትውስታ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ:: ከዚያ ይልቅ ደግሞ እነዚያን የሰማሁዋቸውን ድምጾች እጅግ ወድጃቸዋለሁ፤ አንዳንድ ጊዜም፤ እንደገና በግል እሰማቸው ዘንድ በጣም እናፍቃለሁ እላለሁ:: ወደፊት ይሆናል ብዬ የምጠብቀውም ይህንኑ ነው:: በዚያ ያሉትን ሁሉ ማየት እፈልጋለሁ፤ አንድ ነገር ደግሞ አውቃለሁ ከእነርሱ ጋር ለዘላለም እሆናለሁ:: በመንግስተ ሰማይ በተዘጋጀው ነገር ሁሉ ላይ መሣተፍ እፈልጋለሁ፤ ከሁሉም ይልቅ የምናፍቀው ግን እነዚያን ማብቂያ የሌላቸውን ዝማሬዎች መስማት ነው::

እውነቱን ለመናገር እግዚአብሔር ምን እንደሚሰማው አላውቅም፤ በማያቋርጠው የምስጋና ድምጽ እንደሚደሰትና እንደሚባረክ ባሰብኩ ጊዜ ግን ደስታና መጽናናት ይሰማኛል::

በእነኛ ደቂቃዎች ውስጥ-እርግጥ ነው ለእኔ የጊዜ ጉዳይ ግምት የሚሰጠው አልነበረም-ሌሎች ይነኩኝ ነበር፤ ፍቅር የተሞላው ሞቅ ያለ

የማበረታታት መንካታቸው ፍጹም እውነታዊ ነበር:: በዚያ ከዚህ ቀደም አይቻቸው የማላውቃቸውን ቀለማትም ተመልክቻለሁ:: በዚያ ከነበርኩበት ጊዜ ይህ ሕይወቴ ሙሉ እንደሆነ ተሰምቶኝ የሚያውቅበት ጊዜ የለም::

በቤቴ ውስጥ ነበርኩ፤ ለእኔ ሲሆን በተፈጠረና እኔም የእርሱ በሆንኩ ቤቴ ውስጥ! በምድር ላይ በየትኛውም ስፍራ ከተገኘሁበት ጊዜ ይልቅ በዚያ ብዙ ጊዜ ለመቆየት እፈልግ ነበር:: ጊዜው እያለፈ ሄዷል፤ እኔ ግን አሁንም በመንግስተ ሰማይ ውስጥ ነኝ:: የትኞቹም ጭንቀቶቼ፣ መረበሾቼና ስጋቶቼ ሁሉ ከእኔ ተጠርገው ተወስደዋል፤ ምንም አይነት ፍላጎቶች የሉኝም:: ሁሉም ነገር ፍጹም እንደሆነ ተሰማኝ::

መንግስተ ሰማይ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ፍርሃት ይሰማኛል፤ ምክንያቱም የመንግስተ ሰማይ እይታ ምን እንደሚመስል፣ ሁኔታው ምን እንደሚመስልና ምን ስሜት እንደሚሰማ በቃላት ልገልጸው ስለማልችል ነው:: በርግጥ ሁሉም ነገር ፍጹም ነው፤ ምንም ተጨማሪ ፍላጎት እንደሌለኝና ወደፊትም እንደማይኖረኝ አውቃለሁ:: ሌላው ይቅርና ስለምድር ወይም ወደ ኋላ ትቼው ስለመጣሁት ነገር በፍጹም አላሰብኩም::

እግዚአብሔርን አላየሁትም:: ምንም እንኳን እግዚአብሔር በዚያ እንዳለ ባውቅም፤ መለኮታዊ መገኘቱን የሚጠቁም ምስል ወይም የሚያንጸባርቅ ብርሃን አልተመለከትኩም:: አንዳንድ ሰዎች ወደ ውስጥኛው በር ገብተው እንደገና ስለመመለሳቸው ሲናገሩ ሰምቻለሁ:: ያ በእኔ ልምምድ ውስጥ አልተፈጸመም::



ያየሁት ነገር ቢኖር እጅግ አንጸባራቂ የሆነ የቀስተ ዳመና ከፊል ከበብ ነው:: በበሩ አቅጣጫ አሻግሬ ተመለከትኩ፣ በዚያ ያለውን ለማየት እጅግ ጓጉቼ ነበር:: ጭንቀት የተሞላበት ጉጉት አልነበረም፤ ይልቁንም የመንግስተ ሰማይን ፀጋና ደስታ ለመለማመድ ከነበረኝ ሰላም ካለው ግልጽነት የመነጨ ጉጉት ነበር::

ያንን ሁኔታ በሚመለከት ለእኔ ትርጉም የሚሰጠኝ አስተሳሰብ አንድ ብቻ ነው፤ በእርግጥ እግዚአብሔርን አይቼው ቢሆን ኖሮ ወደ ምድር ለመመለስ በጭራሽ አልፈልግም ነበር:: አንድ ጊዜ በእርግጥ በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ከሆንን፤ በጭራሽ ወደ ምድር ዳግመኛ እንመለስም፤ ምክንያቱም በንጽጽር ሲታይ ሁሉም ነገር ባዶና ትርጉም የሌለው እንደሆነ አስባለሁ::

እንደ እኔ ከሆነ፤ ከመንግስተ ሰማይ ደጃፍ ላይ መድረሱ በራሱ አስደናቂ ነገር ነው:: ከመታወቅ ያለፈም መለኮታዊ ደስታ ነው:: የሆነውን ነገር ለመግለጽ ቃላት እጅጉን ብቃት ያላቸው አይደሉም::

እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ፤ በመካነ መቃብር ሥፍራ በበርካታ የአስከሬን ሳጥኖች ፊት ቆሜ፤ "ጌታን ለሚያውቁትና ለሚወዱት፤ ከሥጋ መለየት ማለት ከእርሱ ጋር መሆን ማለት ነው" እያልኩ ሰብኬአለሁ::

እነዚያን ቃላት አምናቸው ነበር:: አሁን ግን አብዝቼ እምንባቸዋለሁ::

ጥቂት ቆይቶ፣ በአንድነት ሆነን ወደ መግቢያው በር መጓዝ ጀመርን:: ማንም ሰው ባይናገርም እንኳን እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ሁሉ እንዲቀበሉኝና ወደ መግቢያው በር እንዲሸኙኝ የላካቸው መሆኑን አወቅሁ::

አቀባበል ባደረጉልኝ ሰዎች አናት ላይ አሻግሬ ስመለከት፣ በሁለት አቅጣጫዎች ለአይን እየራቁ በሚደበዝዙ አጥሮች ጋር የተያያዘ አስደናቂ የመግቢያ ደጅ ቆሟል:: ከዚህ ከታላቁ የመግቢያ በር ጋር ሲነጻጸር አስቀድሞ ያሰው በር በጣም ትንሽ ነው:: አፍጥጬ ተመለከትኩ፣ ከበሩ በሁለት አቅጣጫዎች የተዘረጉትን አጥሮች መጨረሻ ለማየት ግን አልቻልኩም:: ወደ ላይ ቀና ብዬ ስመለከት የከፍታቸውን መጨረሻ ማየትም አልቻልኩም::

አንድ ነገር እጅግ አስደነቀኝ:: በምድር ላይ ሆኜ ስለመንግስተ ሰማይ ባሰብኩ ቁጥር፣ አንድ ቀን በከበሩ ድንጋዮች የተሠራ አምድ እንደምመለከት እገምት ነበር፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስም በከበሩ ድንጋዮች ስለተገነባ የመግቢያ ደጅ ይናገራል:: ደጁ የተሠራው በከበሩ ድንጋዮች አልነበረም፣ ይልቁን በብርሃን በተንቆጠቆጡ አምዶች የተገነባ ነበር:: ምናልባትም በተለያየ አቅጣጫ ሲመለከቷቸው የተለያየ ቀለማት በሚፈነጥቁ ፈርጦች የተገነባ ቢባል፣ ምናልባት በተሻለ ሁኔታ ይገልጸው ይሆናል:: እኔ የመሰለኝ፣ ልክ አንድ ሰው በተጋገረ ድፎ ኬክ ላይ አንጸባራቂ ማጣፈጫዎችን እንደሚረጭባቸው አይነት ሆኖ ነው የተሰማኝ:: ደጁ ያበራል ደግሞም ያንጸባርቃል::

ባገኘኋት ትንሽ ፋታ አንጸባራቂ ወደሆኑ በቀለማት የተዋቡ የብርሃን እመልማሎችና ወደ ነፀብራቃቸውም ተመለከትኩ:: የቀለማቱ ህብርና ውበት እጅግ አስገረመኝ፣ ለተወሰነ ጊዜም በእርሱ ላይ



እንዳተኩር አደረገኝ:: ይሁን እንጂ ወደፊት መራመዴን ቀጠልኩ፣ ሁኔታው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መገኛ ሥፍራ በክብር እየተሸኘሁ ይመስላል::

ከደጁ ውጭ ቆም አልኩ፣ ወደ ውስጥም መመልከት ቻልኩ:: በተጠረቡ ድንጋዮች የተሰሩ አውራ ጎዳናዎች እንዳሏት ከተማ ትመስላለች:: እጅግ የተደነቅኩት ደግሞ እነኚህ ጎዳናዎች የተሠሩት እውነተኛ በሆነ የወርቅ ጥርቦች ነው:: ምናልባት ከወርቅ ጡቦች የተሠሩ መንገዶችን በአይነ ልቡናችሁ መሣል የምትችሉ ከሆነ፣ ከደጁ ዘልቆ የተመለከትኩትን ሊገልጸው የታቃረበ ገጽታ እንደሆነ አስባለሁ::

ያየሁት ነገር ሁሉ የሚያበራ ነው:: አይኖቼ ካዩዋቸው አንጸባራቂ ቀለማት ሁሉ ድምቀት ነበራቸው በመሆኑም ከኃይሉ የተነሣ እንዲህ ያለውን ብሩህ ድምቀት ምድራዊ ሰው ሊቋቋመው አይቻለውም::

እንዲህ ባለው ታላቅ አግራሞት ውስጥ ሆኜ ወደ በሩ እየተራመድኩ ተጠጋሁ፣ ወደ ውስጥ እየገባሁ እንዳለም ገመትኩ:: ጓደኞቼና ዘመዶቼ ሁሉ ከፊት ለፊቴ ናቸው፣ ይጠሩኛል፣ ያበረታቱኛል፣ እንድከተላቸውም ይጋብዙኛል::

ድንገት ሁኔታዎች ተቀየሩ:: ይህን መግለጽ የምችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፣ ከፊት ለፊት የነበሩት ከበስተኋላዬ ሆነው አገኘኋቸው:: በዚያ ታላቅ ደጅ ውስጥ በማልፍበት ጊዜ ከጎኔ መሆን እንደፈለጉ ገመትኩ::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች፣ "እንዴት ነበር የምትንቀሳቀሰው? ትራመድ ነበር? ትንሳፈፍስ ነበር?" እያሉ ይጠይቁኛል:: እንዴት እንደሆነ እኔ አላውቅም:: እኔ የማውቀው ሊቀበሉኝ ከመጡት ሰዎች

ጋር ሆኜ ዝም ብዬ እሄዳለሁ። ከደጃፉ ዘንድ በተቃረብን ጊዜ የዝማሬው ድምጽ እየጨመረ ውበቱም እያየለ ሄደ። ነገሩ ሁሉ በጥቂቱ የሰሙትን በጣም ከርቀት የዩትን አስደናቂ ሁኔታ በቅርበትና በዝርዝር ለመረዳት እየቀረቡ እየቀረቡ እንደመምጣት ያለ ነው። በተጠጋን መጠን ሁሉም ነገሮች ውበት ያላቸው፣ ሕይወት ያላቸውና አስገራሚዎች እየሆኑ ይሄዳሉ። ልክ ወደ ደጁ እንደቀረብኩ ስሜቴ ይልቁን እየተነቃቃ ሄደ፣ እናም ወሰን በሌለው ደስታ ተሞላሁ።

ልክ በደጃፉ ላይ ቆም አልኩ፣ ለምን እንደሆነ ግን አላውቅም። እይታዬን በገዛው ነገር ሁሉ ተደስቻለሁ፣ እናም ወደ ውስጥ ለመግባት ፈለግኩ። እስከ አሁን ካየሁትና ከሰማሁት ነገር ሁሉ የላቀና አስደሳች ነገር አውቄአለሁ። ልክ በዚያው ቅጽበት የሰው ልጆች ሁሉ ናፍቆት ምን እንደሆነ ተገነዘብኩ። በዚያ ጊዜ በመንግስተ ሰማይ ደጅ ቆሜ ነበር፣ በሚያንጸባርቁ የብርሃን አምዶች አቋርጬ ወደ ውስጥ ለመዝለቅ ተዘጋጅቻለሁ።

ቅጽበታዊ በሆነች የእረፍት ጊዜ ውስጥ፣ አንድ ሌላ ነገር ደግሞ ተቀይሮ ነበር። እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ በሽዎች የሚቆጠሩ ድምጾችንና ዝማሬዎችን ከመስማት አልፌ፣ አሁን እኔ ራሴ የዝማሬው ተሣታፊ ሆኜአለሁ። ከሁሉም ጋር አንድ ሆኜአለሁ፣ በመካከላቸውም አስገብተውኛል። ለረዥም ዓመታት ልጎበኘው እናፍቀው በነበረው ሥፍራ ላይ ተገኝቻለሁ። ወደ ፊት ከመቀጠሌ በፊት በዝግታ ዙሪያዬን ሁሉ ቃኘሁ።

ከዚያ በኋላ፣ በድንገት በመንግስተ ሰማይ ደጆች ላይ እንደ ተገኘሁ ሁሉ፣ ድንገት ትቻቸው ሄድኩ።



4

# ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ምድር

“በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።” መዝ (23)፥4

የህክምና ባለሙያዎቹ አደጋው በደረሰበት ሥፍራ እንደተገኙ ወዲያው የመሞቴን ዜና ተናገሩ። አደጋው በተፈጠረበት ቅጽበት እንደሞትኩም ገለጹ። እንደተዘገበው ከሆነ ግጭቱ የተፈጠረው ከቀኑ 5:45 ነበር። የህክምና ባለሙያዎቹ በአደጋው የተጎዱትን ሌሎች ሰዎች ሲረዱ ቆይተው ወደ እኔ እንደገና የተመለሱት በ7:15 ላይ ነው። የልብ ምቴን አንድ ጊዜ እንደገና ተመለከቱ።


እንደሞትኩ ነበርኩ።

የመንግስቱ ህግ፣ አስከሬኑን ከአደጋው ስፍራ ከማንሳታቸው በፊት መሞቴን በይፋ ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ይደነግጋል። “ሞቷል” ብለው የማያረጋግጡ ከሆነ አምቡላንስ ወደ ስፍራው መጥቶ አስከሬኑን በማንሣት ወደ ሆስፒታል መውሰድ ይጠበቅበታል። አደጋው የተፈጠረበት አካባቢ መንግስት በአደጋ የሞቱ ሰዎችን ጉዳይ የሚመረምር የተለየ ቢሮ አልነበረውም፣ ይሁን እንጂ በኋላ ልረዳ እንደቻልኩት፣ የፍትህ ቢሮው የጸጥታ ክፍል ሞቴን ሊያረጋግጥላቸውና ሙት አካሌን ማንሣት እንዲችሉ ማድረግ ይችል ነበር።

ከእስር ቤቱ አምቡላንሶች መጡ፣ ንብረትነታቸው የመንግስትና የሀንትስ ቢላ ነበር። ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ አምቡላንሶች ምንም



ከወደላይ: የዶን ፎርድ መኪና ከአደጋው በኋላ የነበረበት ሁኔታ ነው::
ከወደታች: አደጋው የተፈፀመበት ሥፍራ





ተጎጂዎችን ሳይጭኑ በመጡበት ተመለሱ:: የመጨረሻውም ሲሄድ ተዘጋጀ:: በኋላ ላይ ከሰበሰብኩት መረጃ እንደተረዳሁት፤ አንድ ሰው በአደጋ የሞቱ ሰዎች ከመቀበራቸው በፊት አስከሬናቸው ወደሚያርፍበት ሥፍራ ሊያስወስደኝ የሆነ መኪና አዘጋጅቶ ነበር::

ከተጨረማመተችው መኪና ውስጥ አካሌን ለማውጣት የሚረዳ መሣሪያ አስመጡ:: የሞትኩ በመሆኑ ነገሮቹን ፈጠን ማድረግ ያን ያህል አስፈላጊ አልነበረም:: ትልቁ ትኩረታቸው መኪናዋን ከድልድዮ ላይ በማንሣት የትራፊክ ፍሰቱ እንደገና ሂደቱን እንዲቀጥል ማድረግ ነው::

ያ ከባድ መኪና ተጠምዝዞ በመምጣት በላዬ ላይ በወጣበት ጊዜ፤ የመኪናዬን የላይኛውን ኮፈን ሙሉ ለሙሉ ጨፈላልቆት ነበር:: በዚህ ጊዜም ዳሽ ቦርድ ወደ እግሬ መጥቶ የቀኝ እግሬን አደቀቀው:: የግራ እግሬ ደግሞ ለሁለት ተጎምዶ በዳሽ ቦርድና በመቀመጫው መካከል ተበታትኗል:: የቀኝ እጄ ከጭንቅላቴ በላይ አልፎ በመቀመጫዎቹ ላይ ተጋድሟል:: ገናም ሙሉ ለሙሉ ከሰውነቴ አልተላቀቀም፤ የሆነ ነገር አጣብቆ በጥቂቱ ተንጠልጥሏል::

ያ የግራ እጄ በሾፌሩ በኩል ባለው በር ላይ የተደገፈ ነበር፤ መኪናውን አሽከረክር የነበረው በቀኝ እጄ ነው:: በኋላ ላይ እንደተረዳሁት ዋና ዋናዎቹ አጥንቶቼ ጠፍተዋል፤ በዚህም ምክንያት የታችኛው የግራ እጄ ክፍል ከቀሪው ሰውነቴ ጋር የተያያዘው በትንሽ ሥጋ መሰል ነገር ብቻ ነው:: በግራ እግሬ ላይ የሆነውም ተመሳሳይ ነገር ነው:: ከጉልበቴ በላይ የነበረ አንድ የደም ሥር ገናም ደም ከጉልበቴ በታች ባለው እግሬ ላይና በእግሬ ጫማ ላይ በማፍሰስ ላይ

ነበር። የህክምና ዶክተሮች መላው ደሜ ከሰውነቴ ፈሶ ለምን እንዳላለቀ ለመግለጽ የህክምና ቋንቋ የላቸውም።

የመስተዋት ስብርባሪና ደም በስፍራው ሁሉ ተረጭቷል። በአደጋው ጊዜ የመኪናው መስተዋት ሲደቅቅ በፊቴ ላይ የፈሰሰ በመሆኑ በርካታ ጥቃቅን ጉድጓዶች በፊቴ ላይ ተፈጥረዋል። የካባድ መኪናው በፊት ጎማ በደረቴ ላይ ቆሞ ስለነበር፤ ከአይኔ፤ ከጆሮዬና ከአፍንጫዬ ደም ይጎርፍ ነበር።

በአደጋው ወቅት የተዘገበውን የህክምና ሪፖርት በማየት እንደተረዳሁት፤ ሃኪሙ ጭንቅላቴ እንደተጠፈጠፈና የውስጥ ብልቶቼ ሁሉ ስፍራቸውን እንደለቀቁ አውቋል። ገና ከመጀመሪያው የልብ ምቴ መቆሙን ካረጋገጠ በኋላ፤ አንድ የህክምና ባለሞያ ውሃ የማያሳልፍ ጨርቅ ሸፈነኝ፤ ይህም የመኪናዋን አካል ሁሉ የከደነ ነበር። እኔን ከስፍራው ለማንቀሳቀስ ወይም ወዲያውኑ ካለሁበት ሁኔታ ውስጥ ለማውጣት ምንም ሙከራ አላደረጉም። ምክንያቱም አካሌን ከመኪናው ውስጥ ጎትቶ ወይም ወደ ላይ አንጠልጥሎ ለማውጣት ከቶውን የማይታሰብ ነገር ነበር የግድ ያ አካልን ከተጨፈላለቀ መኪና ውስጥ ማውጣት የሚችል መሣሪያ ያስፈልጋል።

አደጋው በደረሰ ጊዜ እርዳታ ፈጥኖ መገኘት እንዲቻል ያደረጉት፤ ከከባድ መኪናው ኋላ ኋላ በመከተል ላይ የነበሩት ፖሊሶች ወደ እስር ቤቱ በመደወል የድንገተኛ አደጋ እርዳታ ሰጭ ሠራተኞች እንዲደርሱ በማድረጋቸው ነው። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ የእርዳታ ሰጭ ተሽከርካሪዎች ከሚገኙበት ሥፍራ በጣም የራቅን ነበርን።

በሌሎቹ ሁለት መኪናዎች ውስጥ የነበሩትን አሽከርካሪዎች መረመሯቸው፤ ሁለቱም አልቆሰሉም፤ በመሆኑም ቀጣይ የህክምና



ዕርዳታ እንዲደረግላቸው ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ፈቃደኞች አልሆኑም። ከባድ መኪናውን ያሽከረክር የነበረው እስረኛም ምንም አይነት የመቁሰል አደጋ አልደረሰበትም። የህክምና ባለሙያዎቹ ጤነኛ እንደሆነ ባረጋገጡበት ቅጽበት ይዘው ወደ እስር ቤቱ መለሱት። ፖሊስ በድልድዮ ላይ የነበረውን ሁሉንም የትራፊክ እንቅስቃሴ በመግታት የአምቡላንሱን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ነበር። አምቡላንሱን እየተጠባበቁም በሁለቱም አቅጣጫዎች በተለይም እኔ በመጣሁበት አቅጣጫ ረዥም ርቀት መኪና ተሰልፎ መቆም ቀጠለ። ከሁለት አቅጣጫ መኪና ማስተላለፍ የሚችል ጠባብ መንገዶች ያሉት ድልድይ ነበር፤ መኪኖችን በቀላሉ መታጠፍ የሚያስችል አልነበረም። መጠራቀም የጀመረው ተሽከርካሪዎች መታጠፍ ቢችሉ እንኳን ወደ አቅጣጫቸው በሚያስገባቸው መንገድ ውስጥ ለመግባት ተጨማሪ አርባና ሃምሣ ማይሎችን መንዝ ይጠበቅባቸዋል።

ከተለዋጩ መንገድ ቢያንስ ቢያንስ ግማሽ ማይል በመንዝ፤ ዲክና አኒታ ዋንሪከር በእግራቸው በመንዝ ወደ አደጋው ሥፍራ ደረሱ። ዲክና አኒታ በሰሜን ሃውስተን በሚገኘው ካሊን ውስጥ ቤተክርስቲያን መሥርተዋል። ተካፍዬው በተመለስኩት ጉባኤ ላይ ሁለቱም ንግግር አቅርበዋል። በትሪኒቲ ፒንስ የጉባኤ አዳራሽ በግል ሁለቱም ንግግር ... ስለመገናኘታችን እርግጠኛ አይደለሁም። ለብዙ ዓመታት የዲክ ዋንሪከርን መልዕክቶች አዳምጫለሁ፤ በአካል እርሱን ያየሁበት ጊዜ ግን ያ ጉባኤ ነበር።

ረቡዕ ዕለት ጠዋት ባልና ሚስቱ ከእኔ ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብለው የትሪኒቲ ፒንስን የጉባኤ አዳራሽ ለቀው ወጡ። ከሀውስተን አማካይ የሙቀት መጠን አኳያ የጥር ወር ጠዋት በጣም ቀዝቃዛ ነው።

በጉዟቸው ላይ ሳሉ፤ አኒታ እንዲህ አለች፤ "በብርድ እየተንቀጠቀጥኩ ነው፤ አንድ ጊዜ ቆም ብለን ቡናመጠጣት እንችላለን? ምናልባት ሙቀት ሲሰጠን እንዲችል አስባለሁ" አለች::

ዲክ፣ በሊቪንግስተን ሃይቅ አቅራቢያ አንድ ምግብ ቤት በማየቱ ወደዚያው አመሩ:: እነርሱ ቡና በመግዛት ላይ ሳሉ ነበር እኔ በመኪናዬ አልፌአቸው የሄድኩት::

ከዚያ በኋላ ዲክ ብዙ ጊዜ ፊቱን በእጁ መዳፎች ውስጥ እየቀበረ፤ "በቀላሉ ምን ይደርስብን እንደነበር ታውቃለህ? አደጋው የሚደርሰው በእኛ ላይ ሊሆን ይችል ነበር፤ አንተ እኮ የተጋጨኸው እኛ መኪናችንን በማቆማችንና አንተ አልፈኸን በመሄድህ ነው" ሲል ተናግሯል::

ባልና ሚስቱ ወደ ድልድዩ ከመድረሳቸው በፊት አደጋው ተፈጠረ፤ የመኪና እንቅስቃሴም ቆሞ መኪናዎች መጠራቀም ጀመሩ:: ሰዎች ከመኪናዎቻቸው እየመጡ በአካባቢያቸው እየተንቀሳቀሱ ከፊታቸው ስለተፈጠረው ነገር ጥያቄ መጠያየቅ፣ ያላቸውንም ጥቂት መረጃ ይወያዩበት ነበር::

ዲክና አኒታ ከመኪናቸው ውስጥ እንደወጡ አንዱን አሽከርካሪ፤ "በዚያ የተፈጠረው ነገር ምንድን ነው?" ሲሉ ጠየቁት::

"አንድ ከባድ መኪና አንዷን መኪና ጨፍልቋታል" የሚል ወሬ እየተላለፈ መጣ::

ዲክና አኒታ ጥቂት ደቂቃዎች በዚያ ቆዩ፤ የተፈጠረ ነገር ግን አልነበረም፤ ጭራሽ ከእነርሱ መኪና በኋላ ሌሎች መኪናዎች እየመጡ ይደረደሩ ጀመር:: በ6:30 እና 6:45 መካከል ባለ ጊዜ ውስጥ አደጋው



ወደተፈጠረበት ሥፍራ ለመሄድ ወሰኑ:: አንድ ፖሊስ ባገኙ ጊዜም ዲክ፤ "እኔ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ነኝ፤ እኔ ልረዳው የምችል ሰው ይኖር ይሆን? ማለትም ልጸልይለት የምችል ሰው ይኖር ይሆን?" ሲል ጠየቀው::

ፖሊሱ ራሱን በመነቅነቅ፤ "በእነዚያ ሁለት መኪናዎች ውስጥ ያሉ ሰዎች ..." አለ፣ ወደ መኪናዎቹ በጣቱ እየጠቆመ፤ "የደረሰባቸው ግጭት አነስተኛ ቢሆንም በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው የሚገኙት:: ከፈለጋችሁ ልታነጋግሯቸው ትችላላችሁ::"

"ሌላውስ መኪና? ከባድ መኪናው በላዩ ላይ የቆመበት?"

"በቀይዋ መኪና ውስጥ ያለው ሰው ሞቷል::" ዲክ ከፖሊሱ ጋር በመነጋገር ላይ እንዳለ አኒታ ወደ ሌሎቹ መኪናዎች አመራች:: ገና በጥቂቱ ጎንጨት ያደረገችለትን ቡና ለሽማግሌው ሰጠችው::

በኋላ ላይ ዲክ ሁኔታውን የገለጸው እንዲህ ሲል ነበር፤ "እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረኝ፤ በቀይዋ መኪና ውስጥ ላለው ሰው መጸለይ ያስፈልግሃል":: ዲክ እጅግ ታዋቂ የሆነ የመጥምቃውያን ቤተክርስቲያን ሰባኪ ነው:: ለሞተ ሰው ጸሎት ማድረግ እርሱ ከሚያምንበት ትምህርተ መለኮት ያለፈ ነገር ነው:: "ይህን ማድረግ አልችልም፤" ሲል አሰበ:: "እዚያ ሄጄ የምጸልየው በምን መንገድ ነው? ሰውየው እኮ ሞቷል::"

ዝናቡ ጥቅጥቅ አድርጎ ካፊያውን እየለቀቀው ነበር፤ ይሁን እንጂ ዲክ በዙሪያው ያለውን አጥርቶ መመልከት ችሏል:: ወደ ፓሊሱ አፍጥጦ ተመለከተ፤ ሊናገረው ያለው ነገር ትርጉም ሊሰጠው

እንደማይችል አውቋል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ጥርት አድርጎ ስለተናገረው ሊያደርግ ስላሰው ነገር አንዳች ጥርጥር አልነበረውም:: ለሞተው ሰው ይጸልይለት ዘንድ እግዚአብሔር ተናግሮት ነበር:: ነገሩ ሁሉ እንግዳና ያልተለመደ ቢሆንበትም ዲክ መንፈስ ቅዱስ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ ውስጡን እያነሳሳው ነበር::

"በቀይዋ መኪና ውስጥ ላለው ሰው መጸለይ እፈልጋለሁ" አለው ዲክ በመጨረሻው::

"እንደነገርኩህ ሰውየው ሞቷል::"

"ነገሩ እንግዳ እንደሚሆንብህ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ በማንኛ ውም መንገድ ልጸልይለት እፈልጋለሁ::"

ፖሊሱ አንዳች ቃል ከመናገሩ በፊት ትኩር ብሎ ሲመለከተው ቆየና በመጨረሻው፤ "ደህና ማድረግ የምትፈልገው ያንን ከሆነ ቀጥል፤ ነገር ግን እንደነገርኩህ በዚያ የሚታየው ነገር ሁሉ ዘግናኝ ነው:: ሰውየው ሞቷል፤ ከዚያ መኪናውን ከሸፈነው ጨርቅ በታች የምትመለከተው ነገር ቢኖር የተበጣጠሰ የሰው አካል ነው:: ስፍራውን የሞላው ነገር ደምና ስብርባሪ ጠርሙስ ነው:: አካሉ ደግሞ እንዳይሆን ነገር ሆኗል::"

ዕድሜው በአርባዎቹ ውስጥ የነበረው ዲክ እንዲህ አለው፤ "በሼትናሙ ጦርነት ጊዜ ህክምና በመስጠት አገልግያለሁ፤ እናም የደሙ ጉዳይ የሚያስቸግረኝ አይደለም::"



"ላስጠንቅቅህ ግድ ነው" አለ ሰውየው ቆም አለና፤ ትከሻውንም ሰበቅ አድርጎ "ማድረግ የምትፈልገውን አድርግ፤ ነገር ግን ከዚህ ቀደም እንደዚህ አደጋ የደረሰበት አካል አይተህ እንደማታውቅ እነግርሃለሁ::"

"አመሰግናለሁ" አለና ዲክ ወደተሸፈነችው መኪና አመራ:: በፎቶግራፉ ላይ እንደምትመለከቱት፣ ለማመን እጅግ አስቸጋሪ ነው፤ ይሁን እንጂ ዲክ በደረቱ እየተሳበ በመኪናዊ ከፈን ላይ ወጣ:: መኪናዋ ከኋላዋ የሚከፈት በር ነበራት፤ ደግነቱ ያ የመኪናዋ አካል አልተጎዳም:: መኪናዋ በጨርቅ ተሸፍናለች፤ ያንን ከላዩ ላይ ማንሣት አልቻለም፤ በመሆኑም የመኪናዋ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ጨልሟል:: ዲክ በጥንቃቄ እየተሳበ ከኋላዊ ወደ እኔ ተጠጋ፤ በጀርባው መቀመጫ ላይ በደረቱ ተኛ ና እጁን በቀኝ ትከሻዬ ላይ አሣረፈ::

እናም ይጸልይልኝ ጀመረ:: በኋላ ላይ "እንድጸልይ አንዳች ነገር እያስገደደኝ እንዳለ ተሰማኝ:: ሰውዬው ማን እንደሆነ፤ አማኝ ይሁን አይሁን አላውቅም:: የማውቀው ነገር ለዚያ ሰው እንድጸልይለት እግዚአብሔር እንደተናገረኝ ብቻ ነው" ሲል ተናግሯል::

ዲክ በመጸለይ ላይ ሳለ፤ ስሜቱ ይቀስቀስና ደጋግሞ ማልቀስ ይጀምራል:: ቀጥሎ ደግሞ መዘመር ጀመረ:: ዲክ ድምፀ መልካምና በአደባባይም የሚዘምር ሰው ነው:: ዝማሬን ሲመዘምር ሲል ደጋግሞ ጸሎቱን ቆም ያደርግ ነበር::

ዲክ እግዚአብሔር ለእኔ እንዲጸልይልኝ እንደጠራው ብቻ አልነበረም ያመነው፤ ይልቁንም የማይታየው በሽታ ማለትም ህሊናየና ውስጣዊ አካሌ ህመም ሁሉ እንዲፈውስ ነበር በእምነት ይጸልይልኝ የነበረው::

ይህ ምናልባት ግራ የሚያጋባ ይሆናል፤ ምክንያቱም ዲክ መሞቴን ያውቅ ነበር:: ፖሊሱ በነገረው ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ ንዝረቴን ተመልክቶ አረጋግጧል:: በዚያ ሁኔታ ለምን ይጸልይ እንደነበረ አልተረዳውም፤ የሚያውቀው አንድ ነገር እግዚአብሔር እንደተናገረው ብቻ ነው:: ይፀልይ የነበረው ለሚመለከተው ውጫዊ አካሌ ጉዳት አልነበረም፤ ውስጣዊ ለሆነው ጉዳቴ ብቻ መጸለዩን ቀጠለ:: እርሱ እንደተናገረው ይፀልይ የነበረው ከዚህ በፊት ጸልዮ በማያውቀው ሁኔታ በከፍተኛ ፍቅር፤ ጽናትና ስሜት ውስጥ ሆኖ ነበር:: በኋላ ልረዳው እንደቻልኩት ዲክ በከፍተኛ ስሜት የሚቀጣጠል ሰው እንደሆነ ነው::

እናም እንደገና መዘመር ጀመረ እንዲህ እያለ፤ "ከውድቀት ሥጋት የተነሳ ለምን ሰላምን አጣን? አላስፈላጊ የሆነ ስቃይስ ስለምን ተሸከምን? ምክንያቱ ነገሮችን ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ማቅረብ ባለመቻላችን ነው!" እየሆነ ስለነበረው ነገር ሁሉ በግሌ እርግጠኛ ሆኜ የማውቀው ነገር ቢኖር፤ ዲክ "በክርስቶስ ወንድሞች ነን" የተሰኘውን ቆየት ያለ የተባረከ መዝሙር መዘመር በጀመረበት ጊዜ አብሬው መዘመር መጀመሬን ነው::

ወደ አዕምሮዬ በተመለስኩበት ቅጽበት፤ ሁለት ነገሮችን ተገነዘብኩ:: የመጀመሪያው ነገር እየዘመርኩ ነበር፤ በመንግስተ ሰማይ ከነበረው የዝማሬ ዜማ የተለየ ዝማሬ:: አስቀድሞ የራሴን ድምጽ ነበር የሰማሁት፤ ቆይቶ ደግሞ ሌላም ሰው ይዘምር እንደነበር ተገነዘብኩ::

የተገነዘብኩት ሁለተኛው ነገር፤ አንድ ሰው እጄን ግጥም አድርጎ እንደያዘኝ ነበር:: ያ አያያዝ ጠንካራና ኃይለኛ ነበር፤ ወደ ምድራዊው ሕይወት በተመለስኩ ጊዜ በአካሌ ላይ በመጀመሪያ የተሰማኝ ስሜት ያ ነበር::



እጄን አጥብቆ የያዘኝን የእዚያን እጅ ታላቅነት ለመረዳት ከዓመት በላይ ወስዶብኛል::

# 5
# በምድር ሆስፒታል ውስጥ

“አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሲጠራ በእነርሱ አያፍርም፤ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና”

ዕብ 11፥16

ስለዚያች ብትንትኗ ወጥቶ ስለቆመች መኪና ዓለም ምን እንደዘገበች አላውቅም፤ በዚያ ረቡዕ ከሰዓት በኋላ ግን ዲክ ዋንሪከር መናገር እስኪሳነው ድረስ ይንተባተብ እንደነበር እርግጠኛ ነኝ። የሞተ ሰው አብሮት መዘመር በጀመረ ጊዜ፤ ከዚያች ጭርምትምቷ ከወጣ መኪና ውስጥ እየደኸ ወጥቶ በቅርቡ ወደሚገኝ የህክምና ባለሙያ እየሮጠ ሄደ።

“ሰውዬው በሕይወት አለ! አልሞተም! በሕይወት አለ! ” ማን ሊያምነው ይችላል? ሰባኪው፣ ከሞተ አንድ ሰዓት ተኩል ላለፈው ሰው መፀለይ መጀመሩ በራሱ አስገራሚ ነው።

መንገዱን በፈጣን ሩጫ እያቋረጠ፤ “ሰውየው ወደ ሕይወት ተመልሷል! ” እያለ ይጮህ ጀመር።

የህክምና ባለሙያው ትኩረት ሰጥቶ ይመለከተው ገባ። “በሕይወት አለ! የሞተው ሰውዬ አብሮኝ መዘመር ጀምሯል”



በኋላ ላይ ከሁኔታቸው ሊረዳው እንደቻለው የሚናገሩቸው ቃላት ትርጉም የሰጣቸው አልነበረም። እርሱ ግን፤ “እየዘመረ ነው! በሕይወት አለ” እያለ መጮሁን ቀጠለ።

“ኧረባክህ ... እውነትህን ነው?” ሲል ሃኪሙ በፌዝ ጠየቀ።

“ከምሬ ነው የምናገረው፤ ይህ ሰው በሕይወት አለ! ”

“እኛ የህክምና ባለሙያዎች ነን። የሞተን ሰው በእይታ ብቻ ለይተን እናውቃለን። ያ ሰው ፈጽሞ ሞቷል። ”

“የምነግራችሁን አድምጡ፤ ሰውየው ከእኔ ጋር እየዘመረ ነበር በሕይወት አለ! ”

“ለማንኛውም የፍትህ ቢሮው የፀጥታ ሠራተኛ ወደዚህ እየመጣ ነው።” ካለ በኋላ እኔ መሞቴን እነርሱ ቢያውቁም እንኳን በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው ሰው በስፍራው ተገኝቶ መሞቴን እስካላረጋገጠ ድረስ አካሌን ማንሣት ባለመቻላቸው ምክንያት መዘግየታቸውን ገለጸለት። በመቀጠልም፤ “ነገር ግን ፍጹም እርግጠኛ ሆኜ እነግርሃለሁ ሰውዬው ሞቷል” አለው። ወደ መኪናው ተጠግቶ ሁኔታዬን ማየት ስላልፈለገ ሰውዬው ፊቱን አዙሮ ከዲክ ፊት ፈቀቅ አለ።

በርካታ አምቡላንሶች መጥተው በመጡበት ሁኔታ ተመልሰው ሄደዋል።

ዲክ በዚያ ቀርቶ ወደነበረው አንድ አምቡላንስ በፍጥነት ሄዶ ሹፌሩን፤ “ያ ሰው በሕይወት አለ። ብትፈልግ ሂድና ተመልከተው” ሲል ተማጸነው።

የህክምና ባለሙያው የአዕምሮ ጤና የጎደለበትን ሰው እንደሚያነጋግር እርግጠኛ ሆኖ፣ "እባክህ፣ ሥራችንን ጠንቀቅን እናውቃለን:: ሰውየው ፈጽሞ . . ."

"አንድ ጊዜ አድምጠኝ! በዚህ ድልድይ ላይ ተጋድሜ እተኛለሁ፤ ወደዚህ መጥተህ የማትመለከት ከሆነ፤ ረግጠኸኝ ብቻ ነው ማለፍ የምትችለው!"

"ሰውዬው ሞቷል::"

"እንደዚያ ከሆነ በእኔ ላይ ማላገጥ ትችላለህ:: አንድ ጊዜ ሄደህ የደም ንዝረቱን እጣራ" ዲክ ልመናውን ቀጠለ::

"ይሁን ለአንተ ስንል ሄደን እናጣራለን" ሲል አጉተመተመ ሰውዬው:: ወደ መኪናው ሄደ፣ የተሸፈነውን ጨርቅ ገለጠ፣ ወደ ውስጥ ገባና የቀኝ እጄን ጨበጠ:: የደም ንዝረት እንዳለኝ አየ::

አሁን ሰው ሁሉ በፍጥነት መንቀሳቀስ ጀመረ:: ከመኪናው ውስጥ እንዴት እንደሚያወጡኝ መነጋገር ቀጠሉ:: በአንደኛው የመኪናዋ ጎን ሲያወጡኝ ይችሉ ነበር፤ እንደዚያ አድርገው ቢያወጡኝ የግራ እግሬ እዚያው ይቀር ነበር:: በዳሽቦርዱ፣ በእግሬና በመቀመጫው መካከል እንዳችም ክፍተት አልነበረም:: ስለሆነም የግድ እግሬን መቁረጥ ነበረባቸው:: ለነገሩ እግሬ ከቀረው ሰውነቴ ጋር የተያያዘው ላመል ያህል ነው:: ቀኝ እግሬንም ማውጣት ስለመቻላቸውም እንኳን እርግጠኛ አልነበርኩም:: በተጨፈለቀ መኪና ውስጥ የሰውን አካል የሚያወጣውን ጃውስ ኦፍ ላይፍ የተባለውን መሣሪያ ሳይጠቀሙ እኔን ለማውጣት ቢሞክሩ የተወሰነው አካሌ መኪናው ውስጥ መቅረቱ የግድ ነበር:: አስፈላጊው መሣሪያ እስኪመጣ መቆየቱን መረጡ:: መሣሪያው



ከሁንትስቪላ በፍጥነት እንዲመጣ ስልክ መደወል ጀመሩ፤ ያ ስፍራ ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ ሰላሣ ማይሎች ያህል ርቀት ነበረው:: እርግጠኛ ነኝ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ አድርገውልኛል፤ እኔ ግን የማውቀው ነገር አልነበረም:: ብዥታ በሞላበት ትውስታ ውስጥ ሆኜ ሰዎች በዙሪያዬ ሲንቀሳቀሱ፣ ሲዳስሱኝና ሲነጋገሩ ይታወቀኛል:: ድምጽ ይሰማኛል፤ ነገር ግን የሚነጋገሩት ምን እንደሆነ በውል መረዳት አልችልም:: ዲክ ትቶኝ ለመሄድ አልፈቀደም:: እንደገና ወደ መኪናው ውስጥ ገባና በአጠገቤ ተንበርክኮ መሳሪያው እስኪመጣ ድረስ መጸለዩን ቀጠለ:: ከአጠገቤ የተለየው ከመኪናው ውስጥ አውጥተው አምቡላንስ ውስጥ ካስገቡኝ በኋላ ነበር:: የህክምና ባለሙያዎቹ ከመኪናዋ ውስጥ ሲያወጡኝ ብዙ ሰዎች መሆናቸውን ማስታወስ ጀምሬአለሁ ቢያንስ ስድስት ወይም ሰባት ያህል ነበሩ:: እያንቀሳቀሱኝ ሳለ ስለ እግሬ ሲነጋገሩ ሰማሁ:: እንዲያውም አንደኛው ሰው፤ የግራ እግሬ ተጎምዶ እንዳይወድቅ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ይናገር ነበር::

መላው የሰውነት ሥርአቴ ተናግቶ ስለነበር ምንም የህመም ስሜት አይሰማኝም ነበር በዚያ ጊዜ በምንም አይነት ሁኔታ ህመም አልተሰማኝም:: የህመም ስሜት ይሰማኝ የጀመረው በኋላ ላይ ነው::

በቃሬዛው ላይ አስተኝተው ወደ አምቡላንሱ እየገፉ ወሰዱኝ:: የሆነ የብርሃን ጨረር በፊቴ ላይ አረፈ:: ከበላዬ የነበረው ድልድይ ከተሠራበት የብረት ፍርግርጎች ሌላ የታየኝ ነገር አልነበረም:: ጭንቅላቴን ማንቀሳቀስ አልቻልኩም:: ሰዎች ሲንቀሳቀሱና በእግራቸውም የጠርሙስ ስብርባሪዎችን ከመሬቱ ጋር እያሹ ሲያደቅቁ ይሰማኛል:: ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ነበር የሚናገሩት:: በመሆኑም የሚናገሩት ምን እንደነበር ለማወቅ ተቸግሬ ነበር::

"አንድ አሰቃቂ ነገር በዚህ አካባቢ ተከስቷል፡፡ ይህ አሰቃቂ ነገር የደረሰው ደግሞ በእኔ ላይ ይመስለኛል" የሚል ዐይነት ሃሣብ ያሰብኩ ይመስለኛል፡፡ ምንም እንኳን ወደ አምቡላንሱ እየወሰዱኝ እንደነበር ባውቅም፣ ያለክብደት እንደሆንኩ ይታወቀኛል፡፡

አምቡላንሱ ወዴት ወዴት እንደተጓዘ የማውቀው ነገር የለም፣ በኋላ ግን ወደ ሁለት ሆስፒታሎች መሄዳችንንና የእነዚህ ሆስፒታሎች ደረጃም ከገጠር ክሊኒኮች ትንሽ ከፍ የሚል እንደነበር ተረድቻለሁ፡፡

"ልናደርግለት የምንችለው ነገር የለም" ሲል ሰማሁት አንድ ዶክተር ከመረመረኝ በኋላ፡፡ "በሕይወት መቆየት የሚችል አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ከመኪናው ውስጥ በሕይወት ብታወጡትም፣ የሚተርፍ ነገር አይደለም፡፡ ተስፋ የለውም"

እንደገና በአምቡላንሱ ውስጥ አስገብተው ይዘውኝ ሄዱ፡፡ ከአምቡላንሱ ውስጥ አውጥተው በመጠኑ ሰፋ ወዳለው የክልሉ የህክምና ማዕከል ወደሆነው ሁንትስቪላ ወደተባለው ሆስፒታል ሲያስገቡኝ እንደሰመመን በሆነ ትውስታ ትዝ ይለኛል፡፡ ከቀኑ 8:30 ላይ ነበር፡፡

በዚያ ጊዜ ባለስልጣኖቹ ጉዳዩን ለባለቤቴ ለኢቫ አሳውቀዋት ነበር፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ እያስተማረች ነበር፣ አንድ ሰው ወደ ትምህርት ቤት ደውሎ ስለ አደጋው እንዲነገራት አደረገ፡፡ ሌላ ሰው ደግሞ ሦስቱ ልጆቻችን ወደሚማሩበት ት/ቤት ደወለ፡፡ የቤተክርስቲያን አባላት የሆኑ ሰዎች ከኢቫ አንዳች ቃል እስኪያገኙ ድረስ ልጆቹን ወደ ቤታቸው ወሰዷቸው፡፡

ከሰዓታት በላይ ሞቼ እንደነበር ማንም አላወቀም፡፡ ወደ ምድር በተመለስኩበት የመጀመሪያዎቹ ሰዓታት የጉዳቱ መጠን ምን ያህል



ታላቅ እንደነበር ምንም ዐይነት ግንዛቤ አልነበራቸውም፡፡ ስለአደጋው ዝርዝር ሁኔታ በትክክል ባይረዱትም እንኳን፣ የቤተክርስቲያን አባሎች ስለ መፈወሴ ይጸልዩልኝ ነበር፡፡ ሌሎችም በጸሎት እንዲተባበሯቸው መደዋወል ጀምረዋል፡፡

ኢቫ ሞቼ እንደነበር ያወቀችው አደጋው ከደረሰ ከሁለት ሣምንት በኋላ ዲክ ዋንሪከር ሲጠይቀኝ ወደ ሆስፒታል በመጣባቸው ቀኖች በአንዱ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ብቻ ነበር ነገሩ ምን ያህል ከባድ እንደነበረ የተረዳችው፡፡ በተጨማሪም በዚያው ጊዜ የኢንሹራንስ ወኪላችንና የሳውዝ ፓርክ ቤተክርስቲያን አባል የሆነችው አንዲልማን በአደጋው የተጨፈላለቀችው መኪና ከድልድዩ ላይ ከተነሳች በኋላ የተወሰደውን ፎቶ ግራፍ ይዛ መጣች፡፡ ኢቫ የአደጋውን ከባድነት ማወቅ የነበረባት ቀደም ብሎ መሆን እንደነበረበት ተናገረች፡፡ ጨምራም፣ በወቅቱ ትሠራው በነበረው ነገር ላይ ትኩረት ለጥታ ስለነበር ስለአደጋው በሰማች ጊዜ ቀላል ይሆናል ብላ በመገመት ያን ያህል ትኩረት ሳትሰጠው ልትቀር ትችል እንደነበር ተናግራለች፡፡

ከዚያ በኋላ ልጆቻችን፣ ቤተሰቦቻችንና ወዳጆቻችን ሁሉ አደጋው ምን ያህል ከባድ እንደነበርና በሕይወት መኖር ወደማልችልበት ሁኔታ ተቃርቤ እንደነበር ተገነዘቡ፡፡

ከህክምና ባለሙያዎቹ አንዱ፣ "አሁን እዚህ ደርሰናል፡፡ አሁን ደህና ትሆናለህ" አለ፡፡

ወደ ሆስፒታል ውስጥ እንደገባሁ አውቄአለሁ፡፡ እኔን ለተሸከመው ባለተሽከርካሪ ጎማ ቃሬዛ መንገድ ለመልቀቅ ሰዎች

በፍጥነት ወደ ኋላቸው ሲያፈገፍጉ ድንግዝግዝ ባለ ብዥታ ውስጥ ማየት ቻልኩ:: ፊቶች ወደ እኔ አጎንብሰው ይመለከታሉ፤ ቃሬዛው እየተሽከረከረ ባለበት ሁኔታ ሰቅጽበት አይኖቻችን ይጋጫሉ::

እኔን ይጠባበቅ የነበረ ዶክተር ወዳለበት ክፍል ወሰዱኝ:: ሁሉም ነገር እንግዳ ነው፤ ይመረምረኝ ስለነበረው ዶክተር የማስታውሰው አንድ ነገር፣ ሰውየው መላጣ እንደነበረ ነው:: ለተወሰነ ጊዜ ስመረምረኝ ቆየ:: በኋላም፤ "ሚስተር ፒፐር፤ እንተን ለማዳን ማድረግ የምንችለውን ነገር ሁሉ አድርገናል" አለ:: ሦስት ጊዜ ያህል እንደተናገረ እርግጠኛ ነኝ:: "ከፉኛ ነው የተጎዳኸው፤ በጽኑ ተጎድተሃል፤ ይሁን እንጂ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል::" በኋላ ላይ እንደተረዳሁት፤ ምንም እንኳን ስለእፉ ይህንን ቢናገርም ይተርፋል ብሎ በፍጹም ተስፋ አላደረገም:: ይሁን እንጂ ተስፋ እንዲኖረኝና በሕይወት ስመኖር እንድፍጨረጨር ማድረግ የሚችለውን ነገር ሁሉ አድርጓል:: በርካታ ሰዎች በዙሪያዬ ይሽከረከሩ ነበር:: በእርግጥ እኔ በሕይወት እንድቆይ ጥረት እያደረጉ ነበር፤ እኔ ግን ምንም ዐይነት የህመም ስሜት አይሰማኝም:: ነፍሴ በስለለች ቀጭን የብርሃን አመልማሎ ላይ የተንጠለጠለች አይነት ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ:: ምንም ስሜት አይሰማኝም፤ ይሁን እንጂ ድንግዝግዝ ባለ ስመመን ውስጥ በዙሪያዬ እየሆነ ስላለው ነገር በጥቂቱም ቢሆን ግንዛቤ ነበረኝ::

"ባለቤትህን በስልኩ ውስጥ አቅርበንልሃል" ሲል አንድ ሰው ተናገረ:: በቴሌፎን ወደ ድንገተኛው ክፍል አመጧት፣ ነርሷ የቴሌፎኑን ቀፎ ወደ ጆሮዬ አቀረበችው፤ እናም ከኢቫ ጋር መነጋገራችን ትዝ ይለኛል፤ ይሁን እንጂ ስለተነጋገርነው ነገር አንዲት ቃል አላስታውስም::



ኢቫ የተለዋወጥነውን ንግግር ሁሉ ታስታውሳለች:: እርሷ እንደተናገረችው ከሆነ የተናገርኩት፤ "ይህ ስለተፈጠረ በጣም አዝናለሁ" የሚሉትን ቃላት ብቻ ነበር::

"አይዞህ ዶን፤ ያንተ ስህተት አይደለም"

እኔ እየደጋገምኩ፤ "በጣም አዝናለሁ:: ወደ ቤቴ መምጣት ነበር የፈለኩት፤ እባክሽ ወደ ቤቴ ውሰጂኝ" ማለቴን ቀጠልኩ:: ልክ ህፃናት እንደሚያደርጉት ዐይነት ባለ ሁኔታ፤ በሰማያዊው ቤቴ መቆየት የማልችል ከሆነ ምድራዊ ወደሆነው ቤቴ መመለስ እንደምፈልግ እገልጽ ነበር::

በሀውስተን ወደሚገኘው ሂርማንን ሆስፒታል የአካል ጉዳተኞች ማዕከል፤ በሕይወት አድን ሂሊኮፕተር ሊያጓጉዙኝ እንደሆነ ደጋግመው አሳውቀውኛል:: ይሁን እንጂ የአየሩ ጠባይ ጥሩ ያልነበረና ደመናውም በጣም ወርዶ ሰማዮን ጋርዶ ስለነበር ሂሊኮፕተሯ እንዳትንቀሳቀስ ወሰኑ::

የጤንነቴ ሁኔታ በፍጥነት እያሽቆለቆለ በመውረዱ፤ ነፍሴ ያንን ክሰዓት በኋላ እንኳን ማለፍ እንደምትችል እርግጠኞች አልነበሩም:: በዚህ ምክንያት የህክምና ቡድኑ ከበድ ያለ ውሳኔ ወሰነ:: ወደ አምቡላንሱ መልሰው በማስገባት ሰማንያ ማይልስ ያህል ርቆ ወደሚገኘው ወደ ሀውስተን ሊወስዱኝ ተስማሙ:: እኔን ሊንከባከቡ የሚችሉበት የተሟላ ነገር አልነበራቸውም:: ዳግመኛ በሕይወት የመኖር እድል ያለኝ ከሆነ፤ መድረስ ያለብኝ ብቸኛው ስፍራ የሂርማንን ሆስፒታል ብቻ ነበር::

ሌላ አዲስ አምቡላንስ አቀረቡ:: እንደዚያ በቆሰልኩበት ሁኔታ ውስጥ በየትኛውም ሰኮንድ ልሞት እንደምችል ያስቡ ነበር:: አንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች ማገናዘብ ጀመርኩ፤ ለምሳሌም የአዲስን መኪና አዲስ መአዛ በተለይም ደግሞ የቀለሙን ሽታ መለየት ቻልኩ::

መኪናው መንቀሳቀስ እንደጀመረ "አንተ የመጀመሪያው ህመምተኛችን ነህ" አለ የህክምና እርዳታ የሚሰጠኝ ሰው::::

"ምን አልክ?"

"በዚህ አምቡላንስ ለመጓጓዝ አንተ የመጀመሪያው ሰው ነህ አለ":: ወደ ሆስፒታል ልንወስድህ ነው:: በምንችለው ፍጥነት ሁሉ ወደዚያ እናደርስሃለን::"

"በምን ያህል ፍጥነት ልጓዝ?" ሾፌሩ በአጠገቤ የተቀመጠውን ረዳቱን ጠየቀው::

"መብረር በምትችልበት ፍጥነት ሩጥ"::

"ያ ማለት ፍጥነቱ ምን ያህል ይሁን ማለት ነው?" ሾፌሩ ደግሞ ጠየቀ::

የነዳጅ መስጫውን እስከመጨረሻው እርገጠው! አሁኑኑ ከዚያ መድረስ አለብን!

ጉዞውን ከመጀመራችን አስቀድሞ ምንም አይነት የህመም ስሜት አይሰማኝም ነበር:: በውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ:: ክብደት አልባ እንደሆንኩ ይሰማኛል ማለትም አዕምሮዬ መላውን አካሌን መቆጣጠር አይችልም:: ይሁን እንጂ እስር ደቂቃ ያህል ቁልቁለቱን እንደተጓዝን ቀለል ያለ የህመም ስሜት ይሰማኝ ጀመር:: በመጀመሪያ



የተሰማኝ በግራ ክንዴ አካባቢ ነበር:: ቀጥሎ ደግሞ የግራ እግሬ ህመም ተሰማኝ:: ራስ ምታቱ ቀጠለ:: በደቂቃዎች ውስጥ የመላው አካሌ ስቃይ ተሰማኝ፤ በተለይ የትኛው ስፍራ ላይ እንደሚያመኝ ለይቼ ማወቅ እስከማልችል ድረስ አካሌ ሁሉ በህመም ይሠቃይ ጀመር:: በመሆኑም ከስቃዩ ለማምለጥ ስል መጮህ ቀጠልኩ:: ጥልቅ የሆነ የህመም ስቃይ ሁለንተናዬን አዳረሰው:: ሰውነቴ ሙሉ በሙሉ የቆሰለ፣ የተቆነጠጠ ወይም እንደተነከሰ ዐይነት ነበር የሚሰማኝ:: ከሰውነቴ አካል በስቃይ የማይጮህ እንዳልነበረ አስባለሁ:: እጮህ እንደነበር እገምታለሁ፤ እርግጠኛ ግን አይደለሁም:: በእያንዳንዱ የልቤ ምት ፍጥነት መላው አካሌ አንዳች በሚያህል መራጃ እንደተፈለጠ ያህል ይሰማኛል::

"እባካችሁ አንድ ነገር ማድረግ አለባችሁ" ስል ልመናዬን አቀረብኩ፣ በመጨረሻው "መድሃኒት ... ወይም የሆነ ... " እስከዚያ የነበረውን ነገር አስታውሣለሁ::

"መስጠት የምችለውን ሁሉ ሰጥቼሃለሁ"

"መስጠት የምትችሉትን ሁሉ ሰጥታችሁኛል?" የተናገረው ቃል ትርጉም የሚሰጥ አልነበረም:: መድሃኒት ሰጥተውኝ ከሆነ ያን ያህል ስቃይ እየተቀበልኩ የነበረው ለምንድን ነበር?

"እባካችሁ ..."

"አዕምሮህን እንድትስት ማድረግ አልችልም" አለ ሃኪሙ::

"አዕምሮህ ንቁ እንደሆነ መቆየት አለበት"

"እባክህ ... አንድ ነገር ... "

በአዕምሮዬ ነቅቼ መቆየት ለምን እንዳስፈለገ ሊገባኝ አልቻለም። አውጥተው ቢወረውሩኝ እንኳን ህመሙ ለቆኝ ይሄድ ነበር። "እባክህ ... " ስል እንደገና ለመንኩት።

"አዝናለሁ። ባደርግልህ ደስ ይለኝ ነበር፣ ነገር ግን ከዚህ በላይ ተጨማሪ ልሰጥህ አልችልም። አንተ የወሰድከውን ያህል መድሃኒት ሰዎች ቢወስዱ ብዙዎቹ ሩሃቸውን ይስታሉ። በአመዛኙ ሲታይ ግዙፍ የምትባል ዐይነት ሰው ነህ፣ ይሁን እንጂ ህሊናህን እንድትስት አልፈልግም። "

በቀረው የጉዟችን ወቅት በስቃይ እንዳጓራሁ፣ እንዳጣጣርኩ ወይም ብዙ ጊዜ እንደጮኩ እርግጠኛ ነኝ። መኪናው በሌሎች ተሽከርካሪዎች መካከል እየተሽሎከለከ ወደፊት ወደኋላ እያለና እየተንገጫገጨ ጉዞውን ቀጠለ፣ የሳይረኑ ድምጽ ያለማቋረጥ ይጮሃል። በሕይወቴ ካደረኳቸው ጉዞዎች ሁሉ ስቃይ የተሞላበትና አስጨናቂው ጉዞ ነበር።

አሁን እንኳን አይኖቼን ጨፈን አድርጌ አንቡላንሱ በዚያ ፍጥነት እየበረረ በኩርባ መንገዶች ላይ ሲተጣጠፍ የነበረውን መንገራገጭ ማስታወስ እችላለሁ። ከሃኪሞቹ አንደኛው የተጨናነቀ የትራፊክ ሰዓት ሲናገር ሰማሁ፣ በመሆኑም ሰዓቱ 11:00 አካባቢ እንደሆነ ገመትኩ። በዚያው ቅጽበት ቀኑ እንዴት እየተንቀረፈፈ ይሄድ እንደ ነበር ገረመኝ።

ጉዞው ፈጽሞ ማለቂያ የሌለው ይመስል ነበር፣ ይሁን እንጂ በህመሙ ምክንያት ብዙ ጊዜ ነፍሴ እየወጣች እንደገና እየተመለሰች እንደነበር እስባለሁ። በመጨረሻው በሀውስተን ውስጥ በሚገኘው



ሄርማነን ሆስፒታል የድንገተኛ አደጋ እርዳታ መስጫ ክፍል ውስጥ ተገኘን።

ሰዓቱ ከምሽቱ 12:20 ደርሶ ነበር። አደጋው ከደረሰ አሁን ስድስት ሰዓት ተኩል ሆኗል ማለት ነው።

በሀውስተን በሚገኘው ሆስፒታል በደረስን ጊዜ በሽህ የሚቆጠሩ ሰዎች በፀሎት ላይ ነበሩ። መልዕክቶች በፍጥነት በመቶዎች ለሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናት ተላልፈው ስለነበር ሰዎች ስለ መዳኔ ይጸልዩ ነበር። ለቀጣዩቹ ጥቂት ቀናት፣ ስለደረሰብኝ የአካል ጉዳት መነገር ስለቀጠለ ብዙ ሰዎች በፀሎት መተባበራቸውን ቀጠሉ። በዓመታት ውስጥ በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር ነፍሴን እንዲታደጋት ሲጸልዩ ከነበሩ ብዙ ሰዎች ጋር ተገናኝቻለሁ። ምናልባትም ይህንን መጽሐፍ በማንበብ ላይ ያላችሁ አንዳንዶቻችሁ በሕይወት ስለመቆየቴና ስለመዳኔ ፀልያችሁ ይሆናል። ፀሎቱ ውጤታማ እንደነበር ጨምሬ መናገር እፈልጋለሁ። በሕይወት ተርፌአለሁ፣ አሁንም እየኖርኩ ነው።

ሀኪሙ የተኛሁበትን ቃሬዛ ከአምቡላንሱ ውስጥ ሲያወጣው፣ የኢቫን ፊት አየሁት። ከእጠገቧ ደግሞ የቤተክርስቲያናችን አንድ ዲያቆን ቆሟል። በታላቅ አግራሞትና ድንጋጤ ውስጥ ነበሩ፣ አንዳች ቃል ግን አልተነፈሱም።

ኢቫ ወደ እኔ አፍጥጣ ትመለከታለች። እስከዚያ ሰዓት ድረስ በሰውነቴ ላይ ስለደረሰው ጉዳት የማውቀው በጥቅሉ ብቻ ነበር። የህመም ስሜቱ አልቀነሰም፣ ያም ቢሆን በእንደዚያ ዐይነት አደጋ ውስጥ መሆኔን ራሴን ለማሳመን አልቻልኩም። እኔን ለመግደል የመጣ አደጋ ሲሆን አይችልም።

ፊቷን ትኩር ብዬ ስመለከታት በአይኗ ውስጥ የነበረውን ስጋትና ሀዘን አስተዋልኩ:: ምናልባትም ልታጽናናኝ የሆነ ነገር ተናግራ ሊሆን ይችላል፤ አላውቅም:: ትዝ የሚለኝ ነገር በሕይወት ይኖራል ብላ ባለማሰቧ በፊቷ ላይ ይነበብ የነበረው የስቃይ ስሜት ነበር::

በዚያ ጊዜ ነበር በሰውነቴ ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ እንደነበረና አካሌም ትክክለኛ ቅርጽን እንዳልያዘ ማወቅ የጀመርኩት ደረቴ ወደ ግራጫነት ተለውጧል፤ ሃኪሞቹ አብዛኛውን የሰውነቴን ክፍል በፋሻ ጠቅልለውታል:: ደቃቅ የጠርሙስ ስብርባሪዎች በፊቴ በደረቴና በጭንቅላቴ ውስጥ ዘልቀው ገብተዋል:: እነኚህ ደቃቅ የጠርሙስ ስብርባሪዎች ከቆዳዬ ላይ እየተራገፉ በቃሬዛው ላይ ከጭንቅላቴ አጠገብ ሲበታተኑ አወቅኩ::

በአስቀያሚ ሁኔታ ውስጥ እንደነበርኩ የነገረኝ ሰው አልነበረም:: ያውቀኝ የነበረው ሰው በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ እኔ እንደሆንኩ ሊለየኝ አይችልም:: ኢቫ ራሷ እኔ እንደሆንኩ እንዴት እንዳወቀችኝ ይገርመኛል::

የስቃይ ስሜቱ ወሰኑን ያለፈ ነበር:: በድንገተኛ አደጋ ህሙማን ክፍል ውስጥ ነርሷ አንድ ጊዜ ሞርፊን የተባለ መድሃኒት ወጋችኝ፤ ከዚያ በኋላ ደግሞ በተከታታይ መድሃኒቶችን ተወጋሁ:: የረዳኝ ነገር አልነበረም:: ስቃዩን ሊያስዝበው የሚችል ነገር አልነበረም::

በሂርማነን ሆስፒታል በገባሁ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደ ቀዶ ጥገና ህክምናው ክፍል በአጣዳፊ ተላኩ፤ በዚያ ክፍል ውስጥ ለአሥራ አንድ ሰዓታት ቆይቻለሁ::



የተወዳደው ጓደኞችን ክሊፍ ማክአርድል ቀሪውን ምሽት ከኢቫ ጋር በሆስፒታሉ ቆየ:: ክሊፍ፣ የቅርብ ጓደኛዬ ዴቪድ ጀንቲልስና እኔ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ከተመረቅን በኋላ የቅርብ የአገልግሎት አጋሮች ሆነን እስከ አሁን ድረስ አለን::

እንደገና ወደ አዕምሮዬ በተመለስኩ ጊዜ፤ ሐሙስ ጠዋት ሆኗል:: አይኖቼን ስገልጽ በዚያ አዲስ የህክምና ክፍል ውስጥ ስመታከም የመጀመሪያው ህመምተኛ እኔ መሆኔን አወቅኩ:: አንደኛዋ ነርስ ቁስሌን እያጸዳች ነበር፤ ሌላዋ ደግሞ ሰውነቴ እንዲፈታታ እያደረገች ነበር:: የሆነ ረዥም ብረት በቁርጭምጭሚቴና በክንዴ መካከል ስትከት አስታውሳለሁ:: ስጮህ ራሴን አዳመጥኩት::

"የቀዶ ጥገና ህክምናውን አከናውነናል" አለ ዶክተሩ:: እስከተናገረበት ጊዜ በክፍሉ ውስጥ መኖሩን አላስተዋልኩም:: በጣም ከባድ ጉዳት ነበር የደረሰብህ፣ አስደሳቹ ዜና ግን በጭንቅላትህም ይሁን በመተንፈሻ አካልህ ላይ የደረሰ ጉዳት የለም::

በዚያ ጊዜ ጉዳቱ በየትኛው አካሌ ላይ መድረሱ ግድ የሚሰጠኝ አልነበረም:: አስጨናቂው ህመም በሠራ አካላቴ ሁሉ ላይ ተሰራጭቷል:: ሰው ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ የሆነውን ስቃይ እየተቀበልኩ እንደሆነ አሰባለሁ::

ከዚህ ሥቃይ መገላገልን ፈለግኩ::

ከአደጋው በኋላ ሁለት ሳምንት ቆይቶ፤ ዲክ ዋንሪከር ሊጎበኘን ወደ እኔ በመጣ ጊዜ፤ ከቀዶ ጥገናው ክፍል ገና ወደ ሆስፒታሉ መኝታ

ክፍል እየተዘዋወርኩ ነበር። እግዚአብሔር፣ እንዲጸልይልኝ እንደተናገረውና ይህንንም ደጋግሞ እንዳደረገው ነገረኝ።

"እጅግ አስደሳቹ ዜና የአንጎልም ይሁን የሌሎች ውስጣዊ አካላት ጉዳት በፍጹም አልደረሰብኝም" አልኩት።

ዲክ ትከሻውን ሰበቀና፤ "በእርግጥ ሊደርስብህ አይችልም፤ እግዚአብሔር እንድጸልይልህ ይናገረኝ የነበረው ለውስጥ አካልህ ክፍሎች ነበር፤ እናም እግዚአብሔር ያንን ጸሎት መልሷል" አለ።

"ያንን አምነህ ነበር? እግዚአብሔር ያንን ጸሎት እንደሚመልስ አምነህ ነበር?"

"አዎን አምኜ ነበር" አለ። "ያጋጠሙህን እነኛን ጉዳቶች ሁሉ ለማስተካከል፤ እግዚአብሔር ጸሎቴን እንደሚመልስ አውቅ ነበር።"

እየተናገረ ያለውን ነገር በአግባቡ ለመገንዘብ ጥቂት ሰከንዶች ወስዶብኝ ነበር። በአደጋው ጊዜ ከተፈጠረው ሃይልና ሃይሉም ከፈጠረው ግፊት አኳያ፤ ውስጣዊ የአካል ክፍሎቼ ጉዳት ሊደርስባቸው ይገባ ነበር። ዶክተሩ እንኳን በመደነቅ የጭንቅላትም ይሁን የመተንፈሻ አካላት ጉዳት እንዳልደረሰብኝ ተናግሯል።

"ይህንን ልነግርህ እፈልጋለሁ" አልኩት። "የውስጥ አካል ጉዳት እንደነበረኝ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ ከድልድዩ አንስቶ እስከዚህ ሆስፒታል መካከል ባለ በአንድ ስፍራ ላይ ያ ጉዳት ከእኔ ተወግዷል።"

በዲክ ፊት ላይ እንባ ዘለላዎች መውረድ ጀመሩ፤ "አውቃለሁ። በአደጋው ጊዜ እንደጸለይኩበት ባለ ሁኔታ ሁሉ ጊዜም ለመጸለይ እመኛለሁ" አለኝ።



# 6 እየተሻለኝ መጣ

"በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማን ብናውቅ ከእርሱ የለመንነውን ልመና እንደተቀበልን እናውቃለን።"

1ዮሐ 5፥14-15

የህመም ስሜት የማይለየኝ ጓደኛ ሆነኝ። ለረዥም ጊዜ ምን እንደሆነ አላውቀውም ነበር፤ እንዲህ ሰውነቴ ሁሉ በስቃይ ይጠቃል ብዬ አስቤውም አላውቅም።

ከዚህም ሁሉ ጋር፤ አደጋው በደረሰ በጥቂት ቀናት ውስጥ፣ ምን ያህል ተአምራቶች እንደተከናወኑ መገንዘብ ጀመርኩ። አንዳንዶች እንደ እድል አጋጣሚዎች ቢቆጥሯቸውም፤ እኔ ግን ተዓምራት ነው የምላቸው። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ አጋጣሚም ይሁን ድንገት የሚሆኑ ነገሮች እንደሌሉ አምናለሁ።

በመጀመሪያ ደረጃ፤ የአደጋ ጊዜ መከላከያ ቀበቶዬን አጥልቄአለሁ። ትራፊክ የመቀጫ ደረሰኝ እስከቆረጠልኝ ቀን ድረስ፤ ያንን ቀበቶ ለማጥለቅ እጅግም የማልጨነቅ እንደነበር ከሃፍረት ጋር ስህተቴን እቀበላለሁ። በዚያ ቀን ጠዋት ሆን ብዬ በቀበቶው ራሴን አስሬአለሁ።

በሁለተኛ ደረጃ፤ አደጋው የተከሰተው በድልድዩ ላይ ነው። ወደ ድልድዩ ስጓዝ በሃይቁ መካከል ባለው መንገድ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮስ? መኪናዋ እየተንከባለለች ቢያንስ ቢያንስ ሰላሳ ጫማ ያህል ተወርውራ ወደ ሃይቁ ትገባለች፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ መስጠሜ አይቀሬ ነበር።

ሦስተኛ፤ በጭንቅላቴ ላይ ጉዳት አልደረሰም። እኔን የተመለከተና የህክምና ሪፖርቱን ያነበበ ማንም ሰው፤ የአዕምሮ ጉዳት ሳይደርስብኝ ይቀራል ብሎ በጭራሽ አይገምትም። (ኢቫ አሁን ድረስ፤ ይህ አይነቱ ጉዳት አልደረሰብህም ብዬ ያስብኩበት ጊዜ የለም እያለች ትቀልዳለች) ምንም እንኳን ጉዳዩ ለህክምናው ዓለም ሰዎች ግራ የሚያገባ ቢሆንም፤ አደጋው አንዳችም የውስጥ አካል ጉዳት አላደረሰብኝም። ይህ እውነት በህክምናው ዓለም ምክንያት የሚሰጥበት አልነበረም።

በአራተኛ ደረጃ፤ በአደጋው ዕለት ሂርማነን ሆስፒታል ውስጥ ተረኛ የነበሩት የአጥንት ህክምና ባለሞያ ዶ/ር ቶም ግሪደር ነበሩ እግሬ እንዲተርፍ ያደረጉት። እኚህ ሰው በአሜሪካ ምድር ካሉ እንዲህ ያለውን ጥልቅና ውስብስብ ጉዳት ለማከም ብቃቱ ካላቸው ባለሙያዎች ጎራ እየተቀላቀሉ ያሉ ሰው ናቸው። በጊዜው አዲስ የሆነውን ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘውን አዲስ የህክምና ዘዴ ለመጠቀም ነበር የመረጡት። የቀዶ ጥገናውን ህክምና የጀመሩት ከአደጋው አንድ ሳምንት በኋላ ነበር። በስጋዬ ውስጥ የተቀበረው ኤልዛሮቭ የተሰኘው ቁስ እግሬን እንዲድን ብቻ አልነበረም የረዳው፤ ይልቁንም በአደጋው ጊዜ አራት ኢንች ያህል ተጎርዶ የጠፋው የግራ እግሬ ፊምዮር የተሰኘ አጥንት አካል እንዲረዝምና ስፍራውን እንዲይዝ አድርጎታል። ፊምዮር በሰውነታችን ውስጥ ከሚገኙ አጥንቶች ሁሉ ትልቁና ለመሰበርም በጣም አስቸጋሪ የሆነው ነው።



ዶ/ር ግሪደር በመረመሩኝ ጊዜ፤ ምርጫ ነበራቸው። አንድም ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘውን ህክምና ጥበብ መጠቀም፤ ካልሆነም እግሬን ቆርጦ ማስወገድ። ምንም እንኳን የመጀመሪያውን አማራጭ ቢጠቀሙም እግሬን ላለማጣቴ ግን አስተማማኝ ሁኔታ አልነበረም። እንደእውነቱ ከሆነ በዚያ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ልተርፍ እንደምችል እርግጠኛ አልነበሩም። እጅግም ልምድ የሌለውና ትጋት አልባ የሆነ ዶ/ር ቢሆን ኖሮ እግሬን ቆርጦ ያስወግደው ነበር። ምክንያቱም ፈጥኖም ሆኖ ዘግይቶ መሞቱ አይቀርም ብሎ ስለሚገምት ለእርሱ ብዙ ልዩነት አያመጣም።

በአምስተኛ ደረጃ፤ ሰዎች ለእኔ ይጸልዩ ነበር። አደጋው በደረሰ ጊዜ ወሬውን የሰሙ በርካታ ሰዎች በወቅቱ ይደልዩልኝ እንደ ነበር የሚገልጹ በሺህ የሚቆጠሩ ካርዶችንና ደብዳቤዎችን ልከውልኛል፤ አብዛኞቹን ሰዎች አላውቃቸውም። የመኖሪያ ስፍራዎቻቸውንም ረግጬው አላውቅም። ብዙ ሰዎችም ይህ ተግባራቸው የፀሎት ሕይወታቸውንና በጸሎት ኃይል ያላቸውን እምነት እንደለወጠው ነግረውኛል።

ወደ ሂርማነን የድንገተኛ አደጋ ማዕከል ውስጥ በገባሁበት ምሽት አሥራ አንድ ሰዓት የፈጀ የቀዶ ጥገና ህክምና ተደርጎልኛል። በዚያ ህክምና ወቅት፤ በቀኝ እግሬ ላይ የተሰበረ አጥንት ነበር። የግራ እጄ የመጀመሪያው አንጓ እንደገና መስተካከል ያስፈልገው ነበር፤ ምክንያቱም ከሁለቱም አጥንቶቼ ላይ ሁለት ኢንች የሚያህሉ አጥንቶች ተጎምደው ጠፍተዋል። የግራ እግሬ አጥንቴ መወጠር ያስፈልገው ነበር፤ ምክንያቱም ፊሚዮር ከተባለው የአጥንት ክፍል አራት ተኩል ኢንች ተጎርዶ ጠፍቷል። በቀዶ ጥገና ጊዜም አንድ የአየር መስጫ የላስቲክ ቱቦ

በስህተት ወደ ሆድ እቃዬ ውስጥ ተጨምሮ ነበር። ይሄ ደግሞ ሆዴ ውስጥ አየር እንዲጠራቀም፣ እንዲነፋ፣ ሳንባዬ ደግሞ አየር ቶሎ ቶሎ እንዲተነፍስ አደረገው። የሆዴ ማበጥ ምክንያቱ ይህ መሆኑን ለመገንዘብ በርካታ ቀኖች ፈጅተውባቸዋል። ከዚህም የከፋው ነገር ደግሞ ተከስቶ ነበር፤ ይህም በአተነፋፈሴ ለይ የተፈጠረ ችግር ሲሆን አየር መሳብ አልቻልኩም፤ በመሆኑም ኒሞኒያ በተሰኘ የሳንባ በሽታ ተለከፍኩ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ከመሞት ያመለጥኩት ለጥቂት ነው።

ከቅጥቅጡና በግልጽ ከሚታየው ቁስል ብዛት የተነሣ ዶክተሮቼ ሥራቸውን ከየት እንደሚጀምሩ እንኳን በውል አላወቁም ነበር። እጅግም ጉዳት የማያስከትሉ ችግሮች የታወቁት ከሳምንታት በኋላ ነበር። በመጀመሪያ ላይ ያላገኙትን በብራኳዬ ላይ ያለ ስንጥቅ ያገኙት ከብዙ ዓመታት በኋላ ነበር።

መላው አካሌ ከጥቅም ውጭ ሆኖ በአልጋ ላይ ተጋደምኩ፤ መንቀሳቀስ አልችልም፤ የሰውነትን አካል ሰብስቦና ደግፎ በሚይዝ መሣሪያ ብርታት ነው ያለሁት። ካጠለቅኩት የኦክስጅን ጭንብል በስቲያ አሻግሬ የማየው በመጠኑ ነበር። በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ በነበርኩባቸው በእነዚያ ቀናት ህሊናዬን አሁንም አሁንም እስት ነበር። አንዳንድ ጊዜ ስነቃ ሰዎች ከፊት ለፊቴ ቆመው እመለከትና እገረማለሁ፤ እስከ አሁንም እዚሁ ነኝ ወይስ ዝም ብዬ በሃሣቤ የምፈጥረው ቅዠት ነው?

የህክምና ተቆጣጣሪዎች አዘውትረው ከበውኝ ይቆማሉ? በጣቴ ላይ የተሰካው የደም ግፊት መለኪያ መሣሪያ የኦክስጅኑን መጠን ያመላክታል። በቂ ኦክስጅን የማላገኝ ስለነበር፤ ብዙውን ጊዜ



የማስጠንቀቂያው ድምጽ ይጮህ ነበር፤ በመሆኑም ነርሶቹ እየሮጡ ወደ ክፍሌ ይመጣሉ።

የሂርማነን ሆስፒታል ከሄሊኮፕተር አየር ጣቢያ አቅራቢያ የተሠራ በመሆኑ ሄሊኮፕተሮች ቀኑን ሙሉ ሲነሱና ሲያርፉ ይውላሉ። ከስመመኔ ነቅቼ ይህንን ድምጽ ስሰማ የቪየትናምን ጦርነት ፊልም እየተመለከትኩ እንደሆነ ይሰማኛል። በክፍሉ ውስጥ ሰዓት አልነበረም፤ እናም ስለ ጊዜ ምንም አይነት ግንዛቤ አልነበረንም።

እጠገቤ ባሉ አልጋዎች ላይ ሌሎች ሰዎች ተኝተዋል፤ አልጋዎቻችን የተከለሉት ከመጋረጃ ባልወፈረ ነገር ነው። ከአንድ ጊዜ በላይ ነቅቼ የህክምና ሰዎች ነጭ አንሶላ የተሸፈነ አካል በቃሬዛው ላይ አስተኝተው ሲያወጡ ተመልክቻለሁ። እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ ከአደጋ የቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ብዙዎች በሕይወት አይወጡም።

ቀጣዩ ሰው እኔ እሆን? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ። ምንም እንኳን ጥያቄውን ብጠይቅም፤ የህመም ስቃዩ ከሃሳቤ ያናጥበኛል። ጉዳቱን አልፈለግኩትም፤ እናም ቀላሉና ፈጣኑ መልስ መሞት ነበር።

መንግስተ ሰማይን ተመልክቻለሁ፤ ወደ ምድር ተመልሻለሁ እናም ፈጽሜ በማልፈልገው የምድር ገሃነም በሆነ ስቃይ ውስጥ ገብቻለሁ። የነበርኩበት ሁኔታና የነበረኝ አመለካከት ሊለወጥ ረዥም ጊዜ ወስዷል።

የቅዠት ድምጾች ቀናትንና ሌሊቱን ሙሉ ሳያቋርጡ ይሰሙኛል። የጣር፣ የሰቆቃና የጭንቀት ጩኸት ያለማቋረጥ ከእረፍቴ ይቀሰቅሱኛል፤ ወደ አዕምሮዬም መልሰው ያመጡኛል። ነርሷ ወደ አልጋዬ ትቀርብና፤ "ልረዳህ እችላለሁ?" ትላለች።

"ስለ ምን ጉዳይ ነው የምታወሪው?" ብዬ እጠይቃታለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ዝም ብዬ አተኩሬ እመለከታታለሁ፤ ለምን እንደምትጠይቀኝ ሊገባኝ ከቶ አይችልም::

"የምታሰማው ድምጽ ታላቅ ስቃይ ውስጥ እንዳለህ ያስረዳል"::

"አዎን ነኝ፤ ይመስለኛልም፤" ከዚያ በኋላ እንዲህ ስል እጠይቃለሁ፤ "ይህንን ግን እንዴት ልታውቂ ቻልሽ?"

"ትጮህ ነበር"

በዚህ ጊዜ ነበር አንዳንድ ጊዜ የምሰማው የጩኸት ድምጽ ከራሴ የሚወጣ እንደነበር የተረዳሁት::

እነኝህ የጣርና የጭንቀት ድምጾች እየተፈተለኩ የሚወጡት፤ ቀላል የሆኑ እንቅስቃሴዎች ሳደርግ ለምሳሌም እጆቼንና እግሮቼን ማንቃነቅ በጀመርኩት ጊዜ ነበር:: በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ መኖር እጅግ ዘግናኝ ነው:: ማድረግ የሚችሉትን ነገር ሁሉ ያደርጉልሃል፤ ይሁን እንጂ የህመም ስሜቱ ፈጽሞ አይቆምም::

"እግዚአብሔር ሆይ ለዚህ ነው ተመልሼ የመጣሁት?" እያልኩ ብዙ ጊዜ ጮኬአለሁ:: "ወደ ምድር መልሰህ ያመጣኸኝ ለዚህ ነው?"

ሁኔታዬ ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ ወደሆነ አዘቅት እየወረደ መጣ:: ከግራ እግሬ ላይ በጎደለው አጥንት ምክንያት በአልጋው ላይ በጀርባዬ ለጥ ብዬ መተኛት ነበረብኝ:: (አጥንቱን ፈልገው አላገኙትም:: በአደጋው ወቅት እግሬ በመቀመጫውና በዳሽ ቦርዱ መካከል ገብቶ በተጨፈለቀ ጊዜ ከመኪናው ውስጥ ተፈናጥሮ በሃይቁ ውስጥ ለመግባቱ ጥርጥር የለውም):: በጀርባዬ ለጥ ብዬ በመተኛቴ ሳንባዎቼ በፈሳሽ ይሞሉ



ጀመር:: አሁንም እንኳን ሳንባዎቼ ሥራ አቁመው እንደነበር አልተገነዘብኩም፤ ነርሶቹና የመተንፈሻ አካል ሃኪሞቹ አተነፋፈሴን ለማስተካከል ስፖይሮ ሜትር የተሰኘ ትልቅ መሣሪያ በመጠቀም በኃይል እንድተነፍስ ይረዱኝ ነበር::

በስድስተኛው ቀኑ ላይ፤ ፈጽሞ ለሞት እየታቀረብኩ ስለመጣሁ፤ ሆስፒታሉ ቤተሰቦቼ መጥተው እንዲያዩኝ ጥሪ አደረጉላቸው:: የሳንባ ምች በሽታ በእጥፍ እየጨመረ ሄደ:: ሀኪሞቹ ያችን ሌሊት በሕይወት ኖሬ የማድር አልመሰላቸውም::

በአደጋው ምክንያት ከደረሰብኝ ጉዳት ከሞት ተርፌአለሁ፤ አሁን ደግሞ በሳንባ ምቹ ምክንያት ልሞት ነው::

ዶክተሬ ኢቫን አነጋገራት::

"አንድ ነገር የግድ ማድረግ አለብን" አላት ዶክተሩ:: "አንድም እግሩን ቆርጠን ማስወገድ አለዚያም እንድ ታላቅ ጥረት"

"እንዴት ያለ ታላቅ ጥረት?"

"አንድ ነገር ካላደረግን፤ ማለዳ ላይ ባልሽ በሕይወት የለም":: በዚያ ሰዓት ነበር የጸሎት ተአምራት በእውነት መሥራት የጀመረው:: አደጋውን ከሰሙበት ጊዜ ጀምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እየጸለዩልኝ ነበር፤ ያንንም አውቄአለሁ:: ይሁን እንጂ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ምንም ነገር ልዩነት የሚያመጣ አልነበረም::

ኢቫ እጅግ የቅርብ ጓደኛዬ የሆነውን ዴቪድ ጀንትልስን ጠራችው፤ በሳን አንቶኒዬ ቤተክርስቲያን በመጋቢነት ያገለግላል:: "እባክህ

እንድ ጊዜ ብቅ በል፤ ዶን ይፈልግሃል" የሚል መልዕክት አስተላለፈችለት::

ያለ ምንም ማቅማማት ጓደኛዬ ጉዳዮን ሁሉ ሰርዞ ወደ መኪና ውስጥ ዘሎ ገባ:: ሁለት መቶ ማይሎች የሚያህል መንገድ ተጉዞ ሊያየኝ መጣ:: የህክምና ባለሙያዎቹ በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ እንዲቆይ የፈቀዱለት አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር::

እነኛ ደቂቃዎች ሕይወቴን ቀየሩት::

ይህንን ውሳኔ የወሰንኩት ሆነ ብዬ አልነበረም፤ ነገር ግን ለመዳን ጥቂት ተስፋ ብቻ ቀርቶኝ በተኛሁበት በዚያ ሥፍራ እኔም ብቻ ሳልሆን ማንም ሰው እንደገና ወደ ጤንነቱ ይመለሳል ብሎ ተስፋ አላደረገም:: ለመኖር ፍላጎት አልነበረኝም:: ማለቂያ ማብቂያ የሌለውን ሥቃይ ብቻ አልነበረም ያየሁት፤ በመንግስተ ሰማይ ውስጥም ነበርኩ:: ታላቅ ፍጹምነት ወደተቀዳጀው ወደዚያ ሥፍራ ለመመለስ ፈለኩ:: "እግዚአብሔር ሆይ እንደገና መልሰኝ" ስል ጸለይኩ፤ "እባክህ መልሰህ ውሰደኝ::"

ትዝታዎች አዕምሮዬን ይሞሉት ጀመር፤ እናም እንደገና አንድ ጊዜ በዚያ በር ላይ ለመቆም ውስጤ ተነሣሣ:: "እባክህ እግዚአብሔር ሆይ!?"

ለጸሎቴ እግዚአብሔር የሰጠው ምላሽ፤ "አይሆንም" የሚል ነበር::

ዴቪድ የተኛሁበትን ክፍል በር ከፍቶ ሲገባ፤ ከህመሙ ስቃይና ከመድሃኒቱ ሃይል የተነሣ ብዥታ ውስጥ ነበርኩኝ:: የማየው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ መጀመሪያ ከሰመመን ውስጥ ወጥቼ



ትኩረቴን በነገሩ ላይ አደርግ ነበር:: እየቃዠሁኝ ነውን? ስል ራሴን ጠየቅኩ::

ከዚያ በኋላ ዴቪድ ጣቶቼን ከፍ አድርጎ አነሣቸው፤ እናም መነካቴን አወቅኩ:: አዎ በርግጥ ቅዥት ሳይሆን እውን ነበር::

ጣቶቼን ጨብጦ ያዛቸው፣ ምክንያቱም መያዝ የሚችለው የሰውነቴ አካል እርሱን ብቻ ነበር:: የደም ሥሮቼ እስኪኮራመቱ ድረስ በርካታ መርፌዎች በላዩ ላይ ተሰክተዋል፤ ረዘም ያለ የላስቲክ ቱቦ በደረቴ አልፎ በቀጥታ ከልቤ ጋር ተገናኝቷል:: እንደ ወታደር የተሰለፉት በመርፌ ወደ ሰውነቴ የሚላኩት መድሃኒቶች ይታወሱኛል:: መድሃኒቶቹ በእግሬ መዳፍ የላይኛው ክፍል ሳይቀር ይለቀቁልኝ ነበር:: ቁልቁል እየተመለከትኩ በእግሬ መዳፎች ላይ መርፌዎቹን የተከሏቸው ከሰውነቴ ክፍል ውስጥ ነፃ የሆነ ሥፍራ ባለማግኘታቸው ምክንያት እንደሆነ እገነዘባለሁ::

"እየተቋቋምከው ነው" አለ ዴቪድ:: "መቋቋምም አለብህ፤ እስከዚህ ሰዓት ድረስ ተቋቁመኸዋል::"

"ከዚህ በላይ መቋቋም አልችልም:: በፍጹም እርግጠኛ አይደለሁም ... መቋቋም መፈለጌን እንኳን እርግጠኛ አይደለሁም::"

"መቋቋም አለብህ:: ለራስህ እንኳን ብለህ ሳይሆን፤ ስለ እኛ ብለህ አድርገው"

"ኃይሌ ከውስጡ እያለቀ ነው" አልኩት:: "ማድረግ የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ:: ማድረግ ባለብኝ አቅም ሁሉ አድርጌአለሁ:: አሁን መቋቋም የምችልበት እንዳች አቅም የለኝም" አረፍ አልኩና ደጋግሜ

አየር ሳብኩ፤ ሁለት ቃላት ለመናገር እንኳን በርካታ ሃይል ያስፈልግ ነበር።

"መበርታት መቻል አለብህ፤ እንድትሄድ አንፈቅድልህም"

"መቋቋም ካለብኝ፤ እናንተ ሁላችሁ ስለፈለጋችሁ ብቻ ነው። እኔ አልፈልገውም። በጣም ታክቶኛል። ባለኝ ጉልበት ሁሉ ታግያለሁ እናም አሁን ግን ለመሞት ዝግጁ ነኝ"

"ደህና፤ አሁን አንተ ምንም ማድረግ አይጠበቅብህም። ስለ አንተ እኛ ሁሉን እናደርጋለን። "

መግለጽ በሚያዳግተኝ ሁኔታ፤ በፊቱ ላይ በሚታየው የብርታት ስሜት ላይ አፈጠጥኩ።

"እንድትሞት አንፈቅድልህም። ይህንን ትረዳዋለህ ዶን? ተስፋ እንድትቆርጥ አንፈቅድልህም።"

"እባካችሁ እንድሄድ ተውኝ?!"

"በፍጹም በሕይወት መኖር አለብህ! ይህንን ትሰማለህ? መኖር አለብህ። እንድትሞት አንፈቅድም። "

"መኖር ካለብኝ . . ." በመጨረሻው እንዲህ አልኩ፤ ምክንያቱ እናንተ ስለፈለጋችሁ ብቻ ነው።

"እንጸልይልሃለን " አለ። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰዎች አሁንም እየጸለዩልኝ እንደሆነ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ እንዲህ የሚል ቃል ጨምሮ ተናገረ፤ "ሌሊቱን ሙሉ ስንጸልይልህ ነው የምናድረው። የማውቃቸውን መጸለይ የሚችሉ ሰዎች ሁሉ አጠራለሁ። አንድ ነገር



እንድታውቅ እፈልጋለሁ፤ ስለ አንተ ግድ የሚለን ሰዎች ሁሉ ሌሊቱን ሙሉ ስለ አንተ ስንጸልይ እናነጋለን። "

"መልካም"

ይህንን የምናደርገው ስለ አንተ ስንል ነው ዶን። አንተ የምታደርገው አንዳች ነገር የለም። "

እንደ እውነቱ ከሆነ ቢጸልዩልኝም ባይጸልዩልኝም ግድ አልነበረኝም። እጅጉን ተጎድቻለሁ፤ በሕይወት መኖር አልፈለኩም ነበር።

"ከዚህ ሆነን መነጋገር እንችላለን፤ በሕይወት ለመቆየት ምንም ነገር ማድረግ አያስፈልግህም፣ አንዳች ነገር። ማድረግ የሚገባህ ነገር ቢኖር እዚያው እንደተኛህ ነገሮቹ እንዲፈጸሙ ፍቀድ። በዚህ ሁኔታ እኛ ስለ አንተ እንጸልያለን። "

ለአንድና ለሁለት ደቂቃዎች ያህል በፍጥነት አነጋገረኝ። ከዚያ በላይ የተናገርኩ አይመስለኝም። የህመም ስሜቱ እየጨመረ ሄደ፤ ይህ ቃል ሁኔታውን ገላጭ ከሆነ እናም ከዚያ በኋላ በተናገረው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ አልቻልኩም።

"ይህንን እኛ እንወጣዋለን" አለና ከግንባሬ ላይ ስሞኝ ወጣ። የሙሉ ሌሊት የጸሎት ተጋድሎ ሊያደርግ እርግጥ ነበር። ያ የጸሎት ተጋድሎ በህክምናዬ ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ አስከተለ፤ እናም ሌላ ተአምራቶች ደግሞ ተከታተሉ።

የሳንባ ምች በሽታው በሚቀጥለው ቀን ጠፋ። በጸሎታቸው ከእኔ እንዲነቀል ጠይቀው ነበር። እንደገናም የህክምና ቡድኑ በመተንፈሻ ቱቦዬ ላይ የነበረውን ችግር ምክንያት ደረሱበት።

በዚያ በሰባተኛው ቀን ዕለት፤ ረዥም ሰዓት በፈጀ የቀዶ ጥገና ህክምና ዶ/ር ግሪደር፣ ኤልዛሮብ የተሰኘውን የህክምና መሣሪያ በእግሬ ላይ መግጠም በመቻሉ ቁጭ ብዬ የመተንፈሻ አካል ህክምናዬን መከታታል ቻልኩ:: በተጨማሪም በሆዴ ውስጥ የነበረውን አየር አስወጡልኝ፤ ይህም ሳንባዎቼ አየር መሳብ እንዲችሉ ረዳቸው::

አግባብነት ባለው አሠራር፤ ሆስፒታሎች ኤልዛሮብ ፍሬም የተሰኘውን የህክምና መገልገያ መሣሪያ ለመጠቀም ቢያንስ የስድስት ወር ምክር ይሰጣሉ:: በእኔ ጉዳይ ግን፤ የህክምና ባለሙያዎቹ የሙከራ ተግባሩ ውጤታማ እንደሚሆን ምንም ዓይነት ዋስትና አልሰጧትም:: በተጨማሪም ይህንን የህክምና መገልገያ መሣሪያ ብጠቀም የተወሰነ የአካል ስቃይና ያልተለመደ ስሜታዊና ሥነልቡናዊ ቀውስ ሊያስከትልብኝ እንደሚችል ነግረዋታል:: እጅግ ተስፋ አስቆራጩ ነገር ደግሞ በዚህ ሁሉ ውስብሰብ የህክምና ሂደት ካለፍኩ በኋላ እንኳን እግሬን ላጣ እንደምችል የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ነበር::

“ይህ በጣም ስቃይ የሚያስከትል ህክምና ነው፤ ደግሞም ለመዳን ወራት ምናልባትም ዓመታት ያስፈልጋል” አላት ሃኪሙ ኢቫን:: እንደገናም ሊደርስ የሚችለውን የመጨረሻውን ከባድ አደጋ ሲያስረዳት፤ እንዲህም ሆኖ እግሬ ሊቆረጥ እንደሚችል አሳሰባት:: “ይሁን እንጂ በዚህኛው የህክምና መንገድ መሄድ የማንፈልግ ከሆነ፤ ሌላ ምርጫ አልነበረንም-መቆረጥ ብቻ::”

እግሬን የምቆርጡት ከሆነ ሌላ ተስማሚ ሰው ሠራሽ እግር እንደሚገጥሙልኝና በርሱም መሄድ እንደምለማመድ በዝግታ ገለጻ አደረገ::





ዶን፣ በአጥንት አስረዛሚው በኤልዛሮብ መሣሪያ ውስጥ ሆኖ::

ኢሻ በእኔ ላይ የደረሰው አደጋ ከባድ እንደሆነ ጥርጥር አልነበራትም ወይም በዚህ አስቸጋሪ ሥቃይ ውስጥ ምን ያህል ጸንቼ መቆየት እንደምችል አታውቅም። በርካታ ጊዜ በጉዳዩ ላይ አወጣች አወረደች፤ እግዚአብሔር ምሪትን እንዲሰጣትም በውስጧ መጸለዩን ቀጠለች። በመጨረሻውም፤ የስምምነት ቅጹን እፈርማለሁ አለች።

በሚቀጥለው ሳምንት፤ ከሌላ አሥራ ሁለት ሰዓት ከፈጀ ህክምና በኋላ ስነቃ፤ የቀኝ እግሬ ባለበት በኩል ከለበስኩት ነገር በታች ትልቅ እብጠት የሚመስል ነገር ተመለከትኩ። እግሬን ገልጬ ስመለከት፤ ያየሁት ነገር ትንፋሼን በእጭር ቆረጠው። በግራ እግሬ ላይ አንዳች የሚያክል ከማይዝግ ብረት የተሠራ ክብነት ያለው መሣሪያ ከሙሃይቴ ጀምሮ ከጉልበቴ ዝቅ ብሎ እስከሚገኝ ሥፍራ ድረስ ተገጥሟል። ነርሷ ወደ ክፍሉ ገባችና ዙሪያውን መዞር ጀመረች፤ በእግሬ አካባቢ የሆነ ነገር እየሠራች ነበር፤ ምን ታደርግ እንደነበር ግን እርግጠኛ አልነበርኩም።

ኢሻ ከአልጋዬ አጠገብ ተቀምጣ እንደነበር አስተዋልኩ። "ይህ ደግሞ ምንድን ነው? ስል ጠየኳት። ምን እያደረገች ነው?"

"በዚህ ነገር ላይ መነጋገር ያስፈልገናል" አለች። "ትላንትና ተስማምቼ የፈረምኩት ይህ እንዲሆን ነው። አጥንት እያደገ እንዲሄድ የሚያደርግ መሣሪያ ነው። ፊክሳተር ተብሎ ነው የሚጠራው። ሃኪሞቹ የግራ እግርህን ለማቆየት ያላቸው የመጨረሻ እድል ይሄው ብቻ ነው" አለች። በመቀጠልም፤ "ሃላፊነቱን መውሰድ የግድ እንደሆነ አምናለሁ" ስትል ተናገረች።



መልስ ለመስጠቴም እርግጠኛ አልነበርኩም። ለመናገርስ ምን የቀረ ነገር ነበር? መወሰን የምትችለውን በጣም ጥሩ ውሳኔ ወስናለች፤ ብቻዋን እንድትወስንም ተገዳ ነበር።

ከዚያ በኋላ ደግሞ ከመሣሪያው የሚወጡ በርካታ የኤሌክትሪክ ገመዶችን ተመለከትኩ። "እነኝህ ገመዶች ሁሉ በእግሬ ውስጥ የሚያልፉ ናቸው?"

"አዎን"

ሳላውቀው ራሴን በሃዘኔታ ወዘወዝኩት፤ "በርግጥ በእግሬ ውስጥ የሚያልፉ ገመዶች ናቸው?"

"አዲስ የህክምና ዘዴ ነው። እግርህን ከመቆረጥ ለማትረፍ እየሞከሩ ነው።"

ከዚያ በኋላ አስተያየት ለመስጠት እውቀቱ አልነበረኝም። ራሴን በመስማማት አይነት ነቀነቅኩና ዘና ለማለት ሞከርኩ።

"እንደሚሠራ አምናለሁ።" አለች።

ትክክል እንደነበረች ተስፋ አደረግኩ። ዓመት ሊሞላ ጥቂት ሲጎድለው ጊዜ ያህል መሣሪያው በሰውነቴ ላይ እንደሚሆን ግን በጊዜው የነበረኝ እውቀት ጥቂት ነበር።

# 7

# ውሳኔና ተግዳሮቶች

“ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት፣ ወይስ ፍርሃት ወይስ ሰይፍ ነውን? ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፤ እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን ተብሎ እንደተጻፈው ነው።”

1ዮሐ 8፥35-36

በአካል ከደረሰብኝ ጉዳት በተጨማሪ፤ እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑብኝ ሁኔታዎች አንዱ፤ በቤተሰቦቼና በቅርብ ጓደኞቼ ፊት ላይ እመለከተው የነበረው የድንጋጤና የሃዘን ስሜት ነው። ወላጆቼ ከሂውስተን 250 ማይል ርቃ በምትገኘው ሉሲያና ውስጥ ነው የሚኖሩት። ይሁን እንጂ ወደ ሆስፒታሉ የደረሱት የመጀመሪያው ቀዶ ጥገና በተደረገልኝ ማግስት ነበር። እናቴ ጠንካራ ሴት ነች፤ ሁሉን ነገር መቋቋም ትችላለች ብዬ አስብ ነበር። ነገር ግን ወደ ህክምና መስጫ ክፍሉ በገባችበት ጊዜ ወደ እኔ ተመለከተች፤ እናም ራሷን ሳተችና ወደቀች። አባቴ ነበር ከመሬት አፍሶ ይዟት የወጣው።

የእርሷ ራሷን ስቶ መውደቅ ምን ያህል በአስቀያሚ ሁኔታ ውስጥ እንደምገኝ ግንዛቤ ሰጠኝ።

የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናቶች ብዙ ግራ የሚያጋቡ ነገሮችን ጥለውብኝ አልፈዋል። ሰዎች በእርግጥ ሊጠይቁኝ ይመጡ እንደነበር



ወይም በቅዠት ውስጥ ሆኜ እንደማያቸው እርግጠኛ አልነበርኩም። ኢቫና ነርሷ እንደነገሩኝ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ አዕምሮዬን እስታለሁ።

ሆስፒታሉ፣ በየቀኑ ጠያቂዎች ጥቂት ጥቂት ሆነው እየገቡ እንዲጎበኙኝ ፈቀደ። ምንም እንኳን ቃል ባይናገሩም ሃዘናቸውን ርህራሄን የተሞሉ አይኖቻቸው ምን እንደተሰማቸው በግልጽ ይነግሩኝ ነበር። በአዕምሮዬ መዝገብ በግልጽ ጽፌአቸዋለሁ፣ ምክንያቱም በምን ዐይነት ሁኔታ እንደተቀበልኳቸው አውቃለሁና ነው። ወደ ኋላዬ ዘወር ብዬ ሳስበው፤ ምናልባት ተሳስቼ እንዳይሆን እሰጋለሁ። እንደምሞት ፈጽሞ እርግጠኛ ነበርኩ፣ ደግሞም ፈልጌው ነበር፣ በፊታቸው ላይ ከማየው ነገር ነበር ሥለ እራሴ የማስበው ነገር የሚመነጨው።

ትክክል ልሆንም ላልሆንም እችላለሁ፤ ነገር ግን እንዲህ እያልኩ አስባለሁ፤ አሁን እየተመለከቱ ያሉት ቅርጹን አጥቶ የተከመረ የሰው ሰውነት እንጂ ህያው የሆነ ሰው እየተመለከቱ አይደለም። ምንም እንኳን የሚያበረታታና የሚያጽናና ቃል ቢናገሩም በዚያው ሰዓት ውስጥ እንድሞት እንደሚፈልጉ ይመስለኝ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ይገርመኛል፤ የሚመጡት አይኖቼን ጨፍኜ ለዘላለም ከማንቀላፋቴ በፊት ለእኔ ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽና ለመሰናበት ነው ስል አስባለሁ።

የሳንባ ምች በሽታው ቢሄድም ቅሉ፤ ትቶት የሄደውን ሌላ ጉዳት ደግሞ ማከም ነበረብን። ነርሶቹ በየአራት ሰዓቱ ልዩነት ይመጡና የመተንፈሻ አካሎቼን አክመው ይሄዳሉ። ደረቴን መታመታ እያደረጉ በመጫን ጥሩ ጠረን፣ ጥሩ ጣዕም በማይሰጥ ሳንባዎቼን እንዲሸፍን በተደረገልኝ የህክምና መሣሪያ አማካይነት እንድተነፍስ ያደርጉኛል። እንዲህ አይነቱ ህክምና የሳንባዎች በሽታው ተመልሶ እንዳይጀምር የተከላከለው ሲሆን ሳንባዎቼ እንዲያገግሙም ረድቷል። እነቃና ሰዎች

ወደ ክፍሉ ሲገቡ እመለከታለሁ፤ እናም እንዲህ ሲል እሰማለሁ፤ “አይ ደግሞ መጡ ... በዚያ ነገር አማካይነት እንድተነፍስ ሊያደርጉኝ ነው፤ ያንን ጭነት ይጭኑብኛል፤ በጉሮሮዬ አካባቢ የተከማቸውን ቆሻሻ ፈሳሽ መጥረጊያውን ደግሞ ሊነቅሉት ነው::” የአስቸጋሪ ህክምናነቱን ያህል ውጤታማ ሆነ:: የሂርማነን ህክምና ማዕከል የህክምናው ቡድን መሪ የሆኑት ዶ/ር ሆቺንስ በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ ይመላለሳሉ:: ዶ/ር ሆቺንስ ካላቸው መልካም ባህሪያት ጋር ተደምሮ አንድም በሽተኛቸው በሞት እንዳይወስድ እንደ አዳኝ ውሻ የመናጠቅ ቁርጠኛ የሆነ እልህ አላቸው::

መተንፈስ እንደሚገባኝ ነገሩኝ:: “አሁን አታቋርጥ፣ አታቋርጥ:: መሞከርህን ቀጥል” የሚናገሩት ቃሉን ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም ልክ እንደ እኔ ታማሚ የሆኑ ይመስል ከእኔ ጋር ሆነው ሲታገሉ ይሰማኛል:: “ተስፋ አትቁረጥ፤ መሞከርህን ቀጥል”

ብዙውን ጊዜ ለመተንፈስ የሚያስፈልገኝ ሃይል ስላልነበረኝ መሞከሬን አቆም ነበር::

በፊታቸው ላይ ሃዘን የተሞላበት ስሜት እመለከታለሁ፤ ቆይቶም ያ የሃዘኔታ ስሜት እልህ ወደተሞላበት ንዴት ይለወጣል:: “የምልህን ትሰማኛለህ? ተንፍስ! አሁን ተንፍስ! ተንፍስ! ደግሞ እስል! ቀጥል!”

ራሴን በአሉታ እወዛውዛለሁ:: ከዚያ በላይ ለመንቀሳቀስ እንዳች ኃይል አልቀረኝም::

“ይሄ የምንደራደርበት ጉዳይ አይደለም:: አሁኑኑ አድርገው! ተንፍስ!”



“አልችልም”

“ጥሩ፤ አታድርገው:: በቃ እንደምትክ እወቅ:: የማታደርገው ከሆነ ትሞታለህ:: የምናገረውን እየተረዳኸው ነው?”

እኔ መኖር አልፈልግም ነበር:: እርሳቸው እየጮሁ ሲያበረታቱኝ ግን አንድ ነገር ሆነ::

መተንፈስ ጀመርኩ::

ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የህክምና ቡድኑ መቀመጥ እንድችል እግሬን እንዴት ማንሳት እንዳለባቸው መመካከር ጀመሩ:: ቀና ብሎ መቀመጥ ደግሞ በራሱ በርካታ ደረጃዎች የሚጠይቅ ህክምናን የሚያካትት ነበር:: ከዚያ በኋላ ባለው ሕይወቴ በጎኔ ጋደም እላለሁ ወይም በሆዴ እተኛለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር::

አንድ ጊዜ በዚያው በቀዶ ጥገና ክፍሉ ውስጥ ሳለሁ፤ አይኔን ጨፍኜ በገለጥኩ ቁጥር በየሰኮንዱ ፍጥነት አንድ ሰው ስድስት ኢንች ያህል ርዝመት ያለውን ምግብ የተሞላ ማንኪያ ወደ አፌ እየሰደደ ያስገባል::

“አንድ ጊዜ ብቻ አፍህን ክፈት”

የወንድ ሰው ድምጽ እንደሆነ አወቅሁ::

አይኔን ገለጥኩና አተኩሬ ተመለከትኩ:: አንድ ግዙፍ ሰው ማንኪያውን እንደጨበጠ ቆሟል:: የኦክስጂን ጭንብሌን ከፊቴ ላይ

አንስቶ ማንኪያውን በዝግታ ወደ አፌ ያስገባል፤ “እንዲያ ነው እነጂ፤ ደግሞ አንድ ድገም ... ትንሽ”

እየታዘዘኩ እውጣለሁ፤ በዚያው ቅጽበት አዕምሮዬን እየሰበሰብኩ እየሆነ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ለመገመት እሞክራለሁ::

ቀስ እያልኩ ያ ድምጽ በአሊቪን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ባለብጫ ጃኬቶቹ የተሰኘው የእግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝና የአትሌቲክስ ቡድን መሪ የሆነው የስታን ማውልዲን ድምጽ መሆኑን ተገነዘብኩ:: በህክምና በማገገም ላይ በነበርኩበት ጊዜ ሌት ልጃችን ከስታንና ከባለቤቱ ከሱዛን እንዲሁም ከሁለቱ ልጆቻቸው ጋር አብራ ነበር የምትኖረው:: አሰልጣኙ ማውልዲን ምግብ ባለመውሰዴ ምክንያት አሣሣቢ በሆነ ሁኔታ ክብደቴ እየቀነሰ መምጣቱን ሰማ (ከዚያ በኋላ ከክብደቴ የቀነሰው ጥቂት ፓውንዶች ብቻ ቢሆንም፤ ሆስፒታል በገባሁባቸው በመጀመሪያዎቹ ስድስት ሳምንታት ወደ ሃምሳ ፓውንድ ያህል ክብደት ጥዬ ነበር)::

ስታን ሁኔታውን በሰማ ጊዜ፤ ወደ ሂርማንን ሆስፒታል የሚመጣበትን ጊዜ አመቻቸ:: የሚመጣው ግን ዝም ብሎ ጎብኝቶኝ ሊሄድ አልነበረም:: ምግቤን እንድትሰጠኝ ነርሷን ጠየቃት፤ እናም እስክነቃ ድረስ አጠገቤ ተቀምጦ መጠባበቁን ቀጠለ::

ሙሉ ለሙሉ መንቃቴን ካረጋገጠ በኋላ፤ ምግቡን በማንኪያው እየሰፈረ ወደ አፌ ይልክና መናገሩን ይቀጥላል ያ ደግሞ በተቻለኝ መጠን ምግቡን እንዳለምጥ ጊዜ ለመስጠት ነበር:: ያ በዚያ ሰው የተደረገው ትህትና የተሞላበት የመስዋእትነት ተግባር፤ በማገገሚያው ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ከማስታውሳቸው ማስተዋል ከተሞላባቸው



ሥራዎች አንዱ ነው:: የስታን ጥንካሬና ርህራሄ የተሞላበት የተዋሃደ ባህሪው የተለየ ሰው ያሰኘዋል::

ስለ ኤልዛሮቭ ፍሬም በገለጽኩበት ጊዜ ምናልባት የህክምና ሂደቱን ቀላል አድርጌ ገልጬው እንዳይሆን እሰጋለሁ:: ከዚያ በጣም የተለየ ነው:: ኢቫ የወሰነችው ውሳኔ አንድ ሰው ብቻውን ሊወስነው የሚችል ውሳኔ አልነበረም:: ኤልዛሮቭ የህክምና ሂደት በእኔ ላይ እንዲከናወን መወሰን ነበረባት::

በመጀመሪያ ላይ ይህ መሣሪያ የተሠራው እግርን ቀጥ አድርጎ ለማቆየት ነበር:: መሣሪያው አስቀድሞ ሲፈለሰፍ የተሠራው ገና ከውልደታቸው ጀምሮ አንደኛው እግራቸው ከሌላው እግራቸው ይልቅ አጭር ለሆነ ግለሰቦች ነበር:: እስከ አሥራ ሁለት ኢንች የእግር መበላለጥ ላጋጠማቸው ሰዎች ሁሉ የሚሠራ ነው:: ይልቁንም በተሽከርካሪ ብስክሌቶች ለሚንቀሳቀሱ፤ በብረት ድጋፍና በምርኩዝ ለሚሄዱ ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል:: የኤልዛሮቭ ፍሬም በአካባቢ ያሉ ሌሎች የሰውነት አካላት ሳይጎዱ አጥንቱ እንዲያድግ የሚያደርግ መሣሪያ ነው:: በመሣሪያው አማካይነት ሰውነት በአጥንቶቹ መካከል ባለው ክፍት ስፍራ ላይ አጥንት ያበቅላል::

ኢልዛሮቭ የተሰኘው ይህ አጥንት አብቃይ መሣሪያ ውጫዊ አያያዥ (ማፅኛ) ተብሎ ይጠራል:: የሳይቤሪያ ዜግነት ያለው ኤልዛሮቭ የተባለ ዶክተር ነው የፈለሰፈው::

ዶ/ር ኤልዛሮቭ አስቀድሞ መሣሪያውን የሞከረው በበጎች ላይ ሲሆን፤ ያደጉና ተሰብረው የጠፉ አጥንቶች ወይም ገና ከውልደት ጀምሮ

እጥረው የተፈጠሩ አጥንቶች እንዲያድጉ የተደረገ ሙከራ ነው:: እንደኔ ያሉ የጠፉ አጥንቶችን ስማስተካከል ሂደቱ አጥንትን በትክክል መቁረጥን ይጠይቃል:: የፒያኖ ክር ያህል ውፍረት ያላቸው የኤሌትሪክ ሽቦዎች በቆዳና በአጥንቱ ውስጥ እንዲገቡና በኋላም በሌላኛው አቅጣጫ እንዲወጡ ይደረጋል::

መሣሪያው በእርሳስ ውፍረት ያህል ባላቸው ጠፍጣፋ ብረቶች አማካይነት ከወገብ በታች ካለው አጥንት ጋር እንዲያያዙ ይደረጋሉ:: ዶክተሮቹ አራት ረጃጅም ጠፍጣፋ ብረቶችን ወደ ውስጥ ማስገባት እንዲያስችላቸው በጭኔ ላይ ወደ መቀመጫዬ አቅጣጫ አራት ቀዳዳዎችን በሱ:: ይህንን ካደረጉ በኋላ፤ ቢያንስ ቢያንስ ለላሣ ቀዳዳዎች በግራ እግሬ ላይ ተቀደዱ:: አብዛኞቹ ቀዳዳዎች በቀጥታ በአንደኛው የእግሬ አቅጣጫ ገብተው በሌላኛው ወገን የሚወጡ ናቸው:: ትልልቆቹ ቀዳዳዎች ሥጋ ለሥጋ ሄደው በትልቁ የጭን አጥንት ላይ ብረቶቹ እንዲታሠሩ የሚያደርጉ ናቸው:: ስድስት ወራት ካለፈ በኋላ ቁልቁል እግሬን በመመልከት ትናንሾቹ ቀዳዳዎች እየተለጠጡ እንደመጡ ማየት ችዬ ነበር::

በየቀኑ አንድ ሰው እየመጣ የመሳሪያውን ቡሎኖች ያጠብቃቸዋል፤ ይህም የሚደረገው አጥንቶቼ እንዲለጠጡ ለማድረግ ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት ነርሶቹ ነበሩ:: ወደ ቤቴ ከገባሁ በኋላ ደግሞ ይህንን የማድረጉን ሃላፊነት ኢቫ ተረከበች:: አንድ አመት በሆነ ጊዜ ውስጥ የግራ እግሬ ትልቁ አጥንት አድጎ የጠፋውን የአጥንቴን ክፍል ሙሉ ለሙሉ ደፈነው:: በጥሩ የፈጠራ ክህሎት የተሠራ መሣሪያ ነው:: ምንም እንኳን ስቃይን የሚያስከትልና በርካታ ውስብስብ ችግሮች የሚያስከትል ቢሆንም፤



በአጥንት ላይ የሚፈጠርን እጥረት ስማራዘም የሚያስችል ነው:: እኔ፤ "አስቀያሚው ተአምረኛ" እያልኩ ነው የምጠራው::

ስድስት ቀጫጭን ብረቶችም ከግራ እጄ ክንድ አንስቶ ውስጥ ውስጡን በማስፍ በሌላው አቅጣጫ እንዲወጡ ተደርገዋል:: የመዛግ ባህሪ የሌላቸው ጠፍጣፋ ብረቶች በክንዴ ፊት ለፊትና ኋላ ግጥም ተደርገው ታስረዋል:: ምክንያቱም በክንዴ ውስጥ ያሉት ሁለቱም የመጀመሪያዎቹ የእጅ አጥንቶች በመጥፋታቸው ነው:: ጠፍጣፋዎቹ ብረቶች የእርሳስ ያህል መጠን ያላቸው ሲሆን፤ ዶ/ር ግሪደር በስተቀኝ ካለው መቀመጫዬ አካባቢ የወሰዱትና በእጄ ታችኛው ክፍል ላይ የተከሉት አጥንት ፀንቶ እንዲቆይ ለማድረግ ረድቷል:: ዶክተሩ ይህንን ነገር ሲያብራሩት፤ የነዳጅ ጉድጓድ በሚቆፈርበት ጊዜ ናሙና ከመውሰድ ጋር ያይዙታል:: በተጨማሪም ለላሣ ሁስት ካሬ ኢንች የሚሆን ቆዳ ከቀኝ እግሬ ላይ በመላጥ በግራ እጄ ላይ በነበረ ትልቅ ቁስል ላይ ለጥፈውልኛል:: ከዚህ በኋላ ደግሞ በእጄ ላይ በተተከሉት ሁለት አጥንቶች መካከል ቴፍሎን ስትራይፕ የተባስ መሰያ በእጄ ውስጥ እንዲቀበር ተደርጓል:: ይህም የሚረዳው አዲስ የተተከሉት አጥንቶች እርስ በእርስ እንዳይጠጋጉ እንዲረዳ ነው:: እንዲህ በመሆኑም አጥንቶቹ አቅጣጫቸውን ይዘው በአንድነት ለማደግ ይችላሉ::

እንደ አጋጣሚው ሆኖ ይሄኛው የህክምና ሂደት በእኔ ላይ ውጤታማ አልሆነም አጥንቶቹ ተፈውሰዋል፤ ይሁን እንጂ እርስ በእርሳቸው ተገናኝተው ነበር:: በዚሁ ሳቢያ የእጄን መዳፍ መጨበጥ ወይም የሆነ ነገር አንጠልጥዬ መያዝ አልችልም:: ክንዴን ቀጥ አድርጌ መዘርጋትም ይሁን የእጄን መዳፍ ማሽከርከር ወይም ላይና ታች ማድረግ አልችልም:: እጄን ቀጥ አድርጌ ስዘረጋ ሰዎችን ለመጨበጥ

እስከሚያስችለኝ ርቀት ብቻ ነው የሚነሣው:: እጄ በስተግራም ይሁን በስተቀኝ መዟዟር አይችልም:: ሁሉም ነገር አሰቃቂና ስቃይ የተሞላበት እንደሆነ አውቃለሁ፤ በጊዜውም የሚሰማው እንደዚያ ነው:: ይሁን እንጂ ለኤልዛሮቭ ምስጋና ይግባውና ነገሩ ተከናወነ::

አዎ የኤልዛሮቭ መሣሪያ ውጤታማ ሆነ፣ በህክምናው ሂደት ውስጥ በጽናት ከተቋቋምኳቸው ስቃይ ከተሞሉ ሂደቶች መካከል ዋነኛው ነው::

በእግሬ ውስጥ እንዲያልፉ የተደረጉት የኤልዛሮቭ ብረቶች ክብደት አሥራ ሦስት ኪሎ ተኩል ያህል ይሆናል፤ በተጨማሪ በክንዴ ላይ የታሠሩትና የገቡት ብረቶች ክብደት ዘጠኝ ኪ. ግራም ያህል ይሆናል:: ከስምንት ወራት በኋላ፤ በተሽከርካሪ ብስክሌቴ ላይ ተቀምጬም ይሁን እንደገና አራት ወራት ተጨምሮ በምርኩዝ ስንቀሳቀስ በድምሩ ለአንድ አመት ያህል ማለት ነው ያንን ተጨማሪ ክብደት መሸከም ግዴታ ነበር::

በደረስኩበት ሥፍራ ሁሉ የሚያጋጥመኝን በአግራሞት የፈጠጡ አይኖች መገመት ትችላላችሁ? በተሽከርካሪ ጎማ ላይ ተቀምጦ ያንን ሁሉ ብረታ ብረት በሰውነቱ የተሸከመ ሰው ሲመለከቱ ሰዎች ትንፋሻቸው ቁርጥ ይልና አፍጥጠው ይመለከቱኛል::

አዘውትሬ የተለመደ ጉብኝቴን በተሽከርካሪ ብስክሌቴ ላይ ሆኜ ወደ ዶ/ር ግሪደር ቢሮ አደርጋለሁ፤ በዚያ ያሉ ሌሎች ህመምተኞች አስተያየትም የተለመደ ነበር:: ምንም እንኳን እያንዳንዳቸው ጀሶ የተደረገላቸው፣ የብረት ማያያዣ የሚጠቀሙ ወይም በምርኩዝ የሚሄዱ ቢሆኑም፤ ሁሉም ወደ እኔ፣ ወደ ጠፍጣፋዎቹ ብረቶችና በእግሬ ላይ ወደጠለቀው ክብ ብረት አፍጥጠው ይመለከታሉ:: ከዚያ



በኋላ ያለ ምንም ማወላወል አንድ ሰው በሹፈት የሚናገረው "አ! እኔ ክፉኛ የተጎዳሁ መስሎኝ ነበር" የሚሉ ቃላትን ነው:፤ አንዳንድ ጊዜም አንዳንዶች፤ "አንተን ከተመለከትኩ በኋላ እኔን ተሻለኝ" የሚሉኝ ሰዎች አሉ:: ለረዥም ጊዜ ስቃይ ያለው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ የመመዘኛ ደረጃው እኔ ሆንኩ:: በላዬ ላይ ከተከመረው የብረታብረት መዓት የተነሣ ከዓመታት በፊት የሥነ ምድር አጥኚዎች ቢያገኙኝ ኖሮ አዲስ ፍጥረት ያገኙ ይመስላቸው ነበር እያልኩ ለሌሎች እቀልድላቸዋለሁ:: የሰውነት አካሌ አደረጃጀት ሙሉ ለሙሉ ተለውጦ ነበር::

እንደገና ተመልሶ ቀላል የሆኑ የአካል እንቅስቃሴዎችን እንኳን ማድረግ ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነው፤ ትንሽ የምትባል እንቅስቃሴ እንኳን እንደ ተአምር ትቆጠራለች:: ሁልጊዜም ነገሮችን እንዴት ማከናወን እለማመዳለሁ፤ ከተሳካ ልክ እንደ አንድ ታላቅ ድል ይቆጠራል::

ዶ/ር ግሪደር የግራ እግሬንና እጄን የሚተርፍበትን መንገድ ምን ያህል ተግተው ይፈልጉ እንደነበር የተረዳሁት በኋላ ላይ ነው:: በእኔ ጉዳይ ፈጥነው ተስፋ ባለመቁረጣቸው ሁል ጊዜም ምስጋናዬ ትልቅ ነው::

የቀኝ እግሬ ጉልበት ደቆ ነበር፤ ለተወሰነ ጊዜም በጀሶ ታስሬ ነበር:: የጉልበቴን ሎሚ የሚተካ ክብ ነገር ከተደረገልኝ በኋላ ችግሩ ተቃለለ:: ያልተሰበረው የአጥንቴ አካል ቢኖር የቀኝ እጄ ብቻ ነበር::

የኤልዛሮቭ ፍሬም ህክምናው ስኬታማ ቢሆንም ህመሙ ግን ትቶኝ አልሄደም፤ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን::

"እስከመቼ?" እያልኩ ምን ያህል እንደጠየቅኩ በውል አላውቅም። ማወቅ እፈልግ የነበረው ነገር በዚህ መሣሪያ በሚደርስብኝ ስቃይ ምን ያህል ጊዜ መታገስ እንደሚኖርብኝ ነበር። መስራትና አለመስራቱን ለማወቅ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? እንደገና ለመራመድ ምን ያህል ጊዜ ይጠይቀኛል?

ማንም ሰው መልስ አልሰጠኝም፤ መልስ ሊሰጠኝ የሚችልም አልነበረም፣ እኔ ግን መጠየቄን አላቋረጥኩም።

"ጥቂት ወራት" የሚለው የተለመደ መልስ ነበር።

"ጥቂት ሲባል ስንት? " ወጥሬ እይዛቸዋለሁ።

አንዱ ዶ/ር በመጨረሻው እንዲህ አለኝ፤ "ብዙ ወራት፤ ምናልባትም ረዥም ጊዜ።"

"ጥቂት አመታትም ሊወስድ ይችላል ማለትህ ነው?"

"አዎ፤ ምናልባትም ዓመታት"

"እናም እግሮቼንና እጆቼን እንደገና ለማንቀሳቀስ ዋስትና የለም ነው የምትለኝ?"

"ምንም ዋስትና የለም። በድንገት የማመርቀዝ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፤ እናም እግርህን ለማስወገድ የምንገደድበት ሁኔታ ይከሰታል"

"ለወራት ያህል ይህን ስቃይ ታግሼ ከቆየሁም በኋላ ነገሬ ያለ እግር ይጠናቀቃል እያልከኝ ነው?"

በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ።



እንደ እውነቱ ከሆነ መስማት የምፈልገው ያንን አልነበረም። ምንም እንኳን ኢቫም ተመሳሳይ ነገር የነገረችኝ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ የለማሁትን መካድ ነበረብኝ። ሙሉ ለሙሉ ጤናማ እንደምሆን የሚያረጋግጥልኝን ዋስትና ያለማቋረጥ መፈለግ ቀጠልኩ።

መልስ ማግኘት እፈልጋለሁ፤ ምናልባትም ከዚያም በላይ እንኳን ደህና እንደምሆን ዋስትና እፈልጋለሁ። ከዚያ ሆስፒታል ውስጥ በሁለት እግሮቼ እየተራመድኩ መውጣት መቻልን እፈልግ ነበር፤ እናም ወደቀደመው የተለመደ የሕይወት እንቅስቃሴ መቀላቀል። ይሁን እንጂ ያንን ዋስትና ሊሰጠኝ ፈቃደኛ የሆነ ወይም ችሎታ ያለው ማንም ሰው አልነበረም።

ብዙ ወራቶች አለፉ፤ አንድ ቀን ግን ወደዚያ ሆስፒታል ተመልሼ ሄድኩና በዚያ የነበሩትን ነርሶች እጅ እየጨበጥኩ ሰላምታ ሰጠኋቸው።

ያንን ኤልዛሮቭ ፍሬም የተሰኘ መሳሪያ ባደረኩባቸው ወራቶች ሌሎች ችግሮችም ነበሩብኝ። ብዙ ጊዜ የማመርቀዝ ሁኔታ ያጋጥመኝ ነበር። በእያንዳንዱ ጊዜም መመረዙ ወደ ሰውነቴ ሁሉ ይሰራጭና ያለ እግር እንድራመድ ሊያበቃኝ ይችላል በሚል ፍርሃት እጠመዳለሁ።

ከሃኪም ቤት ከወጣሁ በኋላም እንኳ የሰውነት መመረዝ ተከስቶብኝ ነበር። ለሶስት ጊዜ ያህል ወደ ሆስፒታል ተመልሼ ገብቻለሁ፤ እናም መመረዙን ለመከላከል ቁጥር ስፍር የሌላቸው ፀረ ታሃስያን የሆኑ መድሃኒቶች ተጠቅሜአለሁ።

ከዚያ በኋላም እንኳን ለብዙ ሌሊቶች፤ "እግዚአብሔር ሆይ እንደገና ወደ መንግስተሰማይ ውሰደኝ። ወደ ምድር ለምን መልስህ

እንዳመጣኸኝ ፈጽሞ አልገባኝም፤ እባክህ በዚህ አትተወኝ" እያልኩ ጸልዩአለሁ::

እግዚአብሔር ለጸሎቴ የሰጠው ምላሽ ቢኖር፤ "አይቻልም" የሚል ነበር::

ዛሬም ድረስ ምክንያቶቹን ሙሉ በሙሉ አላውቅም፤ ነገር ግን ወራቶቹ እያለፉ ዓመታቶችም እየነጎዱ በሄዱ ቁጥር በዝግታ አንድ ነገር ተገነዘብኩ፣ ቢያንስ ቢያንስ ወደ ምድር የተመለስኩባቸው ጥቂት ምክንያቶች ተገለጹልኝ::

የፈውስ ሂደቱ ጀመረ:: በዚያ ሆስፒታል አልጋ ላይ ዕለት ዕለት ተጋድሜ፤ እግዚአብሔር መልሶ ወደ ምድር እንደላከኝ በዝግታ መቀበል ጀመርኩ:: ያንን ሁሉ በአካሌ ላይ የደረሰ ስቃይ ለምን በጽናት መቀበል እንደነበረብኝ፣ ለምን እንደሆነ አላውቅም፤ ነገር ግን ዴቪድ ጃንቲሊስ የተናገራቸውን ቃላት ዝም ብዬ ማሰላሰሌን ቀጠልኩ:: እርሱና እጅግ ብዙዎች እኔ በሕይወት እንድኖር በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ጮኸዋል:: እግዚአብሔር ጸሎታቸውን የሰማ በመሆኑ ምክንያት በሕይወት መቆየቴ የሆነ ዓላማ አለው::

በቀናት መካከል ባለፉ መጠነ ሰፊ ስቃዮች ውስጥ የዴቪድን ቃላት አስታውሳቸዋለሁ:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሕይወት በመኖሬ ያለው ዓላማ ነው በሕይወት እንድቆይ ያደረገው ስል አስባለሁ::

በሄርማነን ሆስፒታል ቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ ለአሥራ ሁለት ቀናት ያህል ቆይቻለሁ:: ወደ ታችኛው የቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል



እስኪያዘዋውሩኝ ድረስ ሌላ አራትና አምስት ቀናት በዚያው በሄርማነን ሆስፒታል ውስጥ ቆይቻለሁ:: ሁለቱም ሆስፒታሎች በዓለም ላይ ከሚገኙ ታላላቅ የህክምና ማዕከሎች የሚመደቡ ናቸው:: በቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ለ105 ቀናት ቆየሁ:: ወደ ቤት ከተመለስኩ በኋላ ለአሥራ ሦስት ወራት ያህል ተኛሁ:: ሰላሣ አራት የቀዶ ጥገና ህክምናዎች ተደረጉልኝ:: ያስምንም ጥያቄ ዛሬ በሕይወት ያለሁት ሰዎች ይጸልዮልኝ ስለነበር ነው::

ከዴክ ዋንሪከር ጀምሮ በሃገሬ ምድር የሚገኙ አብዛኛዎቹም የማላውቃቸው ሰዎች ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር አንብተዋል::

ምናልባትም ትልቁ ተአምር ያ ነበር:: ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ፣ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን አከበረ::

ዛሬ ወደ ኋላ ዘወር ብዬ ስመለከት፤ እግዚአብሔር እኔን ለማዳን ምን ያህል ሰዎች እንደተጠቀመ ይገርመኛል:: ዲክ ዋንሪከር ያላቋረጠ ፀሎቱን በመቀጠሉ ሕይወቴን ታደገ:: ዶ/ር ግሪደር ያንን የመጀመሪያ የቀዶ ጥገና ህክምና በማድረግ እጄና እግሬ እንዲተርፍ አደረጉ:: ዶ/ር ሆቼንስ ከቀዶ ጥገናው ህክምና በኋላ ሕይወቴን አተረፏት፤ ምክንያቱም ልክ እንደ አዳኝ ውሻ ተናጣቂ በሆነ እልኸኝነት "መኖር አለብህ" የሚል ቁርጠኛ አቋም የነበራቸው በመሆኑ ነው:: በቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል ውስጥ ያሉ ሁልጊዜ የሚያበረታቱኝ የድንገተኛ አደጋ ክፍል ነርሶች ቀንና ሌሊት ይንከባከቡኝ ነበር:: እያንዳንዳቸው የተጫወቱት ሚና ቀላል አልነበረም::

የቀዶ ጥገና ህክምና ክፍሉን ለቅቄ የወጣሁት የዴቪድ ጀንቲሊስና በሌሎች ፀሎት ነበር። "እኛ ይህንን እንወጣዋለን። ለመኖር አንተ ማድረግ የሚገባህ ነገር የለም። በዚህ ጉዳይ ላይ እኛ እንጸልያለን"

እንደማልሞት እያወቅኩ መጣሁ።

የእግዚአብሔር ሰዎች እንድሞት አልፈቀዱም።



[redacted]

"እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፤ እረዳህማለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ።"

ኢሣ 41፥10

ምንም እንኳን ሆን ብለው ባይሆንም፤ ጠያቂዎች ሁኔታዬ እንዲባባስ ምክንያት ሆኑ። ስለ እኔ ግድ ያላቸው ነበሩ፤ እናም ያንን ስሜታቸውን ለመግለጽ ይፈልጉ ነበር። ለእኔ ግድ ያላቸው በመሆኑ ምክንያት በዓለም ላይ የተለመደውን ነገር ነበር የሚያደርጉት። ይጎበኙኝ የነበረው በህክምናው ሆስፒታል ውስጥ በነበረው የመኝታ ክፍሌ ነው። ችግሩ ደግሞ ያ ነበር።

በክፍሌ ውስጥ የሚፈጠረው የማያቋርጥ የመግባትና የመውጣት እንቅስቃሴ አሰልቺ ሆኖብኝ ነበር። እዚያ ተኝቼ እንዲቀመጡ በማድረግ ላጫውታቸው አልችልም። ምናልባትም እንደ ቤተክርስቲያን መጋቢነቴ መጫወት የሚገባኝን ሚና መጫወት ወይም እነርሱን ለማዝናናት የተወሰነ የሃላፊነት ስሜት ይሰማኝ ነበር። ጠያቂዎቼን ክፍሉን ለቀው እንዲወጡ በመጠየቅ ወይም ዳግመኛ እንዳይመጡ በመናገር የማንንም ስሜት መጉዳት አልፈለግኩም።